መስከረም

* ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና

* የድኅረ—ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ

* የፖሊቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈ ሐሳብና የተግባር ዕውቀት

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 9 ቁጥር 36
ታኅሣሥ 1981

ቅጽ 9 ቁጥር 36
ታኅሣሥ 1981

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና 9
በላቸው ሙሉጌታ

* የድኅረ—ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ 35
በላይነህ አስጉ

* የፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈ ሐሳብና
የተግባር ዕውቀት 53
ደስታ ወዳጆ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቍጥር — 80001
የስልክ ቍጥር — 113000

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

ሰላም ፣ ለዕድገት መሠረታዊ ዋስትና

ባለፉት የአብዮት ዓመታት በሀገራችን ፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝ
ምን ተጽዕኖ በማስወገድ ለአዲስ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት
ለመጣል በርካታ ተጨባጭ እርምጃዎች ተወስደዋል ። በልዩ ልዩ መልክ
የሀገራችንን ህልውና ለመቀናቀን የተሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመቋቋም ተችሏል ።
በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ መብቱ በእኩልነት የሚከበርበ
ትን ፣ ከኋላቀርነት በመላቀቅ ለብልፅግና የሚበቃበትን ሥርዓት እውን
ለማድረግ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍሏል ፣ ጉልህ ታሪካዊ ውጤቶችን
ለመጨበጥ በቅቷል ። ይሁን እንጂ በጀመረው የማኅበራዊ ዕድገት ጉዞ
እርምጃውን እንዳያፋጥን በሰሜን በኩል የገጠመው ሰላምና አንድነቱን
የሚሻረር ሁኔታ ጋሬጣ ሆኖበት ቆይቷል ።

በክልሉ የሀገራችንን ህልውና የሚፈታተነው ጦርነት የቱን ያህል
ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት መሥዋዕትነት እንደጠየቀ በተለያዩ አጋጣሚ
ዎች ተገልጿል ። በተለይ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ
ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ባቀረቡት ሪፖርት እንደገለጹት በመከላከያ
ረገድ ብቻ እንኳን የሚደረገው እጅግ ከፍተኛ ወጭ ሁኔታውን በግልጽ ያሳያል።
በሪፖርቱ እንደተመለከተው "የመከላከያን በጀት ብንመለከት በ1966 105.8
ሚሊዮን ብር የነበረው በ1981 1 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ደርሷል ። ...በ1980
የመከላከያ ወጭ ያለው ድርሻ ከጠቅላላው ምርት ውስጥ 15 በመቶ ፣ ከመደበኛ
በጀት 50 በመቶ ፣ ከጠቅላላው ገቢ 54 በመቶ ደርሷል ።" በዚህ መልክ በቀጥታ
ለመከላከያ ከሚደረገው ወጭ ሌላ በዐረ አንድነት ቡድኖች የሚፈርሱ
ተቋሞችን ፣ የሚወድሙ ልዩ ልዩ የአገልግሎት መስጫ አውታሮችንና
ንብረቶችን መልሶ ለማቋቋም ፣ ለመጠገንና ለመተካት የሚወጣው ገንዘብ
እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው ። ይህም ብቻ አይደለም ። ችግሩ ባለባቸው
አካባቢዎች ለሚገኙት ዜጎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን
ለማድረስ የሚደረገው ጥረትና ወጭም እጅግ ከባድ ነው ።

እንደሚታወቀው በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ በኤርትራ ክልል ያለው
ችግር በአብዮቱ ዓመታት የተፈጠረ አይደለም ። ይልቁንም ኤርትራ እንድትገነ

ጠል የማድረግ ባሕርዩ መሠረት እንዲያጣ የተደረገው በአብዮቱ ነው ። በተለይ በፊውዳሉ አገዛዝ ዘመን በክልሉ የነበረው እንቅስቃሴ ፀረ ፊውዳል ነው በሚል በውስጥም ሆነ በውጭ የተወሰነ የተራማጆች ድጋፍ እንደነበረው የሚዘነጋ አይደለም ። ሆኖም የመላ ኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የእኩልነትና የፍትሕ ጥያቄ የሚያካትተው ሀገር አቀፍ አብዮት ሲቀጣጠል በኤርትራ ያለው እንቅስቃሴ ምንነት ይፋ ወጣ ። በእንቅስቃሴው ውስጥ በተሰለፉት መካከልም መጠየየቅ ግድ ሆነ። በተፈጠረውም ቅራኔ ውስጥ አቋማቸው ታፍኖ የመገንጠልን ጠባብ ዓላማ እንደፍጹማዊ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ አድርገው የያዙት የበላይነትን ሊይዙ በቅተዋል።

እነዚህ የመገንጠል ዓላማ የሙጢኝ ያሉትና ይህንኑ ለማስፈጸም ጦርነትን ዋንኛ ምርጫቸው ያደረጉት ወገኖች ለጭፍን ዓላማቸው ድጋፍ ለማስገኘት አመች የመሰላቸውን የፖለቲካ አቋም ሲለዋውጡ ቆይተዋል ። ቀደም ሲል ያደናግሩበት የነበረውን የፀረ ፊውዳል አቋም ከላይ እንደተጠበቀው አብዮቱ ፉርሽ አድርጐባቸዋል ። የብሔር ጥያቄ በሚልም ለረጅም ጊዜ ለማሳመን ሞክረው ነበር ። አልተሳካላቸውም ። በቀይ ባሕር አካባቢ አረባዊነት ጐላ ብሎ ስለሚታይ ምናልባት ዐረባዊ ነን በማለት ከኢትዮጵያ ልዩ መምሰል ተቀባይነት ያስገኝ ይሆናል በሚልም ብዙ ተሞክሯል ። በመጨረሻም ሌላው ሁሉ ሳያዋጣ ሲቀር ጣሊያን በክልሉ በቅኝ ገዢነት ለተወሰነ ጊዜ ያደረገውን ቆይታ ምክንያት በማድረግና ግዙፉን የኢትዮጵያ ታሪክ ገሸሽ ለማድረግ በመሞከር ለማደናገር ይጥራሉ ። "ቀድሞ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት የነበረች ኤርትራ እንደገና በኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ሥር ወደቀች ፣ ስለዚህም ትግላችን ፀረ ቅኝ አገዛዝ ነው" ይላሉ ። የኤርትራ ክልል በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች እንደተፈለገ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ተቀጥሮ ለተወሰነ ጊዜ የመቆየቱ ጉዳይ የማያጠያይቅ ቢሆንም፣ ይህ ግን የክልሉን ታሪክ ምን ያህል ከኢትዮጵያ ታሪክ ጨርሶ የተለየ ሊያደርገው "እንደቻለ" በተለይ ከተጨባጩ ሁኔታ ይበልጥ ሊያሳምን የሚችል አይኖርም ። እርግጥ የመገንጠሉ ዓላማ እንዲሳካላቸው የሚፈልጉ ወገኖች በአንዳንዶች ዘንድ የፈጠሩት ውዥንብር በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

በአጠቃላይ የጦርነት ሁኔታ ባስከተለው አለመረጋጋትና ተገንጣዮቹ ለጠባብ ዓላማቸው በሕዝብ መካከል መቃቃር እንዲፈጠር ባደረጉት ያልተቋ ጠበ ሙከራ በርካታ ዜጎች በየባዕድ አገሩ ለስደት መዳረጋቸው ይታወቃል ። ብዙዎቹ ከሀገራቸው ውጭ ከማኅበራዊ ኑሮ ተገልለው መብታቸው በሕግ የማይከበርበት የሰቀቀን ሕይወት መግፋታቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው። አልፎ አልፎ በመጠኑ በኢኮኖሚ የቀናቸው ሊኖሩም ቢችሉ በባዕዳን መካከል የሚደርስባቸው ተጽዕኖ የሚያዝናና አይደለም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ጊዜ እየሄደ ፣ ትውልድ እያለፈ ትውልድ የመተካቱ አዝማሚያ በየባዕድ ሀገሩ ምን

ዓይነት ዜጎችን እያፈራልን ነው የሚለው ጥያቄ እጅግ የሚያሳስብ ነው ። ሁሉም የሚያምረው ያለጥርጥር በሀገር ነው ። ባህል ፣ ቋንቋ ፣ እምነት ፣ በአጠቃላይ የእራስ ማንነት ሊከበር የሚችለው በእራስ ሀገር ነው ። የስደት ሕይወት የሚያስከትለው ጉዳት በተሰደደው ዜጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በሀገርና በወገንም ነው ። ከዚህ አንፃር በተለይ በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በኩል የደረሰው ጉዳት የቱን ያህል የከፋ እንደሆነ የተሠወረ አይደለም ።

የኤርትራ ተገንጣዮች ያንኑ ጠባብ ዓላማቸውን ዳር ለማድረስ ያልፈጸሙት ድርጊት የለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት እንዳይደርስባቸው በእሩቁ ለመከላከል በነበራቸው ፍላጐት ትግራይ ክልል ውስጥ መሰላቸው የሆነ ቡድን መፍጠራቸው አንዱ አድራጐታቸው መሆኑ ይታወቃል ። የእነርሱ ዓላማ ኤርትራን መገንጠል ሲሆን አብዮቱን ከራሳቸው ራቅ አድርገው ለመገደብ በነበራቸው ምኞት በትግራይም ለፈጠሩት ቡድን ያሸከሙት ግብ "ሐርነት ትግራይ" ወይም ትግራይን ነፃ ማውጣት የሚል ነበር ። በዚህም የማይመስል ዓላማ ምክንያት የብዙ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ደም በከንቱ እንዲፈስ እየተደረገ ነው።በእርግጥ የዚህ የማይመስል ዓላማ ተቀባይነት በማግኘት ከቶውንም እንደማይሆን ሲታይ ትግራይ ውስጥ የሽብር ተግባር የሚያካሂደው ቡድን የተወሰነ አካሉን "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ" (ኢሕዴን) የተሰኘ ካባ በማልበስ ወደጐንደርና ወደወሎ የመሳብ ሙከራ ከጀመረ ውሎ አድሯል ። በቅርቡ ደግሞ ይባስ ብሎ በእራሱና "ኢሕዴን" በሚለው ፍጡሩ መካከል ስምምነት ላይ ተደርሶ "የጋራ ግንባር" ፈጥረናል ብሎ ለፍፏል ። "ግንባሩ" የሚመራበት "ፕሮግራም" ነው ብሎ ባወጣውም ውስጥ በተራ ቁጥር 13/ሀ/ የኤርትራን መገንጠል እንደሚደግፍ በግልፅ አመልክቷል ። ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል በሚመለከትም አቋሙ "ዋናው ቅራኔ የብሔር ቅራኔ ነው ።" በሚል ብሔረሰቦችን ማቃቃርና በዓላማ አንድነት የአብዮታቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው ።

በሌላ በኩልም ይሄው "ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ" (ሕወሐት) ነኝ የሚለው ቡድን ቀደም ሲል በሚያዝያ 1980 "ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ" (ሕግሐኤ) ወይም "ሻዕቢያ" ነኝ ከሚለው ቡድን ጋር ባወጡት መግለጫ ኤርትራ እንድትገነጠልና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ ብሔረሰቦች ደግሞ በየራሳቸው ጠባብ አቋም እንዲሰለፉ ለማድረግ የሚታገሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል ። በዚሁ መግለጫ ላይ "ሕወሐት" ነኝ ባዩ እራሱን የኤርትራን መገንጠል ደጋፊ የሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካይ አስመስሎ አቅርቧል ።

እነዚህ ቡድኖች በቅርጻቸውና ከየራሳቸው ጠባብ ፍላጐት አንፃር ልዩነት ሊኖራቸው ቢችልም በመሠረታዊ ዓላማቸው አንድ ናቸው ። ይሄውም በተለየየ

አቀራረብ የኢትዮጵያን አንድነት ለመናድ መረባረብ ነው ። በራሳቸው አቅም የተቻላቸውን ያህል ጥፋት ከመፈጸማቸውም ሌላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን በእራሱ እንዲታገል ይገፋፋሉ ። እነሱው ሰላምን እየወኩና የሀገርን ኢኮኖሚ እያደቀቁ መልሰው ሕዝብን "ለችግር ተዳረክ" ብለው ያፌዛሉ ። በአንድ በኩል በሕዝብ ጥቅም ላይ ጦርነት እየከፈቱ በሌላ በኩል ሕዝቡ እንዳይቋቋማቸው "ለጦርነት ለምን ትዳረጋለህ" ብለው ያዘኑለት ለመምሰል ይሞክራሉ ።

እነርሱም ምንም ሊሉና የሚቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ ላይመለሱ ይችላሉ ፡ ወሳኙ ግን ያለጥርጥር ሕዝብ ነው ። የእነርሱም ብርታት ከተለየዩ ፀረ አብዮትና ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ከሚያገኙት ድጋፍ ሌላ ሕዝብን ከማዘናጋትም ጭምር የሚመነጭ ነው። ዋንኛ ዕራቸው ማንነታቸውን ሕዝብ ጠልቶ መረዳት መቻሉ ነው ። ይህ የሕዝብ ግንዛቤ እየዳበረ የመጣ ሲሆን ቀድሞ በፊውዳሉ አገዛዝ ዘመን ተቃውሞ ተቀስቅሶ ከነበረበት የኤርትራ ቆላ በትርቡ በኢትዮጵያዊነት በመጽናት ለክልሉ የራስገዝ ደረጃ ይሰጠው ዘንድ ለጓድ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያም የቀረበው ጥያቄም በባሕርዩ የሕዝብን ፍላጐት የሚያንፀባርቅ እንደሆነ መገመት አያዳግትም ። ጥያቄው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና በአጠቃላይ በሕዝብ ፍላጐት መሠረት ለክልሉ ችግር በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ ማስገኘት እንደሚቻል እምነት ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። ይህ እምነት እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢ መልስ ከማስገኘት ሌላ ዓላማ የሌለው እንደመሆኑ በሰላም አግባብ ያለው ውጤት ላይ መድረስ ይቻላል።

የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ ዛሬ የሦስተኛው ዓለም ወይም የታዳጊ አገሮች ክስተት እንጂ በዕድገት በገፉት ሀገሮች ጊዜ ያለፈበት ጉዳይ ከሆነ ቆይቷል ። በእርግጥ በዕድገት በገፉት ሀገሮች ውስጥም ሆነ በመካከላቸው ቅራኔ የለም ወይም አብቅቷል ማለት አይደለም ። ነገር ግን የቅራኔ አፈታት ሥልታቸው በአብዛኛው መሥዋዕትነቱ በቀለለ በሰላማዊ መንገድ በመሆኑ የከፋ ጉዳት አያደርስም ። የታዳጊ ሀገር ሕዝቦችም ያለጥርጥር ምርጫቸው ሰላም ነው ። በዚህ መንፈስ አብዮታችን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ላለው ችግር መፍትሔ ለማስገኘት በሰላማዊ መንገድም የተደረገው ጥረት በጣም ሰፊ ነው ። ይሁን እንጂ ተገንጣዮች ለተደረገው የሰላማዊ መፍትሔ ጥረት ሁሉ አፍራሽ ትርጉም በመስጠትና ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ሳይቀበሉ ቀርተዋል ። ይልቁንም "ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል"

እንደሚባለው የበለጠ ጥፋት እየፈጸሙ መልሰው በተለይ በውጪው ዓለም ለአብዮታችን የተዛባ ግምት ለማሰጠት ይሯሯጣሉ ። ነገር ግን እነርሱ እንደሚሉት ሳይሆን ባለፉት ዓመታት በተግባር እንደታየው የአብዮታችን ዓላማ ማኅበራዊ ዕድገት ማስገኘት ነው ። ለዚህ ዓላማው ተፈጻሚነት ደግሞ ያለጥርጥር መሠረታዊ ዋስትና ሰላም ነው ። ስለዚህ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ በያሉበት ለአብዮታችን የሰላምና የዕድገት ዓላማ ተግባራዊነት የነበረት ጥረታቸውን ማጠናከራቸው እጅግ አስፈላጊ ነው ።



www.binyamhk.wordpress.com

ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና

በላቸው ሙሉጌታ

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com
WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

በምዕራቡ ዓለም ፕሮፓጋንዳ የገዢው መደብ አስተሳሰብ ማስረጫ ፣ የሰፊውን ሕዝብ ስሜትና ዝንባሌ በተፈለገው አቅጣጫ መምሪያና የመላው ኅብረተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት መቆጣጠሪያ መሣሪያ ነው። በሁለቱ ተቃራኒ ሥርዓቶች መካከል በሚደረገው የርዕዮተዓለም ትግል ሂደት ውስጥ ደግሞ ፕሮፓጋንዳ የሶሻሊዝም አስተሳሰቦች ማጥላሊያና ማዛቢያ ፣ የፀረአብዮት ድርጊቶች መቀስቀሻና ማነሣሻ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ።

ከብሔራዊና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች መለወጥ ጋር የርዕዮተዓለም ትግሉ በሁሉም መልኩ እየከረረና የባሕሪይ ለውጥ እያሳየ በሄደ መጠን የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በባጀት አጠቃቀሙ ፣ በአደረጃጀቱና በስርጭት ስፋቱ ብቻ ሳይሆን በስልቱና በቴክኒኩ ጭምር እየተወሳሰበ ፣ ጥልቀት እያገኘና እያደገ መጥቷል ።

ኢምፔሪያሊዝም የማኅበራዊ ሕይወት የተለያዩ ዘርፎችን (ኢኮኖሚን ፣ ፖለቲካን፣ ርዕዮተዓለምን ፣ ባህልን ወዘተ.) ለመዳሰስ በሚያስችለው መንገድ የአገሮችን ውስጣዊና አካባቢያዊ ባሕርይ በመተንተን የድርጊት ፖሊሲ ነድፎ ፣ የሰላይ ድርጅቶችንና በየአገሩ ያሉትን ፀረ አብዮት ቡድኖች ሳይቀር ዓለምአቀፍ የፕሮፓጋንዳ ተቋሞቹን አቀናጅቶና የዘመኑን አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶችና የምርምር ውጤቶች ተጠቅሞ በሰፊው ሕዝብ ንቃተሕሊና ላይ ጥቃት የሚሰነዝር በመሆኑ የዘመኑ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ባህርይ ከቀድሞዎቹ ወቅቶች ይልቅ በእያሌው የረቀቀና የተወሳሰበ ሆኗል ። ማኅበራዊ ሚናውም የዚያኑ ያህል እየከፋና አፍራሽነቱ እየሰፋ መጥቷል ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳን አፍራሽ ሚና ለመረዳት ምንነቱን ፣ ተግባሩን ፣ ሥልቱንና ቴክኒኩን ተንትኖ መገንዘብ ይጠይቃል ። ይህ ተግባር ደግሞ በበቂ ጥልቀት እየተመረመረ ይሠራ ዘንድ ተቋማዊ ጥናትን ይሻል ። በዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ሐሳቦችን ብቻ ለማስጨበጥ ይሞከራል ።

1. የቡርዧ ፕሮፖጋንዳ ምንነትና ዓይነት

1.1. የቡርዧ ፕሮፖጋንዳ ምንድነው?

የቡርዧ ፕሮፖጋንዳ ሲባል የቡርዧውን መደብ ርዕዮተዓለም አስተሳሰቦች ፣ ፋይዳዎች ፣ የአሠራርና የአኗኗር ሥርዓቶችን ለማስተዋወቅና በሕዝቦች ንቃተኅሊና አስርጐ ለማስገባት የካፒታሊስት መንግሥታት ፣ የቡርዧ ፓርቲዎች ፣ የግል ኮርፖሬሽኖችና ድርጅቶች የሚያሰራጩት ዓላማ ያለውና በዕቅድ የሚከናወን ተግባር ነው ።[1]

ይሁንና ለቡርዧው ፕሮፖጋንዳ የሚሰጠውን እንዲህ ዓይነቱን መደባዊና ወገናዊ ትርጉም ቡርዧዎች አይቀበሉትም ። ምክንያቱም በቡርዧው አስተሳሰብ መሠረት ፕሮፖጋንዳ አንድ የተወሰነ ቡድን የኅብረተሰቡን ንቃተኅሊና ለራሱ ዓላማዎች የሚገለገልበት ሁለንተናዊ መሣሪያ እንጂ መደባዊ ባሕርይ ያለው አይደለም ።[2] የቡርዧውን ፕሮፖጋንዳ ምንነትና የመሰራጫ ስልቶቹን ለመረዳት የቡርዧው ምሁራን እራሳቸው ስለፕሮፖጋንዳ ያላቸውን ግንዛቤ መመርመሩ ተገቢ መነሻ ይሆናል ።

ሮበት ኬ. ሜርቶን የተባለ ምሁር "ማኅበራዊ ንድፈሐሳብና ማኅበራዊ ፕሮፖጋንዳ" በተሰኘው መጽሐፍ ፕሮፖጋንዳ ሲባል ለኛ የሚገባን በኅብረተሰቡ ዘንድ አከራካሪና አወያይ የሆኑ ጥያቄዎችን አስመልክቶ ሰዎች በሚኖራቸው አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶችና ተግባራት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ማናቸውም ዓይነት ተምሳሌዎች (Symbols) ናቸው ። እነዚህ ተምሳሌዎች በእጅ የተጻፉ ፣ በእትም ፣ በንግግር ፣ በምስል ወይም በሙዚቃ የቀረቡ ሊሆኑ ይችላሉ ። ይሁንና አንድ ጉዳይ በሕዝቡ ዘንድ የመወያያና የመከራከሪያ ርዕስ እስካልሆነ ድረስ ፕሮፖጋንዳ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም በማለት ጽፏል ።[3]

ፕሮፖጋንዳ በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ፣ እምነት ፣ አስተሳሰብና አድራጐት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር መረጃዎችን ፣ ዜናዎችን ፣ ልዩ መልዕክቶችን ፣ ጥሪዎችንና "የማሳመኛ ነጥቦችን" ማሰራጨት ማለት ነው ። ለግልጋሎት የሚውሉት "የማሳመኛ ነጥቦች" ዓይነት በአሠራጩ ቡድን ባሕርይ የሚወሰን ነው [4] የሚለው ሌላው ግንዛቤ ከ1953 ገደማ ጀምሮ በአሜሪካ ምሁራን ዘንድ በስፋት ተቀባይነት አግኝቷል ።

ቹካስ የተባለው አሜሪካዊ ምሁር "ፕሮፖጋንዳ ዳብሯል" በተሰኘው መጽሐፉ ፕሮፖጋንዳ በቅድሚያ የታቀደን የተወሰነ ቡድን ፍላጐት ለማሟላት እንዲቻል ሰዎችን ለተግባራዊ ክንዋኔ ለማነሣሣት በማሰብ ሆን ተብሎ የተዛባን አስተሳሰብ በተቀናጀ መልኩ ማሰራጨት ነው ሲል አስፍሮታል ።[5]

በማኅበራዊ ሳይንስ ኢንሳይክሎፒዲያ ውስጥ ፕሮፖጋንዳ በተምሳሌዎች (በቃላት፣ በእንቅስቃሴዎች ፣ በዓርማዎች ፣ በምስሎች ፣ በቅርጻቅርጾች ፣ በሙዚቃና በመሳሰሉት) አማካይነት ሕዝቡ አከራካሪ ናቸው ብሎ ከሚመለከታቸው እምነቶች ፣ ፋይዳዎችና ዘይቤዎች ጋር የተዛመዱትን አስተሳሰቦቹንና አድራጐቶቹን ሆን ብሎ ለራስ ዓላማዎች መገልገል ነው የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል ።[6] ይህም ትርጓሜ የተለያዩ የቡርዧ አስተሳሰቦችን አካትቶ ያቀረበና በምዕራቡ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ነበር ።

ከላይ ለአብነት ያህል የተመለከትናቸውንም ሆኑ ሌሎችን ስለፕሮፖጋንዳ የተሰነዘሩትን የቡርዧ ምሁራን ግንዛቤዎች በጥሞና ብናስተውል የፕሮፖጋንዳን ገቢራዊ ሂደት በመግለጽ ላይ የተመሠረቱ ትርጓሜዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን ። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ የፕሮፖጋንዳውን ሂደት በማሳየት እንጂ የአድራጊውን (የፕሮፖጋንዳውን ባለቤት) መደባዊ ባሕርይ አያመለክትም ። በመሆኑም ቡርዧው ከዚህ አቀራረብ አኳያ ለፕሮፖጋንዳ ትርጓሜ ለመስጠት መነሣቱ ያለምክንያት አይደለም ። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ የሚመረጠው የፕሮፖጋንዳን መደባዊ ባሕርይ ለመሸፋፈን ስለሚያስችል ነው ።

የቡርዧው ፕሮፖጋንዳ መሠረታዊ ዓላማ ዕውቀትን በተለይም ሳይንሳዊ ዕውቀትን በማሰራጨት የሕዝቡን ባሕል ማዳበር ሳይሆን በተለያዩ ስልቶች አማካይነት የሕዝቡን ንቃተኅሊና ማዛባት ፣ ማነሣሣት ለራሱ ዓላማ ሆን ብሎ መገልገል መሆኑን በመግለጽ የቡርዧ ምሁራን ለፕሮፖጋንዳ የሰጡት ትርጉም ጽንሰሐሳቡ ለአፍራሽ ተልዕኮ መግለጫ ብቻ እንዲያገለግል አድርጐታል ። በዚህም የተነሣ የዛሬዎቹ የቡርዧ ምሁራን የራሳቸውን የፕሮፖጋንዳ ተግባራት ፕሮፖጋንዳ ብለው ከመጥራት ተቆጥበዋል ። ይልቁንም "የማርክሲዝም ፕሮፖጋንዳ" "ቀይ ፕሮፖጋንዳ" ወዘተ· በማለት "ፕሮፖጋንዳ" የሚለው ጽንሰሐሳብ ለሶሻሊዝም ብቻ የሚያገለግል አድርገው ለማቅረብና እንዲለመድ ለማድረግ ይሞክራሉ ።

በአኳያውም የራሳቸውን የፕሮፖጋንዳ ተግባራት "ዲሞክራሲ" ፣ "ሰብአዊ መብት ማስከበር" ወዘተ·[7] ብሎ በመጥራት መሰሪ ተግባራቸውን ይሸፍናሉ ።

በሌላ በኩል የቡርዧ የፕሮፖጋንዳ ምሁራን በሰፊው ሕዝብ ንቃተኅሊና ባመቻቸው መንገድ ለመጠቀም እንደሚችሉና እንዲያውም ሰፊው ሕዝብ በነቃ ግንዛቤ የማይመራ ፣ ግብታዊና ወደተፈለገው አቅጣጫ ሊዋልል የሚችል የሰዎች ስብስብ ተደርጐ መታየቱን ቀደም ሲል ለፕሮፖጋንዳ ከሰጡት ትርጓሜዎች መገንዘብ እንችላለን ። በርግጥም ቡርዧው የሰፊውን ሕዝብ በተለይ ደግሞ የሠራተኛውን መደብ እንቅስቃሴ በተለያዩ ሁኔታዎች ከሚፈጠረው ትርምስ (Crowd)* ለይቶ አይመለከተውም ። ከዚህም በመነሣት ፕሮፖጋንዳ አድራጊውን ክፍል "በእረኛ" ፣ የፕሮፖጋንዳ ተደራጊ የሆነውን ሰፊ ሕዝብ ደግሞ "እረኛ በሚሻ መንጋ" ይመስሉታል ።[8] ይህ ደግሞ የቡርዧ ምሁራን የሰፊውን ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት እንዴት አንቋሸው እንደሚመለከቱና ለታሪክ ያላቸውን የተዛባ ግምት በገሀድ ያሳየናል ።

---

* የሰዎች ትርምስ (crowd) መዋቅር አልባ የሆነ የሰዎች ስብስብ ነው ። በአንድ ያልተጠበቀ (አጋጣሚ) ወይም በቅድሚያ በታሰበ ሁኔታ ወይም በግብታዊ ሂደት አማካኝነት የሚፈጠርና ወደ በለጠ ስሜታዊ ሁኔታዎች በመሸጋገር እየሰፋ የሚሄድ ማኅበራዊ ክስተት ነው ።

ፕሮፓጋንዳ በሰፊው አግባቡ ከተወሰደ አንድ የተወሰነ ግለሰብ ወይም ቡድን በሌላው ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ፤ አንድን የተወሰነ አስተሳሰብ የሚያሰራጭ ሂደት ነው ። ይህ የሥርጭት ሂደት አንድ መልዕክት ከአድራጊው ወደ ተደራጊው እንዲሸጋገር ከማድረጉም በላይ ተደራጊው ለተግባራዊ ክንዋኔ እንዲነሣሣ ያዘጋጀዋል ። በመሆኑም ይህ የሥርጭት ሂደት አንድን ክንውን የመግለጽ ወይም የማብራራት ብቻ ሳይሆን የማነሣሣት ወይም የመቀስቀስ ባሕርያትን አቀናጅቶ የያዘ ነው ። ሌኒን የስርጭቱን ሂደት የፕሮፓጋንዳ ተግባርና የቅስቀሳ ተግባር በማለት በሁለት የከፈለው ይህን የሐሳብ ስርጭት ባሕርይ በመገንዘብ ነበር ።[9] በነዚህ የስርጭት ሂደቶች አማካይነት የሚተላለፈው መልዕክት (አስተሳሰብ) ማኅበራዊ ዕድገትን ሊያፋጥን ወይም ሊያጓትት የሚችል ነው ። በመሆኑም የአንድ ፕሮፓጋንዳ ተራማጅነትና አድኃሪነት በሚሰራጩ አስተሳሰቦች ይዘትና ውጤት ይወሰናል ። የፕሮፓጋንዳው መልዕክት ይዘትና ውጤት ደግሞ በፕሮፓጋንዳ አድራጊው መደባዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ነው ። ስለዚህም ፕሮፓጋንዳ ቡርዧዎች እንደሚሉት መደብአልባ ወይም ከመደብ በላይ ሳይሆን መደባዊና በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ማኅበራዊ ክስተት ነው ። በመሆኑም በቡርዧው ፕሮፓጋንዳና በሶሻሊስት ፕሮፓጋንዳ መካከል ሰፊ የይዘትና የስልት ልዩነት እንዳለ ልናስተውል ይገባል ።

ሶሻሊስት ፕሮፓጋንዳ የነባራዊውን ዓለም ትክክለኛ ገጽታዎች ለሰፊው ሕዝብ በማሳወቅ ፤ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ መደባዊ ንቃቱ እንዲዳብር ፤ አሮጌውን ሥርዓት በመገርሰስ አዲስና እኩልነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ እንዲገነባ በማነቃቃት ላይ ያተኰረ ሲሆን የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ግን በተለያዩ የማዛባት ስልቶች አማካይነት በሰፊው ሕዝብ ንቃተኅሊና ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ፤ ሰፊው ሕዝብ ስለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ያለውን ዝንባሌና ስሜት በመሸርሸር ፀረ ሶሻሊስት አቋም እንዲይዝ በማድረግ ዓላማዎች ላይ ያተኮረ ነው ።

ከዚህ መደባዊ ዓላማውና ስልቱ አኳያ የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል ። ሀ/ በረቀቀ ስልት ለራስ ዓላማ የመገልገል (Manipulative)፣ ለ/ የማዛባት (Subversive) ፡ ሐ/ መረጃ የማሰራጨት (Informative) እና መ/ የማፍረስ (Distructive or Distortive) ተግባራት ናቸው ።[10]

በቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ሂደት ውስጥ እነዚህ ዓበይት ተግባራት እርስበርሳቸው የተያያዙና በመስተጋብራዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ሆኖም በዚህ የግንኙነት ሥርዓት ውስጥ ዋነኛውን ቦታ የያዘውና ዓቢይ ሚና የሚኖረው የሰፊውን ሕዝብ ንቃተኅሊና በረቀቀ ስልት ሆን ብሎ ለራስ ዓላማ የመገልገል ተግባር ነው ። ይህም ተግባር የገዢው (የቡርዧው) መደብ አንዳንድ አስተሳሰቦችን ቀስበቀስ በአእምሮ ውስጥ በማስረግ የሕዝቡን ሥነልቡናዊ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚገለገሉበት ፤ እውነታን አስመስሎ በማቅረብ ሰብአዊ ፋይዳዎችን ወደ ተፈለገው አቅጣጫ እንዲያመሩ የሚያስገድዱበት መሣሪያ ነው ።[11]

ከዚህ ጋር ቅርበት ያለው ሌላው የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ተግባር የሰፊውን ሕዝብ ንቃተኅሊና የማዛባት ነው ። ይህ ዓይነቱ የፕሮፓጋንዳ ተግባር እጅግ አድኃሪ ፤ የፋሺስት ቡድኖች የሚገለገሉበትና በጦርነት ወቅቶች ብቻ በጥቅም ላይ የሚውል የፕሮፓጋንዳ አንድ ተግባር መሆኑ በተለያዩ የቡርዧ ጽሁፎች ውስጥ ሰፍሯል ። ይሁንና ንቃተኅሊናን የማዛባት ተግባር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለና ዛሬም የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች የሚገለገሉበት ነው ።

ሌላው የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ተግባር መረጃ (ኢንፎርሜሽን) የማሰራጨት ነው ። ይህ ተግባር በበርካታ የቡርዧ ምሁራን ዘንድ እንደ ዋነኛ ተግባር በመታየቱ ቀዳሚ ሥፍራ ይሰጠዋል ። እንዲያውም እኛ የምናከናውነው ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን የመረጃ ስርጭት ነው በማለት ፕሮፓጋንዳ የተሰኘውን ጽንሰሐሳብ "መረጃ" በተሰኘው ጽንሰሐሳብ ለመተካት ይሞክራሉ ።[12] ይህ በቡርዧ ርዕዮተዓለም ውስጥ የሚታየው ዝንባሌ በፕሮፓጋንዳና በመረጃ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለማድበስበስ ፤ የቡርዧው የማዛባት ተግባር ፕሮፓጋንዳ ተብሎ እንዳይጠራና ከአፍራሽ ትርጉም ለመሸሽ የሚደረግ ጥረት መሆኑን ያስገነዝበናል ።

መረጃና ፕሮፓጋንዳ በማኅበረ ፖለቲካዊ መስክ በማይነጣጠል መልክ የተሳሰሩ ናቸው ። በዚህ መስክ ውስጥ አንድን መረጃ የመምረጡ ጥያቄ እራሱ በአንድ ወይም በሌላው መደብ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ነው ። በመሆኑም የቡርዧው መረጃ የማሰራጨት ተግባር የሕዝቡን ንቃተኅሊና ለራስ ዓላማ ከመገልገልና ከማዛባት ተግባራት ተነጥሎ መታየት የሚችል አይደለም።

ሌላው የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ተግባር የማፍረስ ተግባር ነው ። ቡርዧው በዚህ ተግባር አማካይነት ሰፊው ሕዝብ ስለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የጨበጣቸው አስተሳሰቦች እንዲናዱ ፤ ከሕዝቡ ኅሊና ውስጥ ታጥበው እንዲወጡ ጥረት ያደርጋል ። ሰዎች የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን አስተሳሰቦች እንዲጠሉ፣ ፀረ ሶሻሊስት አስተሳሰቦችን እንዲቀበሉ ፤ ቀስበቀስም ለካፒታሊስቱ ሥርዓት መጠናከር እንዲሰለፉ ለማድረግ ይጥራል ።

1.2. የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ከተለያዩ መስፈርቶች አኳያ በተለያዩ ዓይነቶች ይከፈላል ። የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ከሥርጭት ባሕርይ አንፃር አፍአዊ ፤ የሕትመትና እይታዊ ፕሮፓጋንዳ ፡ ከክንዋኔ ሂደቱ አኳያ ደግሞ ስትራተጂያዊና ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ፤ እንዲሁም ከፕሮፓጋንዳው ምንጭ ባህርይ አኳያም "ነጭ" ፡ "ጥቁር" እና "ግራጫ" ፕሮፓጋንዳ በመባል ይታወቃል ። ሌሎችም የፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች ቢኖሩም በዚህ ርዕስ ላይ የመነሻ ሐሳብ ለማግኘት ያህል ከላይ የተመለከቱት የፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች በቂ ስለሆኑ እነዚህኑ ጠቅለል አድርገን ለመቃኘት እንሞክር ።

1.2.1. ፕሮፓጋንዳ ከሥርጭት ባሕርዩ አንፃር

ሀ/ አፍአዊ ፕሮፓጋንዳ፡— ይህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ ከሁሉም በፊት በሰዎች አንደበት ማለትም ታዋቂ የቡርዧ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ምሁራን ፡ የሃይማኖት

መሪዎች ፣ ሃያሲያን ፣ ወዘተ. በሚያደር
ጓቸው ንግግሮች ፣ ሌክቸሮች ፣ ሲምፖ
ዚየሞች ወዘተ. መልክ የሚተላለፍ
የፕሮፓጋንዳ ዓይነት ነው ። አፍአዊ
ፕሮፓጋንዳ ከማዝናናት ተግባር ጋር
ተቀናጅቶ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እን
ዲተላለፍ ይደረጋል ። በሬዲዮ የሚተላ
ለፍ ፕሮፓጋንዳ ምንም እንኳ በደሀው
ኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ሥርጭቱ አነ
ስተኛ ቢሆንም ማይም የሆነውንና ያል
ሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚዳስስ
በመሆኑ ከሌላው የመገናኛ ብዙኃን
አኳያ ሲታይ ሰፊ የስርጭት አድማስ
አለው ። አቀራረቡ ቀላልና ግልፅ እንዲ
ሆን ታስቦ ከተዘጋጀ ሕዝቡን ለተፈለ
ገው ዓላማ ለማነሣሣት የሚያስችል
መሣሪያ በመሆኑ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ
በሚገባ ይጠቀምበታል ። መላውን
ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ ትተን በኢትዮ
ጵያ ላይ የተከፈተውን የሬዲዮ ፕሮፓጋ
ንዳ ጥቃት በምሳሌነት ብንመለከት
የፀረ አብዮትና የፀረ አንድነት ሀይሎች
ሰባት የሀገር ውስጥ እንዲሁም የውጭ
ቋንቋዎችን በመጠቀም በቀን ለ16
ሰዓት በሳምንት ደግሞ ለ120 ሰዓት
አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዳሉ ።
ቴሌቪዥንም እይታንና ድምጽን አቀና
ጅቶ የሚቀርብ በመሆኑ በተመልካች
ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እጅግ ከፍ
ተኛነቱ ታውቆ በስፋት ይሠራበታል ።
(በዚህ ረገድ የውጭ ኃይሎች በኢትዮ
ጵያ ላይ የሚያካሂዱት ጥቃት በቪዲዮና
በፊልም ብቻ የተወሰነው ።)

ለ/ የሕትመት ፕሮፓጋንዳ፡— ይህ የፕ
ሮፓጋንዳ ዓይነት በመጽሐፍ ፣ በመጽ
ሔት፣ በጋዜጦች፣ በፖስተሮች፣ በፎቶግ
ራፎች፣ በፖስት ካርዶችና በመሳሰሉት
እትሞች አማካይነት የሚሰራጭ ፕሮ
ፓጋንዳ ነው ። በእነዚህ ዘዴዎች የሚ
ሠራጭ ፕሮፓጋንዳ በማንኛውም ጊዜ
ስለሚነበብ ወይም ስለሚታይ መልዕ
ክቱ ወደ ሰዎች አዕምሮ ሊሸጋገር
የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው ። ከዚ
ህም በላይ በቀላሉ ከሰው ወደሰው
ሊተላለፍ ፣ የሚፈልገው ክፍል ተለ
ይቶ ወይም እንዳለ እትሙ በሰነድነት
ሊቀመጥ ይችላል ። እትሞች ወደ
ገጠሩም ጭምር ዘልቀው ሊገቡ
የሚችሉ የፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች
ናቸው ። በመሆኑም የቡርዧ የሕት
መት ፕሮፓጋንዳ በመላው ዓለም በስ
ፋት በመሠራጨት ላይ ይገኛል ።

ለምሳሌ ዩኔስኮ በ1980 (እ.ኤ.አ) በአወ
ጣው መረጃ መሠረት በዓለም ውስጥ
በአንድ ቀን ብቻ በ550 ሚሊዮን ቅጂ
ዎች የሚታተሙ 8,550 ጋዜጦች አሉ።
ከነዚህ ጋዜጦች ውስጥ አብዛኛዎቹ
የሚታተሙት በኢምፔሪያሊስት ድር
ጅቶች አማካይነት ነው ። በሌላ በኩል
ደግሞ በዓለም ውስጥ በዓመት 10
ሚሊዮን ያህል መጻሕፍት ይታተ
ማሉ። ከነዚህ መጻሕፍት ውስጥ 85%
ያህሉ በካፒታሊስት አገሮች የሚታተ
ሙና የሚሰራጩ ናቸው ።[13] ጋዜጦች
የአንድን ግለሰብ የዕለት ተዕለት ግን
ዛቤ በመቅረጽ ፤ መጻሕፍት ደግሞ
የሰዎችን ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት
በማነጽ በኩል የሚያበረክቱትን ድርሻ
ስናስብ በዚህ ፕሮፓጋንዳ ዓይነት ቡር
ዧው በሕዝቡ ላይ የቱን ያህል የጎላ
ተጽእኖ እንደሚያደርግ መገንዘብ እንች
ላለን ።

ሐ/ እይታዊ ፕሮፓጋንዳ፡— ይህ ዓይነቱ
ፕሮፓጋንዳ በተለያዩ መንገዶች ማለ
ትም በቴሌቪዥን ፣ በሲኒማ ፣ በቪዲዮ፣
በሥዕላዊ ምስሎች ፣ በሙዚቃዊ ትር
ኢት ፣ በኪነጥበባዊ ሥራዎች ወዘተ.
አማካይነት የሚቀርብና የሚሰራጭ
ነው ። የሰው ልጅ ስለአካባቢዎቹ
መረጃ የሚሰበስበው በተለያዩ የስ
ሜት ሕዋሳቶች አማካይነት ቢሆንም
40% ያህሉ መረጃ የሚሰበሰበው በማ
የት መሆኑ ታውቋል ።[14] ይህም
የእይታ ፕሮፓጋንዳ ከሌሎች የፕሮፓ
ጋንዳ ዓይነቶች ይልቅ በሰው ልጅ ላይ
ከፍተኛ ተጽዕኖ ማድረስ እንደሚችል
ያስገነዝበናል ። ከዚህም በላይ በእይታ
የሚተላለፍ ፕሮፓጋንዳ ከሌሎቹ የፕ
ሮፓጋንዳ ዓይነቶች ይልቅ ከፍተኛና
የተሻለ ውጤት ያስገኛል ። ለምሳሌ
ቴሌቪዥን ጥሩ የእይታ ፕሮፓጋንዳ
መገልገያ ነው ። ምስልና ድምጽን
አቀናጅቶ በማቅረብ ተመልካቹ የአን
ድን ድርጊት ሂደት እንዲያይና ስለሁኔ
ታው መስካሪ እንዲሆን ያስገድደዋል።
የአዝናኝነትም ባሕርይ ስላለው የመሰ
ልቸት ስሜትን አይፈጥርም ። አንዳ
ንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ዛሬ
በዓለም ላይ 800 ሚሊዮን ያህል መመ
ልከቻ ቴሌቪዥኖች ሲኖሩ ወደ 2
ቢሊዮን ሕዝብ ፕሮግራሙን ይከታተ
ላል ። ከእነዚህ ለሕዝብ ከሚተላለፉት
ፕሮግራሞች ውስጥ 95% ያህሉ በጥ
ቂት ካፒታሊስት አገሮች የሚዘጋጁና
የሚሰራጩ ናቸው ። በዓለም ከሚታ
ዩት ፊልሞችም ቢሆን 85%ያህሉ
የካፒታሊስቱ ዓለም ምርት ናቸው ።[15]

1.2.2. ፕሮፓጋንዳ ከክንዋኔ ሂደቱ አኳያ

የቡርዧውን ፕሮፓጋንዳ ከክንዋኔ
ሂደቱ አኳያ ስንመለከት ስትራቴጂያዊና
ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ተብሎ በሁለት ይከ
ፈላል ።

ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ
የፕሮፓጋንዳው አድራጊ ከቆመለት መደብ
ዓላማ አኳያ የኅብረተሰቡን ክፍሎች በጠላ
ትነት ፣ በወዳጅነትና በገለልተኝነት በመክ
ፈል የጥቃት ኢላማውን ፣ የማጥቂያ መንገ
ዶቹንና ስልቶቹን በማቀናጀት በሩቅና በቅ
ርብ ጊዜ ክንውኖች ከፋፍሎና አጣጥሞ
የሚያዘጋጀው የድርጊት ፕሮግራም ነው ።

ሀ/ ስትራቴጂያዊ ፕሮፓጋንዳ

ስትራቴጂያዊ ፕሮፓጋንዳ ሰፋ ያሉ የፕ
ሮፓጋንዳ ስልቶችን በመያዝ ረዘም ላለ ጊዜ
የሚከናወንንና ዘላቂውን የፖለቲካ ግብ
በማስፈጸም ላይ ያተኰረ የፕሮፓጋንዳ ዓይ
ነት ነው ። በጠላት ወገን ላይ የተሟላ ድል
መቀዳጀትን ፣ ለጠላት መገልገያ የሆኑ
አውታሮችን ማፈራረስንና ወዳጅ ማበራከ
ትን ዓላማ አድርጐ የሚከናወን ፕሮፓጋ
ንዳ ነው።

ለ/ ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ፡

ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ የፕሮፓጋንዳው
የስርጭት አድማስ ጠበብ ያለ ፣ ለአጭር
ጊዜ የሚከናወንና የወቅቱን አጣዳፊ ሁኔታ
ዎች በማገናዘብ በአጭር ጊዜ ግቦች ላይ
የሚያተኩር የፕሮፓጋንዳ ዓይነት ነው ።
ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ በየወቅቱ ከሚከሰቱ
ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር አብሮ ስለሚለ

ወጥ አንዳንድ ጊዜ ከስትራቴጂያዊ ግቦች ጋር የሚቃረን መስሎ ይታያል ። ሆኖም የቡርዧው የፕሮፓጋንዳ ጠበብቶች በስትራቴጂና በታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ መካከል ተገቢው መጣጣም እንዲኖር ከጊዜና ከቦታ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲገናዘብና ዘላቂውን ስትራቴጂ እንዲያገለግል ጠንካራ ጥረት ያደርጋሉ ። የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ለታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ቅድሚያ በመስጠት ለጊዜያዊ ድል ሲሉ ፀረ ሶሻሊዝም አቋማቸውን አይለውጡም ። በአኳያውም ሶሻሊዝምን ብቻ በመኮነን ተጨባጩ ሁኔታ በፈቀደላቸው ምቹ አጋጣሚዎች ከመጠቀም አይቆጠቡም ። ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ተነጣጥለው የሚታዩ ባይሆንም ሁለቱም የፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች የየራሳቸው ዝግጅት ፣ የአቀራረብ ስልትና የሙያ ሥልጠና የሚሹ በመሆናቸው በቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ዘንድ ተገቢው ትኩረት ይሰጣቸዋል ።

1.2.3. ፕሮፓጋንዳ ከምንጩ ባሕርይ አኳያ

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ዓይነት ከፕሮፓጋንዳው ምንጭ ባሕርይ አኳያ ሲታይ በሦስት ምድቦች ይከፈላል ። ይህ አከፋፈል በቡርዧ ምሁራን ዘንድ የተለመደና በስፋትም አገልግሎት ላይ የዋለ ነው ።

ሀ “ይፋ” (ነጭ) ፕሮፓጋንዳ

የፕሮፓጋንዳው ምንጭ በግልጽና በይፋ የተነገረ ብሎም በማን ላይ እንዳተኰረ በግልጽ የሚታወቅ የፕሮፓጋንዳ ዓይነት ነው ። ይህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ አብዛኛውን ጊዜ የሚታገሉለትን አቋም ወይም ፕሮግራም በይፋ ባሳወቀ አካል ማለትም በመንግሥት ወይም በግል ድርጅቶች የሚከናወን ፕሮፓጋንዳ ሲሆን በፕሮፓጋንዳው ሳቢያ ለሚፈጠሩ ማናቸውም ሁኔታዎች የሚያከናውነው አካል ኃላፊነቱን የሚወስድበት ነው ። “ለይፋ” ፕሮፓጋንዳ ("White" (Overt)) የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ፣ የእንግሊዝ ቢ.ቢ.ሲና ሌሎችም መንግሥታዊ የሆኑ የሬዲዮ ጣቢያዎች የሚያከናወኗቸው ተግባራት በምሳሌነት ሊወሰዱ ይችላሉ ።

ለ “ስውር” (ጥቁር) ፕሮፓጋንዳ

የፕሮፓጋንዳው ምንጭ ሳይታወቅ ወይም የተሸፋፈኑና የተለያዩ የሐሰት መረጃዎች የሚተላለፉበት የፕሮፓጋንዳ ዓይነት ነው ። ይህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ እንደ ይፋ ፕሮፓጋንዳ ከይፋዊና ሕጋዊ ተቋሞች ጋር ሳይሆን በአመዛኙ ከኢምፔሪያሊስት የስለላ ድርጅቶችና ከተለያዩ ሕቡዕ ድርጅቶች ጋር የተያያዘ ነው ። ይህ ፕሮፓጋንዳ በተለይም በጦርነት ወቅቶች ይበልጥ ተግባራዊ የሚሆንና በውሸትና በቅጥፈት መረጃዎች የሕዝብን ንቃተኅሊና ለማዛባት የሚጥር ነው ። “ለስውር ፕሮፓጋንዳ” ("black" (Covert)) የኢትዮጵያን አብዮት ለመዋጋት በምስጢር የተቋቋሙትን የሬዲዮ ጣቢያዎች ተግባር በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል ።

ሐ “የተለባበሰ” (“ግራጫ”) ፕሮፓጋንዳ

ይህ ፕሮፓጋንዳ የይፋንና የስውር ፕሮፓጋንዳን አንዳንድ ባሕርያት አቀናጅቶ የያዘና በሁለቱ መካከል ሊመደብ የሚችል የፕሮፓጋንዳ ዓይነት ነው ። ስለአንድ እውነታ ሰዎች የተሳሳተ ግምት እንዲኖራቸው ራሱን በመሸፋፈን የሚቀርብ ወይንም የተወሰኑ ትክክለኛ መረጃዎችን በመስጠት ሰዎች ከተሳሳተ መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ታስቦ የሚከናወን ፕሮፓጋንዳ ነው ። “የተለባበሰ ፕሮፓጋንዳ” ("Grey") አንዳንድ የዜና ድርጅቶች ፣ የሬዲዮ ጣቢያዎች ፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንደሚያደርጉት “ከሚታመን ምንጭ” “ስሙን ለመግለጽ ካልፈለገ ግለሰብ” ፣ “ከዲፕሎማቲክ ምንጮች” ወዘተ በሚል “በስውር ፕሮፓጋንዳ” ስልቶች በመጠቀም እንደ ይፋ ፕሮፓጋንዳ ይፋዊና ሕጋዊ መድረክ አግኝቶ እንዲቀርብ የሚደረግበት ዘዴ ነው ።

ከላይ አጠር ባለ መልክ ለመቃኘት የሞከርናቸው የፕሮፓጋንዳ ዓይነቶች (ይፋ፣ ስውርና የተለባበሰ ፕሮፓጋንዳ) እርስ በርሳቸው የተዛመዱ ፣ የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ አውታሮች በተለያዩ ስልቶች የሚገለገሉ በመሆናቸው በሙያው ከሠለጠኑ ሰዎች በቀር ድንበራቸውን ለይቶ ማወቅ ቀላል አይደለም ።

2. የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ስልቶችና የአቀራረብ ቴክኒኮች

2.1. የፕሮፓጋንዳ ስልቶች

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ስልቶች በተለያዩ የፕሮፓጋንዳ ሥርዓት አካላት ማለትም በፕሮፓጋንዳ ምንጭ (Source) ፣ በፕሮፓጋንዳው መልዕክት (Message) ፣ በፕሮፓጋንዳው ጊዜያት (Time) ፣ በፕሮፓጋንዳ ተደራጊ ወይም ተደራሲያን (Audience) ፣ እና በፕሮፓጋንዳ ምላሽ መረጃ (Feedback) ወዘተ. መካከል ያለውን ውስጣዊ ተዛምዶ በመጠበቅ ጥበብ ላይ የተመሠረተ ነው ።[18] የፕሮፓጋንዳውን ስልት ውስጣዊ ባሕርያት ለመገንዘብ ከላይ የተመለከቱትን የፕሮፓጋንዳ አካላት ባሕርይ ጠቅለል ባለ መልክ ለመቃኘት እንሞክር ።

ሀ/ የፕሮፓጋንዳ ምንጭ

የፕሮፓጋንዳ ምንጭ ሲባል የፕሮፓጋንዳውን ፖሊሲ የሚያወጡትን (የሚነድፉትን) ፣ ለስርጭት የሚሆኑ መረጃዎች የሚሰበስቡትን ፣ የፕሮፓጋንዳውን ሥራ የሚያካሂዱትን ፣ የመጨረሻውን ዝግጅት የሚፈቅዱትን ፣ የፕሮፓጋንዳውን መልዕክት በስማቸው የሚያስተላልፉትን ግለሰቦች ወይም ቡድን የሚያካትት ሰፊ ጽንሰሐሳብ ነው ፡ እንዲህ ዓይነት ዝርዝር ሁኔታዎችን በማደራጀት በፕሮፓጋንዳ ምንጭነት የሚታወቁት መንግሥታት ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ፣ የመገናኛ ብዙኃን ባለቤት የሆኑ የግል ድርጅቶች ናቸው ።

አንድ የፕሮፓጋንዳ ምንጭ ተልዕኮው ውጤት እንዲያገኝ ታዋቂ መሆን ፣ ተቀባይነት ማግኘትና ተአማኒነትን ማትረፍ መቻል ይኖርበታል ። የፕሮፓጋንዳው ምንጭ እነዚህን ባሕርያት እየተላበሰ በመጣ መጠን ፕሮፓጋንዳውም የዚያኑ ያህል ውጤታማ እየሆነ ይሄዳል ። በጥጥንትና በስፋት የራስን አስተሳሰብ በሕዝቦች ንቃተሕሊና ውስጥ ለማስረግ ያስችላል ። ይህ ደግሞ ፕሮፓጋንዲስቶቹ በሚኖራቸው የሙያ ሥልጠና ፣ የፖለቲካ ብቃትና የተደራሲውን የባህል ደረጃ ፣ የፍላጐት አድማስና የአስተሳሰብ ባሕርይ ለማገናዘብ ባላቸው ብቃት ላይ የሚመሠረት መሆኑ ይታመናል ። ምንጩ መረጃዎችን አሟልቶ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ሲያሰራጭ

የበለጠ ተአማኒነት እንዲኖረው መስናዶና ጥንቃቄ ይደረጋል ። የሚተላለፈው ፕሮፓጋንዳ ምንጭ የግለሰብን ስም ወይም የኃላፊነት ቦታ የሚያመለክት ከሆነ "ከሚታመን ምንጭ" "የተሟላ መረጃ ያለው" "ለመንግሥት አመራር ቅርብ የሆነ" ወዘተ. በሚሉ ሐረጎች እንዲታጀብ ይደረጋል ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ጠቃሚ የሆነ ነገር ሁሉ እውነት ነው በማለት እውነትን ከጠቃሚነት ጋር አንድ አድርጐ በሚመለከተው በገቢራዊነት (Pragmatism) ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለተአማኒነት የሚኖረው ግንዛቤ የተዛባ ነው ።[18] ለቡርዧ ምሁራን ተአማኒነት (Credibility) ማለት የሚነገረውን ነገር ተደራሲው አምኖ መቀበሉን እንጂ የሚነገርለት ነገር የግድ እውነት መሆኑን አያመለክትም ። ጭንቀታቸው ተደራሲው የሚነገረውን ነገር አምኖ መቀበሉ ላይ ነው ። በመሆኑም በቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ውስጥ የተአማኒነት ጥያቄ በተደራሲያኑ ዘንድ አመኔታ የማግኘት ሁኔታ እንጂ በፕሮፓጋንዳው መልዕክት ይዘት የሚለካና የሚወሰን አይሆንም ። ከዚህም በመነሣት ከእውነት ይልቅ ለማሳመን በሚያስችሉ ረቂቅ ስልቶችና የምርምር ውጤቶች ወደመጠቀሙ ያተኩራሉ ።

ለ/ የፕሮፓጋንዳ መልዕክት

የሚተላለፈው መልዕክት በፕሮፓጋንዳው ሥርዓት ውስጥ አንድ ዓቢይ ክፍል ነው ። የፕሮፓጋንዳው ውጤት በሚተላለፈው መልዕክትና በአቀራረቡ ባሕርይ ይወሰናል ። የዘመኑ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ መልዕክት ይዘት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፋይናንስ ምስፍና ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ነው ። የዚህ ፖሊሲ ዓላማና ግብ ደግሞ እየከረረ የመጣውን የመደብ ትግል በማለዘብ የናጠጠ ትርፍ ማካበትና የብዝበዛ ዕድሜን ማራዘም ነው።

ዛሬ በዓለምአቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኃይል አሰላለፍ ምክንያት የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ መልዕክት ከቀድሞው የተለየ አዲስ ባሕርይ ይዞ ይታያል ። ቀደም ባሉት ወቅቶች የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ መልዕክት የካፒታሊዝምን ሥርዓት ትክክለኝነት በመናገር ፤ መርሆዎቹንም በማስተማርና ሕዝቡን በዚህ አስተሳሰብ ዙሪያ በማሰባሰብ ለሥርዓቱ እንዲታገሉ በማነሣሣት ላይ ያተኮረ ነበር ። ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ተለውጦ መልዕክቱ ሶሻሊዝምን በማጥላላት ላይ እንዲመሠረት ተደርጓል ፤ ስለሆነም ፀረ ሶሻሊስት መልዕክት ማሰራጨት የዘመኑ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ አቋም ሆኗል ።[19]

በቡርዧ ፕሮፓጋንዳ የሚተላለፈው መልዕክት ንድፈሐሳባዊና ሥነ ልቡናዊ አቅጣጫዎችን የተከተለ ነው ። የመልዕክቱ ንድፈሐሳባዊ አቅጣጫ ከማኅበራዊ ንቃተኅሊና የተለያዩ መልኮች (ከፖለቲካ ፤ ከሕግ ፤ ከሞራል ፤ ከሃይማኖት ፤ ከኪነጥበብ ወዘተ) አኳያ ሶሻሊዝምንና አስተሳሰቦቹን ማጥላላት ፤ ሕዝባዊ ድጋፍ ለማሳጣት ሙከራ ማድረግ ሲሆን የፕሮፓጋንዳውን ስትራቴጂያዊ መሥመር የሚያንፀባርቅና የሚያገለግል ነው ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ መልዕክት ሌላው አቅጣጫ በማኅበራዊ ሥነልቡና ዘርፍ ላይ ተመሥርቶ የሚከናወነው ነው ። ይህ የፕሮፓጋንዳ መልዕክት ሥነ ልቡናዊ ስልቶች በመጠቀም ዛሬ ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ ስላሚገኙ ወይም ይህን የዕድገት ፈለግ ስለተከተሉ አገሮች የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ፤ በማዛባትና በማጥላላት ሰዎችን በሥርዓቱ ላይ የማነሣሣት ስልት የሚከተል ነው ። ይህ አቅጣጫ በአመዛኙ የፕሮፓጋንዳውን ታክቲካዊ መሥመር የሚያንፀባርቅና የሚያገለግል ነው ። እንዲያውም በዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ በውሸት ፤ በማስመሰል ፤ በጥቅሉ በሥነ ልቡናዊ ስልቶች ላይ የተመሠረተ የፕሮፓጋንዳ መልዕክት ማስተላለፍ በቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ውስጥ ጐልቶ ይታያል ።

የቡርዧ የፕሮፓጋንዳ መልዕክት ይዘት ቡርዧው በሚያራምደው ርዕዮተዓለምና ፖለቲካ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ዘወትር ከዚሁ ጋር እንዲጣጣምና እንዲያገለግል ይደረጋል ። ከዚህም በላይ ከፕሮፓጋንዳው ምንጭ ፤ ከጊዜ ጥያቄዎች ፤ ከተደራሲው ፤ እንዲሁም ከማሰራጫ አውታሮች ልዩ ባሕርይ ጋር የተገናዘበ እንዲሆን የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ጥረት ያደርጋሉ ። እንዲያውም የፕሮፓጋንዳው መልዕክት ተደራሲውን ለተፈለገው ክንውንና አቅጣጫ እንዲያነሣሣ ሆኖ መዘጋጀት ስለሚኖርበት የፕሮፓጋንዳ ሁኔታዎችን መመርመርንና ማገናዘብን የሚጠይቅ ጥበብ ነው ። በመሆኑም የፕሮፓጋንዳ ሥራችን የት እንደደረሰ መለካት ያለበት በዚህ የፕሮፓጋንዳ ጥበብ መሆን ይኖርበታል በማለት የቡርዧ ምሁራን ለዚህ ሙያ ከፍተኛ ግምት ይሰጣሉ ።

ሐ/ የፕሮፓጋንዳ ጊዜ

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ እንደማናቸውም ሁኔታዎች ፤ ክስተቶችና ሂደቶች ከጊዜና ከቦታ ውጭ የሚታይ አይደለም ። አንድ ፕሮፓጋንዳ የተወሰነ ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ግቦች እንዳሉት ይታወቃል ። እነዚህ ግቦች ደግሞ በክንዋኔ ጊዜያት የተከፋፈሉና በጊዜ የሚለኩ ናቸው ። እነዚህ የፕሮፓጋንዳ ተግባራት ከመቼ እስከመቼ ይከናወናሉ? በየትኛው ቀንና ሰዓትስ ይሰራጫሉ? ፕሮግራሙስ ለምን ያህል ሰዓት ይካሄዳል ? የፕሮፓጋንዳው ግቦችስ መቼ ይቀየራሉ ? ከጠላት ፕሮፓጋንዳ አኳያ ምን የጊዜ መስተካከል ሊደረግ ይገባል ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች በፕሮፓጋንዳ ተግባራት ውስጥ ምላሽ የሚሹ ናቸው ። የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች የጊዜን ጥያቄ በሚመለከት የተለያዩ ጥናቶችን በስፋት ያካሂዳሉ ። ከተጨባጭ ለውጦች ጋርም የጊዜ ለውጥ ያደርጋሉ ።

የፕሮፓጋንዳ ተግባራት ቅደም ተከተልና የጊዜ ጥያቄዎች ከፕሮፓጋንዳው ምንጭ ፤ ከፕሮፓጋንዳው መልዕክት ፤ ከፕሮፓጋንዳው ተደራጊ ፤ ከፕሮፓጋንዳው ግቦችና ከማሰራጫ አውታሮች ባሕርይ ጋር ውስጣዊ ተዛምዶአቸው እንዲጠበቅ ብርቱ ጥረት ይደረጋል ። የቡርዧ የፕሮፓጋንዳ ምሁራን የቅደም ተከተልንና የጊዜን ጥያቄዎች በስፋትና በጥልቀት በመተንተን ረገድ የተካበተ ልምድ አላቸው ። በቅደም ተከተልና በጊዜ በትክክል መጠቀም መቻል ለፕሮፓጋንዳ ሥራ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ሁሉ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ያላስገባ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ውጤት የሌለው ከንቱ ልፋት እንደሚሆን አጥብቀው ያምናሉ ።

መ/ የፕሮፓጋንዳ ተደራጊ (ተደራሲ)

የፕሮፓጋንዳው አድራጊ ዓላማውን እንዲቀበሉትና ለተግባራዊ ክንዋኔም አብረው እንዲሰለፉ ለማድረግ በረቀቀ ጥበብ

የተቀመሩ መልዕክቶቹን የሚያስተላልፍላቸው ማኅበራዊ መደቦች ፣ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፣ ቡድኖችና ግለሰቦች የፕሮፓጋንዳ ተደራጊ (object) በሌላ አቀራረብ ተደራሲያን ይባላሉ ።

ፕሮፓጋንዳ የተሳካ ውጤት እንዲኖረው የፕሮፓጋንዳውን ተደራጊ (ተደራሲ) በጥልቀትና ከሁሉም ጐኖች መርምሮ መረዳት እንደሚያስፈልግ የቡርዧ ምሁራን አጥብቀው ይናገራሉ ። የፕሮፓጋንዳ ውጤታማነት የሚወሰነው በፖለቲካዊ ይዘቱ ፡ (በመልዕክቱ) በምንጩ ተአማኒነት ፡ በጊዜ ምርጫው ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ አወቃቀር ፣ የፕሮፓጋንዳው ዒላማ የሆነውን የተለየ ኅብረተሰብ ክፍል ባሕርይ ፡ ልማዱን ፣ ባህሉን በአጠቃላይም ማኅበራዊ አካባቢውን ተንትኖ ማወቁና ከዚሁ ጋር ማገናዘብ በመቻሉ ጭምር ነው። በመሆኑም ፕሮፓጋንዳው ከመከናወኑ በፊት የምናሰራጨው የኢንፎርሜሽን (መረጃ) ሞገድ በየትኛው ኅብረተሰብ ክፍል ላይ ያተኰረ ነው ? ፡ የመረጥነው የፕሮፓጋንዳ ተደራጊ (ተደራሲ) ለምናሰራጨው ፕሮፓጋንዳ የቱን ያህል የተዘጋጀ ነው? ዝግጁ ነው ተብሎ ከታመነበትስ የምናሰራጨው ፕሮፓጋንዳ መልዕክት በምን ላይ የተመሠረተ ነው? በሥነልቡና ፡ በፖለቲካ ፣ በማኅበራዊ ጉዳዮች ፡ በኢኮኖሚ ወይስ በብሔራዊ ስሜት ላይ ነው ? ፕሮፓጋንዳችን የተለያዩ መስኮችን በማቀናጀት የሚከናወን ከሆነ ከመካከላቸው የትኛው ዓቢዩን ሚና መጫወት ይኖርበታል ? የተመረጠውን ፕሮፓጋንዳ ለማካሄድ የሚያስችለን የውስጣዊ ኃይሎች አሰላለፍ ምን ይመስላል ? ተሳትፎአቸውስ በምን መንገድ ሊገለጽ ይችላል ? በጠላትነት ፣ በደጋፊነት ወይስ በገለልተኝነት ? የፕሮፓጋንዳ ተደራሲውን በመጠንና በዓይነት መስፈርቶች እንዴት ልንመዝነው እንችላለን ?፡ ከኅብረተሰቡ ውስጥ ምን ያህሉ ነው በዚህ ክፍል የታቀፈው? አባላቱስ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ምን ቦታ የያዙ ናቸው ? ከመንግሥትና ከፓርቲ ጋርስ ምን ግንኙነት አላቸው ? በአመራሩና በፈጻሚው ክፍልስ መካከል ምን ልዩነቶች ይታያሉ ? ወዘተ. የሚሉና የመሳሰሉ አያሌ ጥያቄዎችን በማንሣት የተደራሲውን አጠቃላይ ሁኔታ ይተነትናሉ ። ከዚህም ትንተና በመነሣት የሚደርሱባቸው ማጠቃለያ ሐሳቦች ከፕሮፓጋንዳ ሌሎች ሁኔታዎች ማለትም ከምንጩ ፣ ከጊዜ ጥያቄዎች ፣ ከመልዕክቱ ይዘትና ከማሰራጫ አውታሮቹ ጋር በማጣጣም ፕሮፓጋንዳቸውን ያከናውናሉ ።

ሠ/ ምላሽ መረጃ

ምላሽ መረጃ (feedback) የሚባለው አንድ ፕሮፓጋንዳ ከተሰራጨ በኋላ በተደራሲው ላይ ያስከተለውን ውጤት በጐና መጥፎ ጐኖቹን ለመገምገም የሚያስችሉ የመረጃዎች ስብስብ ነው ። የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች በደብዳቤዎች ፣ በቴሌፎን መልዕክቶች ፣ በውይይቶች ከሚሰበሰቡት መረጃ ሌላ በሕዝብ ውስጥ የተለያዩ የሶሲዮሎጂ ጥናቶችን ያደርጋሉ ። በየአገሩ በተመሠረቱት ኅቡዕ ድርጅቶችና በስለላ ተቋሞቻቸው አማካኝነት ሰፊ ጥናት በማድረግ መረጃ ይሰበስባሉ ። የሚያሰባስቡት መረጃ ተተንትኖ የተሰራጨው ፕሮፓጋንዳ ግቡን እንዳልመታ ወይንም የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ እንዳላስቻለ ሲታወቅ የፕሮፓጋንዳው አድራጊ, የፕሮፓጋንዳው ቅርጽ ፣ ስልት ፣ የክንዋኔ ቅደም ተከተልና ፣ የመልዕክቱ ይዘት እንዲለወጥ ፣ የተፈጸሙ ድክመቶች ወይም የተከሰቱ ስህተቶች እንዲታረሙ ያደርጋል ። ያለምላሽ መረጃ የፕሮፓጋንዳን ሥራ ማካሄድ ዓላማን አለማወቅና ከንቱ ጥረት በመሆኑ ቡርዧው ዘወትር በፕሮፓጋንዳ ተደራሲው ዘንድ የሚታየው ለውጥ ምንድነው ? የጠላት ወገን የአጸፋ ፕሮፓጋንዳ ባሕርያት ፣ ስልቶችና የአትኩሮት መስኮች ምንድናቸው ? በሕዝቡ ዘንድ የጠላት ወይስ የወገን ፕሮፓጋንዳ ነው የበላይነቱን ይዞ የሚገኘው ? ለዚህስ ምክንያት የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው ? የጠላት ወገንን ለማዳከምና የወዳጅ ወገንን ለማጠናከር ፣ ካልሆነም በገለልተኝነት ለማቆየት ምን መደረግ ይኖርበታል ? የወደፊቱ የፕሮፓጋንዳ ሥራችን ከአለፉት ክንውኖች ውስጥ ምን ማረምና የቱን ማጠናከር ይኖርበታል ? በማለት የፕሮፓጋንዳውን የወደፊት ሂደት ለማመልከት የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል ፣ ወደ ተግባር መመሪያነትም ይለውጣቸዋል ። ለዚህ ደግሞ በሙያው የተካኑ ምሁራንና ተቋሞች አሉት ።

በአጠቃላይ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ስልት እነዚህንና ሌሎችም በዚህ ጽሑፍ ያልተመለከትናቸውን የፕሮፓጋንዳ ክፍሎች ተናጠላዊ ባሕርይ በመተንተንና ውስጣዊ ተዛምዶአቸውን በመመርመር ተመርጦ በተግባር የሚተረጐም በመሆኑ የአያሌ ሁኔታዎች ትንጅታዊ ውጤት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል ።

2.2. የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ የአቀራረብ ቴክኒኮች

የቡርዧው ፕሮፓጋንዲስቶች ሰፊ ጥናትና ምርምር ያልተደረገበት የፕሮፓጋንዳ አቀራረብ ቴክኒክ እምብዛም ውጤት ሊያስገኙ አለማስቻሉን በሚገባ የሚገነዘቡት ነው ። በመሆኑም በአቀራረብ ፣ በቃላት አመራረጥና በቅላጼ እንኳ ሳይቀር ከፍተኛ ጥንቃቄና ዝግጅት ያደርጋሉ ። የቡርዧውን የፕሮፓጋንዳ የአቀራረብ ቴክኒኮች አጠቃለን ባናወሳም የቅድሚያ መረጃ ማሰራጨትንና የሁለት ወገን መረጃ ማቅረብን በተለይም የተዛባ መረጃ ማሰራጨትን በምሳሌነት አንስተን እንመልከት ።

2.2.1. የቅድሚያ መረጃ ማሰራጨት

የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ዕድገት በዓለም የመገናኛ ብዙኃን ላይ የመጠንና የዓይነት ለውጥ አስከትሏል ። ዛሬ ዓለም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በመገናኛ ብዙኃን መረቦች ተተብትባለች ። በአገርም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ በጣም የተቀላጠፈና የተፋጠነ ሆኗል ። በእኳየውም መረጃ በዘመኑ የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚይዘው ቦታና የሚያበረክተው ድርሻ በእጅጉ አድጎ ይታያል ።

በዚህ ዓለምአቀፍ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ የካፒታሊስት ሞኖፖሎች የኢኮኖሚ የበላይነት በመያዛቸው በዓለም የተዛባ የመረጃ ስርጭት ሥርዓት ሰፍኖ ይገ

ኛል ። ዛሬ ያለው ዓለምአቀፍ የመረጃ ሥርዓት ለምዕራቡ ሞኖፖሊስቶች እንደ አንድ ኢንዱስትሪና የፋይናንስ ተቋም ብቻ ሳይሆን በአገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡበት ፣ የሕዝቦችን የዕድገት ምርጫ የሚቃወሙበትና የኅሊና ጥቃት የሚሰነዝሩበት የፖለቲካ መሣሪያም በመሆን ያገለግላቸዋል። በዚህ የተዛባ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ በመረጃ ሥርጭት ቀድሞ መገኘት የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ መሠረታዊ መርህ ነው ።

የቅድሚያ መረጃ በአንድ በኩል የዜና ባሕርይ በመያዝ እስከአሁን በይፋ ለሕዝብ ያልቀረቡ ትኩስ ጉዳዮችን ወደ ሰዎች ጆሮ የሚያደርስ በመሆኑ ፈጣን የሥርጭት ኃይል ያለውና በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ ለመቆየት የሚችል ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የጠላት ወገን በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በቅድሚያ የተነገረበትን የተዛባ መረጃ በማስተባበል ብሎም የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ በማድረግ ላይ እንዲወሰን ስለሚያስገድድ ፕሮፓጋንዳ አድራጊው የአጥቂነት አቋም ይዞ እንዲቆይ ያደርጋል ።

እንደሚታወቀው የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ ሥራ ደግሞ ሐሰት የሆነውን መረጃ እውነት ከሆነው መለየትን ፣ ሐሰት የሆነውን ማጋለጥን ፣ የጠላት ፕሮፓጋንዳ የዳሰሰውን ሰፊ አካባቢ ማጽዳትን የሚጠይቅ በመሆኑ በባሕርይው አስቸጋሪና ውስብስብ ነው። ስለሆነም የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ የአንድን አገር የልማት ዕቅድ፣ የፖለቲካ አቋም፣ የግንባታ ሥራ ወይም መሰል ተግባራትን አስመልክቶ በተደራሲያኑ ዘንድ የተዛቡና የተውገረገሩ መረጃዎችን ቀድሞ ማሰራጨት እንደአንድ የፕሮፓጋንዳ ዘዴ በማድረግ በስፋት ይገለገልበታል ።

2.2.2. የሁለት ወገን መረጃ ማቅረብ

የሁለት ወገን መረጃ ማቅረብ የሚባለው በአንድ የፕሮፓጋንዳ ጉዳይ ላይ የደጋፊዎችና የተቃዋሚዎች ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የገለልተኞች አስተያየት በአንድ መልዕክት ተቀናጅቶ ለተደራሲያኑ የሚቀርብበት ዘዴ ነው ። የሁለት ወገን መረጃ በዜና ፣ በጥያቄና በመልስ ፣ በውይይትና በመሳሰሉ መንገዶች በመገናኛ ብዙሀን ሊቀርብ ይችላል ።

በዓለም ላይ የካፒታሊዝም የበላይነት ሰፍኖ በነበረባቸው ወቅቶች ፣ የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ የአንድ ወገን መረጃ ማቅረብን በስፋት ይገለገልበት ነበር ። ዛሬ በተከሰተው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ሳቢያ በቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ተደራሲያን ዘንድ ውስጣዊ የመዋቅር ለውጥ ተከስቷል ። አያሌ አገሮች የሶሻሊዝምን ፈለግ በመከተላቸው ከዚያ መድረክ አባልነት ወጥተዋል ። ሌሎችም በርካታ አገሮች በኢምፔሪያሊዝም የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ ላይ እምነታ እያጡ መጥተዋል ። በመሆኑም የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ተአማኒነትን ለማትረፍ እንደ ቀድሞዎቹ ወቅቶች የአንድ ወገን መረጃ ከማቅረብ ይልቅ የሁለት ወገን መረጃ ማቅረብን የተሻለና ለዘመኑ ሁኔታ የሚመጥን የአቀራረብ ዘዴ አድርጎ መርጦታል ።

የሁለት ወገን መረጃ የደጋፊዎችን የተቃዋሚዎችንና የገለልተኞችን አስተሳሰብ በማቀናጀት የሚቀርብ በመሆኑ በተደራሲያኑ ዘንድ ተአማኒነትንና ተደማጭነትን

ሊያተርፍ ይችል ይሆናል ። ሆኖም በዚህ መልክ የሚቀርብ ፕሮፓጋንዳ በተደራሲያኑ ላይ ምን ዓይነት የአስተሳሰብ ለውጥና ስሜት ማሳደር እንዳለበት በቅድሚያ በጥንቃቄ የሚዘጋጅ በመሆኑ የዘመኑ ፕሮፓጋንዳ ስውር የማታለያ ስልት በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ በሬዲዮ ውይይት አማካይነት የአንድን አገር አብዮት ለማጥላላት ሲዘጋጅ በተደራሲያኑ ላይ የተፈለገውን የኅሊና ጥቃት ለማስከተል እንዲቻል በውይይቱ ላይ የሚሳተፍ እያንዳንዱ ግለሰብ በቅድሚያ የተወሰነለትን ሚና እንዲጫወት ያዘጋጃል ። የተቃዋሚው ወገን በቁጥር እንዲበራከት ፣ የሚቀርቡት አስተሳሰቦችም የተደራሲውን ሥነልቡናዊ ሕይወት እንዲፈታተኑ ለመቀበል የቀለሉና በአብዮቱ ወገን ላይ የአጥቂነት አቋም የያዘ እንዲሆን ይሞከራል ። አብዮቱን በመደገፍ የቆመው ክፍል ደግሞ በተደራሲያኑ ዘንድ ደካማ መስሎ እንዲታይ በአጋጣሚ ጠንካራ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ከፕሮግራሙ መሪ በሚሰነዘሩ አስተያየቶች አማካይነት ጠንካራነቱ እንዳይታይ ይደረጋል ። ሌላው ተሳታፊ ደግሞ የአብዮቱን መሠረታዊ ዓላማ በመደገፍ ሽፋን አመራሩን የሚያጥላሉ ሐሳቦችን በመሰንዘር በገለልተኝነት ካባ እንዲሸፈን በማድረግ ሆን ብሎ በሕዝቡ ላይ ሥነልቡናዊ ፣ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ አሻጥር ይፈፅማል ።

2.2.3. የተዛባ መረጃ ማሰራጨት

የተዛባ መረጃ ማሰራጨት (Disinformation) ማለት ስለ እውነታ የተዛቡ ፣ የተውገረገሩ ወይም ጨርሶ ውሸት የሆኑ አስተሳሰቦችን በሰዎች አዕምሮ ውስጥ በማስረግ ሆን ብሎ ለማታለል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ወይም ትርጓሜ ነው ።[20] ማለትም ስለተፈጸመ ድርጊት ሂደትና ክስተት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ወይም እስከነአካቴው ስላልተፈፀመ ነገር “በራስ ፈጥሮ” እና “በሐሰት መረጃ ደግፎ” የተሳሳተ መልዕክት ማሰራጨት ማለት ነው ።[21]

የተዛባ መረጃ ማሰራጨት ከዱሮ ጊዜ ጀምሮ ገገርው መደብ የአገሩን ሠፊ ሠራተኛ ሕዝብ ለመበዝበዝና ለመጨቆን ሲገለገልበት የቆየ ጥንታዊ ቴክኒክ ነው ። ዛሬም ኢምፔሪያሊስት ቡርዧው በያንዳንዱ አጋጣሚ ካፒታሊዝምን የሚያሞካሽበትና ሶሻሊዝምን የሚያጥላላበት ፣ የማሌን ርዕዮተዓለም የሚቃናቀንበትና የቡርዧውን ርዕዮተዓለምና ሞራል የሚያጠናክርበት ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል ። የተዛባ መረጃ ማሰራጨት በተለያዩ መንገዶች ማለትም ፋይዳ በማሳጣት ፣ የሐሰት ሰነዶችን በማሰራጨት ፣ አጋኖ በማቅረብ ፣ ትኩረት በማስለወጥ ፣ ነገሮችን ደጋግሞ በማቅረብ ፣ ያልተረጋገጡ ወሬዎችን በማዛመት ፣ ነገሮችን በዝምታ በማለፍና በመሳሰሉ በርካታ መንገዶች በተግባር የሚተረጐም በመሆኑ የተወሳሰበ ባህርይ አለው ።

ሀ/ ፋይዳ ማሳጣት

በቡርዧው የፕሮፓጋንዳ ቴክኒክ ሥርዓት ውስጥ ፋይዳ ማሳጣት ማለት አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ፣ መንግሥታዊ አካል ፣ ሕዝባዊ ድርጅት ፣ የፖለቲካ ዘመቻ ወይም የአገር መሪዎችን ፣ የሳይንስ ተመራማሪዎ

ችን ፣ ጸሐፊዎችንና መሰል ታዋቂ ግለሰቦችን ወይም ንድፈሐሳቦችንና አመለካከቶችን አንኳሶ ፣ አቃሎና አጥላልቶ ማቅረብ ማለት ነው ።[22] የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ጠበብት ፋይዳ ለማሳጣት ስለፈለጉት ጉዳይ በቅድሚያ በተለያዩ መንገዶች መረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋሉ ። ከዚያም የተገኙትን ድክመቶች ፣ ችግሮችና ስህተቶች ለይተው በማውጣት አጋንነው በማቅረብ ወይም ጨርሶውኑ ውሸት የሆኑ ነገሮችን ከራሳቸው አመንጭተውና ሊያጥላሉት ከፈለጉት ጉዳይ ጋር በረቀቀ ጥበብ በማያያዝ የተከናወነውን ድርጊትና ክስተት ብቻ ሳይሆን አገርን ፣ መሪዎችንና የተከተሉትን የልማትና የፖለቲካ አቅጣጫዎች አንኳሰውና ፋይዳ አሳጥተው ያቀርባሉ ። ሕዝቡም በተቃዋሚነት እንዲሰለፍ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ያካሂዳሉ ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ካፒታሊዝም "ዲሞክራሲያዊ ተሀድሶ" እያደረገ በመሄድ ላይ በመሆኑ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም "ጊዜው ያለፈበት" ንድፈሐሳብ ሆኗል በማለት በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈሐሳብ ላይ የማጥላላት ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ያካሂዳሉ ። ይህንንም አስተሳሰባቸውን ለማጠናከርና የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ቅራኔዎች ለመሸፋፈን አያሌ ንድፈሐሳቦች አቀንቅነው በድምፅና በጽሑፍ መልክ አሰራጭተዋል ። "የኮንቨርጀንስ" ንድፈሐሳብ ፣ "የኢንዱስትሪያላዊ" እና "የድህረ ኢንዱስትሪያላዊ" ኅብረተሰብ ንድፈሐሳቦች ሶሻሊዝምና ካፒታሊዝም ወደአንድ ግብና ኅብረተሰብ የሚያደርሱ የተለያዩ ጎዳናዎች ናቸው በማለት የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንሳዊ ንድፈሐሳብ ፋይዳ ለማሳጣት ይጥራሉ። በሀገራችን የሚካሄደውን የሠፈራ ፕሮግራም ፣ መንደር ምሥረታን ድርቅ የመቋቋምን ጥረትና የመሳሰሉ ዓበይት ክንውኖችን ፋይዳ ለማሳጣት የተደረገው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለዚህ ዓይነቱ ቴክኒክ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ።

ለ/ የሐሰት ሰነዶች ማሰራጨት

የቡርዧው ፕሮፓጋንዲስቶች የሕዝብን ንቃተኅሊና ለማዛባት ከራሳቸው ፈጥረው በማዘጋጀት ወይም በተለያዩ ስልቶች አማካይነት ጠላት ከሚባለው ወገን የተገኙትን መረጃዎች ከውሸት ጋር በማዳቀል የተለያዩ የሐሰት ሰነዶችን ፣ አኃዛዊ መረጃዎችንና ጽሑፎችን ማዘጋጀትና ለተደራሲያን ማሠራጨት አንዱ ዘዴአቸው ነው ።

የሐሰት ሰነዶቹ ከሀገር ከድተው በሚወጡ ግለሰቦች እንደበት ለተደራሲያኑ እንዲቀርቡ ወይንም በበራሪ ወረቀቶች መልክ ተዘጋጅተው እንዲበተኑ ፣ በደብዳቤ መልክም ተጽፈው ለግለሰቦችና ለድርጅቶች እንዲላኩ ወይም ከሀገር ውስጥ ከግለሰቦች የደረሱ መልዕክቶች ተብለው በመገናኛ ብዙኃን እንዲነበቡ ይደረጋሉ ።

በተለይም ከሀገር በከዱ ግለሰቦች ወይም በስለላ ድርጅቶች አማካይነት አንዳንድ መረጃዎች የሚገኙ ከሆነ ለፕሮፓጋንዳ ቸው በሚያመች መንገድ ቆራርጠው ከውሸት መረጃዎች ጋር አጣጥመው ለተደራሲያኑ ያቀርባሉ ። ይህም በረቀቀ ጥበብ የተዳቀለ መረጃ በተደራሲያኑ ዘንድ ተቀባይነትንና ተአማኒነትን እንዲያገኝ ልዩ ጥንቃቄዎች ይደረጋሉ ። ለዚህም ተደራሲያኑ የሚሰራጭላቸውን መረጃ ትክክለኛነት ለመመርመር ያላቸውን ፍላጎትና ችሎታ ፣ በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል ያጋጠሙ ሁኔታዎች መኖርና አለመኖር፣ ለተደራሲያኑ ለመበተን የተዘጋጀው መረጃ ሌላው ወገን ለሚያከናውነው የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ አመቺ መሆኑና አለመሆኑ ወዘተ. በጥሞና ይጠናል ። በተለይም ዛሬ የሰው ልጅ የተለያዩ ምስሎችንና ጽሁፎችን አገናኝቶ የሀሰት ሰነዶችን ለማዘጋጀትና በፎቶግራፍና በፊልም ዝግጅት ጥበብ የተፈለገውን ነገር መሥራት መቻሉ ለቡርዧው ፕሮፓጋንዳ መሠሪ ተግባር በእጅጉ በጅቷል ።

ሐ አጋኖ ማቅረብ

አጋኖ ማቅረብ ማለት አንድን ድርጊት፣ ሂደት ወይም ክስተት እጅግ አግዝፎ ማቅረብ ማለት ነው ። በዚህ መልክ ተጋንነው በቀረቡ ነገሮች ምክንያት በሰዎች ዘንድ የሚፈጠሩ የተለያዩ ስሜቶችንና ዝንባሌዎችን ሆን ብሎ ለራስ ዓላማ መገልገል በቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ውስጥ የተለመደ አሠራር ነው ።

የሳይንስና የቴክኒዮሎጂ ዕድገት የመረጃን ልውውጥ በሁሉም መልኩ አቀላጥፎ በሚገኝበት በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ የመረጃ መልዕክት በማሰራጨት በሰዎች ላይ የከፋ ማኅበራዊ ውጥረት ፣ ጭንቀት ወይም ሽብር መፍጠር ይቻላል ። በዚህ አማካይነት የቡርዧ የፕሮፓጋንዳ ምሁራን አንዳንዴ ራሳቸውን በሌላ ጊዜ ጠላት የሚባለውን ወገን አድራጊነት አጋንነው በማቅረብ በሕዝብ ላይ ሥነልቡና ጥቃት ያካሂዳሉ ።

በሚያሰራጩት ፕሮፓጋንዳ ውስጥ ራሳቸውን ከነባራዊ እውነት በላይ አግዝፈው በማቅረብ ጠላት የሚባለው ወገን በፍርሀት እንዲጨነቅ ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ እንዲገምት ፣ ተጠቂነቱንና ተሸናፊነቱን አምኖ እንዲቀበል ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ ። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ጠላት በሚባለው ክፍል የተፈጸሙ አነስተኛ ስህተቶችንና ችግሮችን ነጥሎ በማውጣት ያለቅጥ አጋንነው በማቅረብ ፓርቲን ፣ መንግሥትን ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችንና መሪዎችን ለማጥላላትና ሕዝቡን ከአመራሩ ለማቃቃር ይሞክራሉ ።

የአብዮትና የፀረ አብዮት ትንቅንቅ አይሎ በሚገኝበት ሁኔታ ደግሞ ፀረ መንግሥት ኃይሎች ታላላቅ ከተሞችንና ሕዝባዊ ተቋሞችን እንዳወደሙ ፣ ስፍር ቁጥር የሌለው (በአሀዝም ጭምር በመጥቀስ) የጦር መሣሪያና ተዋጊ ሠራዊት እንደማረኩ ፣ ጥቃቱም ወደመሀል አገር እየገፋ እንደመጣ በማውሳት ፀረ አብዮት ኃይሎች

ያከናወኗቸውን አፍራሽ ድርጊቶች አምካሽተውና በብዙ ጊዜ እጥፍ አጋንነው በማቅረብ በአብዮቱ ወገን ሥነልቡና ላይ ጥቃት ይሰነዝራሉ ።

የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በማጋነን ቴክኒኮች አማካይነት የተደራሲያንን አትኩሮት ለመሳብ ፣ ሊሆን የማይችሉትን ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ለማቅረብ ፣ በተደራሲያኑ ስሜቶች ላይ ፈጣን ጥቃት ለመሰንዘር በጥቅሉ የፕሮፓጋንዳውን የማዛባት ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ በተለያየ መልኩና አቀራረቡ ይጠቀምበታል ።

መ/ ትኩረት ማስለወጥ

ትኩረት ማስለወጥ ፣ ጠላት የሚባለው ወገን በአንድ ወቅት በሚያካሂደው ፖለቲካዊ ተግባር ላይ ሕዝቡ አትኩሮት እንዳይኖረው ስሜቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ (አብዛኛውን ጊዜ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ) ለማስለወጥ የሚገለገልበት የቡርዧው የፕሮፓጋንዳ አንድ ቴክኒክ ነው ።[23]

የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች እንዲህ ዓይነቱን ቴክኒክ የሚጠቀሙት በአመዛኙ የሶሻሊዝምን የዕድገት ጎዳና የመረጡ አገሮች የአብዮት ቀናቸውን ፣ የነፃነት በዓላቸውን በሚያከብሩበት ፣ የፓርቲ ጉባኤያቸውን በሚያካሂዱበት ፣ ወይም አንድ የጐላ ድርጊት በሚያከናውኑባቸው ወቅቶች ነው ።

የዚህ የፕሮፓጋንዳ ቴክኒክ መሠረታዊ ዓላማ ሕዝቡ በበዓሉ ፣ በጉባኤውና በድርጊቱ ዝግጅት አማካይነት ፀረአብዮት ኃይላት የፈፀሙበትን አፍራሽ ተግባራት እንዳያስብ ፣ ሶሻሊስት ሥነልቡናና ፖለቲካዊ አቋሙ ይበልጥ እንዳይጠናከር ፣ በጥቅሉ የተፈጠረው ፖለቲካዊ መድረክ ለፀረ ኢምፔሪያሊስት ፕሮፓጋንዳ እንዳያገለግል ለማድረግ ነው ። ለዚህም ከበዓሉ ፣ ከጉባኤውና ከድርጊቱ ዋዜማ ጀምሮ የኢምፔሪያሊስቱ የመገናኛ ብዙኃን በአብዮቱ ዓመታት የተከሰቱ ደካማ ጐኖችን ፣ ያጋጠሙ ተፈጥሮአዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በተለያዩ መልኮቻቸው አጋንነው በማቅረብ አብዮቱንና አመራሩን ይኮንናሉ ፤ ሕዝቡም በሀገሩ ውስጥ በመከናወን ላይ ካለው ድርጊት ይልቅ በአለፉት ሂደቶች የታዩትን ደካማ ጐኖች ብቻ እንዲያስብ ለማስገደድ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያደርጋሉ ። ለዚህም ተግባራቸው የሚገለገሉባቸውን ፕሮግራሞች በዕቅድ ይዘው በቅድሚያ አዘጋጅተው ያስቀምጣሉ ።

ሠ/ ድግግሞሽ

ምንም እንኳ አንዳንድ የቡርዧ ምሁራን አንድን ነገር ደጋግሞ ማቅረብ በፕሮፓጋንዳው ላይ እምነት እንዳይኖር ያደርጋል በማለት ድግግሞሽን ባይቀበሉም አብዛኞቹ የፕሮፓጋንዳ ጠቢባን በፕሮፓጋንዳ ሥራ ውስጥ አንድን ጠቃሚ ነው የተባለን ስያሜ ፣ ሐሳብ ፣ አቀራረብ መደጋገም የፕሮፓጋንዳው መልዕክት በሰዎች ኅሊና ውስጥ ተቀርጾ እንዲቀር ስለሚያስገድድ ልንገለገልበት ይገባል በማለት ይስማማሉ።

ይልቁንም በፕሮፓጋንዳ ተግባራቸው ውስጥ ድግግሞሽን እንዴት ሊጠቀሙበት፣ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን አይነቶች ምን ባህርይ ሊይዝ እንደሚገባና ከሌሎችም የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ ክንውኖች ጋር እንዴት ሊገናዘብ እንደሚችል በማወቁ ላይ ይበልጥ ማተኮር እንደሚገባቸው በዝርዝር ያጠናሉ ።

ለምሳሌ ድግግሞሹ የሚቀርበው በሬዲዮና በቴሌቪዥን ፕሮግራም ከሆነ በቁጥር ለስንት ጊዜ መሆን አለበት? በምን ያህል የጊዜ ርቀት? መቼ? የቃላት አጠቃቀም ፣ የድምጽና የምስል አመራረጦችን እንዴት ከድግግሞሹ ጋር ልናቀናጅ ይገባናል? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሣት በርካታ ሞዴሎች ፣ ቻርቶችና የሥራ መመሪያዎች በማውጣት ይገለገላሉ ።

የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ውሸት የሆነውን ነገር ደጋግሞ በማቅረብ እውነት ሊያደርጉት ወይም የተመረጡ ስያሜዎችን በመደጋገም በሰዎች የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ እንዲለመዱ ለማድረግ ዘወትር ይጥራሉ ። ለዚህም ነው አብዛኛውን ጊዜ የቡርዧው የመገናኛ ብዙሀን ስለካፒታሊስቱ ዓለም በሚያወሱባቸው ወቅቶች “ነፃ ዓለም” ፣ “ዲሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ” ፣ “ነፃ ባለቤትነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ” ወዘተ. ፣ ስለሶሻሊስቱ ኅብረተሰብ በሚናገሩበት ወቅት “ሰብአዊ መብት የተገፈፈበት” ፣ “ዝግ ኅብረተሰብ” ፣ “ግላዊ ነፃነት የሌለበት ኅብረተሰብ” ወዘተ. በማለት የሚደጋግሙት ። ስለአንድ የተወሰነ አስተሳሰብ ፣ ግለሰብ ወይም የአመራር አካልም ለመናገር ሲፈልጉ “አፍቃሪ ምሥራቅ” ፣ “የሞስኮ መሣሪያ” ወዘተ. የሚሉ የጥላቻ ቃላትን አዘውትሮ በመደጋገም በተደራሲያን ሕይወት ውስጥ እንዲለመዱ ብሎም ርዕዮተዓለማዊ ብክለት እንዲያስከትሉ ተዘውትረው ይቀርባሉ ።

የቡርዧው ፕሮፓጋንዲስቶች ለዚህ ዓላማቸው ለማዋል በአመዛኙ የሚመርጧቸው ቃላት ለምሳሌ “ነፃነት” ፣ “እኩልነት” ፣ “ዲሞክራሲ” ፣ “ሰብአዊ መብት” ወዘተ. በሁለቱ ማኅበራዊ ሥርዓቶች (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) ገለልተኛ የሚመስሉ ፤ ያለመደባዊ ልዩነት በማንም ዘንድ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው የሚመስሉ (ላይላዩን ለሰው ልጅ ሁሉ በተመሳሳይ የሚያገለግሉ የሚመስሉ ፣ ቡርዧው ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ዲሞክራሲ ወዘተ. ሲል እርሱ ልዕልና የያዘበትን ሁኔታ ብቻ ማለቱ እንደሆነ በግልጽ የማያሳዩ) አደናጋሪ ቃላትን ነው ። በዚህ ረቂቅ ስልት የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በየዕለቱና በየሰዓቱ የሕዝቡን ንቃተኅሊና ለማዛባት ይጥራል ።

ረ/ ያልተረጋገጠ ወሬ

ያልተረጋገጠ ወሬ (Rumor) የሚባለው ምንጩም ሆነ እውነትነቱ ያልታወቀና ከአፍ ወደአፍ የሚዛመት አንድ ዓይነት የመረጃ ልውውጥ ነው ።[24]

በመሠረቱ ያልተጨበጠ ወሬ የማኅበራዊ አስተሳሰቦችና ዝንባሌዎች መግለጫ ነው ። በመሆኑም በአንድ ሀገር ውስጥ በዚህ የመረጃ ልውውጥ መንገድ የቀረበውን አስተሳሰቦችና ዝንባሌዎች መመዝገብና መመርመር መቻል በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙትንና ያላገኙትን ጉዳዮች ለይቶ ለማወቅ የሚያስችልና አመራሩ ራሱን የሚያርምበት ፣ የሚለካበት አንድ መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል ። ከዚህም በላይ በአንዳንድ ሁኔታዎች ሕዝቡን በተፈለገው መንገድ ለመቅረፅና ለመምራት ፣ የጠላትን ጥቃት ነቅቶ እንዲጠብቅ ለማዘጋጀትም ይረዳል ። ሆኖም ያልተረጋገጠ ወሬ ማሰራጨት የዚያኑ ያህል ለመጥፎ ዓላማ እንደሚያገለግልም ሊታወቅ

ይገባል ። የገገርው መደብ ከጥንት ጀምሮ
በዚህ የፕሮፓጋንዳ ቴክኒክ አማካይነት
ሕዝቡን ሲከፋፍል ፡ እርስ በርሱ ሲያጋ
ጭና የብዝበዛ እድሜውን ለማራዘም ሲገለ
ገልበት ኖሯል ። ዛሬም ቡርዧው በስፋት
ይገለገልበታል ።

የቡርዧ ምሁራን ያልተረጋገጠ ወሬ
በርዕዮተዓለም ትግል ውስጥ ሊያበረክት
የሚችለውን ሚና በመገንዘብ ክስተቱንና
የስርጭት ሕግጋቱን ማጥናትና መመርመር
የጀመሩት ገና በ1920ዎቹና በ1930ዎቹ
ዓመታት ነበር ። ከዚህም ምርምር ያገኙ
ትን ልምድ ወዲያውኑ በፕሮፓጋንዳ ሥራ
ቸው ውስጥ መገልገል በመጀመራቸው
በዚህ ረገድ በቂ እውቀት አካብተዋል
ማለት ይቻላል ። እንዲያውም ባልተረጋ
ገጠ ወሬ አማካይነት የሚሰራጭ ፕሮፓጋ
ንዳ በመገናኛ ብዙኃን ከሚካሄደው ፕሮፓ
ጋንዳ ጋር የሚስተካከል እንደሆነ አበክ
ረው ይናገራሉ ።[25]

የቡርዧ ፕሮፓጋንዲስቶች ስለአንድ
እውነታ በቂ መረጃ ባለመገኘቱ ሳቢያ
በሕዝቡ ዘንድ የሚፈጠረውን የመረጃ
ጥማት በማጤን ሆን ብለው የተዘጋጀ የሀ
ሰት መረጃዎችን በማሰራጨት ሕዝቡ ከተ
ሳሳተ (ነገር ግን በቡርዧው የሚፈለግ)
መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ያደርጋሉ ።
ወይም አንድን አድራጐት በሞያልነት
በመውሰድና በቅድሚያ ከተዘጋጁ መረጃ
ዎች ጋር በማዳቀል ጠላት ወደሚባለው
ወገን ጆሮ እንዲደርስ በማድረግ የሥነል
ቡና ጥቃት ይፈጽማሉ ። በዚህም ስልት
አማካይነት ሕዝቡ የጥርጣሬ ፡ የፍርሀትና
የሽብር ሕይወት እንዲመራ ብሎም ከመረ
ጠው የዕድገት ጉዞ እንዲያፈገፍግና ከራሱ
የመገናኛ ብዙኃን ይልቅ ለኢምፔሪያሊስ
ቶች የፕሮፓጋንዳ ሥራ አመኔታ እንዲኖ
ረው ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ያደር
ጋሉ ። ያልተረጋገጠ ወሬ በተለያዩ ምክንያ
ቶች ፡ ግብታዊ ሆኖ ወይም ሆን ተብሎ
በተዘጋጀ ድርጊት ሊከሰት የሚችል በቀ
ላሉ ከአፍ ወደአፍ በመተላለፍ ይበልጥ
እየተጋነነና ስፋት እያገኘ በፍጥነት የመዳ
ረስ ባሕርይ ያለው በመሆኑ የቡርዧው
ፕሮፓጋንዲስቶች የተለየ ትኩረት ሰጥ
ተው የሚያጠኑትና የሚገለገሉበት ነው ።

ሰ ዝምታ

በተደራሲያኑ ዘንድ አንገብጋቢ ሆነው
የተነሡ ጉዳዮችን በዝምታ ማለፍና ስለሌ
ሎች ጉዳዮች ዝርዝር ነገሮችን ማቅረብ
በቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ዘንድ የተለመደ
አንድ ቴክኒክ ነው ። ይህ ቴክኒክ አንዳንዴ
በነባራዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነት በሌላ
ወቅት ደግሞ በተደራሲያኑ ዘንድ ተአማኒ
ነት ለመፍጠር በማሰብ ሆን ተብሎ በተግ
ባር ላይ ይውላል ። በሶሻሊስት ወይም ይህን
የዕድገት ፈለግ በመረጡ አገሮች ውስጥ
ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ አምኖ የተቀበላቸውን
ድሎች ማጥላላት በተደራሲያኑ ዘንድ ማንነ
ታቸውን ይፋ የሚያደርግ ስለሚሆንና ድሎ
ቹን አሞካሽቶ ማቅረቡ ደግሞ የሥርዓተ
ማኅበሩን ትክክለኛነት መመስከር በመሆኑ
ዝምታን መምረጥ ይገደዳሉ ። ለዚህም ነው
ለምሳሌ በአንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች የእር
ሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውጤት ያላስገኘ ከሆነ
ለዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ መዳከም መሠረታ
ዊው ምክንያት የአምራቾች የኅብረት ሥራ
ማኅበር መኖር ነው በማለት የአምራቾች
የኅብረት ሥራ ማኅበርን ለመኮነን ሲጣ
ደፉ፡ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት
ውጤት ባስገኙባቸው አገሮች ግን በሶሻሊ

ስት የእርሻ አደረጃጀት ምክንያት የተገኘ
ድል ነው ብሎ ከማቅረብ ይልቅ ዝምታን
የሚመርጡት ።

በሌላ በኩል ደግሞ የቡርዧ የመገናኛ
ብዙኃን ስለአንድ አገርና አብዮት የሚያሰ
ራጩት ተደጋጋሚ ፕሮፓጋንዳ በተደራሲ
ያን ዘንድ ትዝብት እንዳይፈጥር መገናኛ
ብዙሀኑ ለዚሁ ተግባር ብቻ የተደራጁ
ሆነው እንዳይቆጠሩ ነገሮችን ሳያነሡ በዝ
ምታ ያልፋሉ ። በዚህ መልኩ ዝምታቸው
“እኛ ስለእናንተ ጉዳይ ብቻ አይደለም የምን
ናገረው ፤ የናንተን አገርና አብዮት ለማጥላ
ላት ብቻ የምንሠራ አድርጋችሁ አትቁጠ
ሩን ማለታቸው ነው ።” ይህ ደግሞ በአንድ
በኩል በተደራሲያኑ ዘንድ ተአማኒነትንና
ተደማጭነትን ለማትረፍ ፡ በሌላ በኩል
ደግሞ ለረዥም ጊዜ ስለአንድ አገርና አብ
ዮት ሲለፈልፉ መቆየታቸውን በዝምታ
ለማካካስ የሚያደርጉት ጥረት ነው ። በአን
ዳንድ ሁኔታም ስለተወሰነ አገርና ጉዳይ
መረጃ ሲጠፉ ወይም ጉዳዩን ለጊዜው
ማንሣቱ አስፈላጊ አለመሆኑ ሲታመንበት
በዝምታ ሊታለፍ እንደሚችል ከዚሁ ጋር
ልናስተውል ይገባል ።

ከላይ የተመለከትናቸው የፕሮፓጋንዳ
ቴክኒኮች ነባራዊውን እውነታ በተሳሳተና
በተዛባ መንገድ በማቅረብ ግለሰቦች ፤
ማኅበራዊ ክፍሎች ፤ በአጠቃላይም ሰፊው
ሕዝብ የምዕራቡን የአኗኗር ሁኔታ አድና
ቂና ናፋቂ እንዲሆን ፡ ኑሮውንና የዕለት
ተዕለት ሕይወቱን በራሱ ሳይሆን በምዕ
ራቡ መስፈርቶች እንዲመዝን ለማስገደድ
የተዘረጉ የማጥመጃ መረቦች ናቸው ።

በአጠቃላይ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ንድፈ
ሐሳቦችን ፤ ተግባራት ፤ ዓይነት ፤ ስልትና
ቴክኒኮችን መሠረታዊ ተልዕኮ ስናስተውል
በመዋሸት ፡ በማጭበርበርና በማሻጠር የሕ
ዝብ ንቃተኅሊናን ለራሳቸው እኩይ ዓላማ
መገልገያ ማድረግ መሆኑን ልንገነዘብ ይገ
ባል ።

ማጠቃለያ

የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ በሰዎች ሥነ አመ
ክንዩአዊ (ሎጂካዊ) ዕውቀት ሳይሆን የዕ
ለት ተዕለት ዕውቀታቸውን ፤ የደመነፍስ
ግንዛቤአቸውንና አለማወቃቸውን መጠቀ
ሚያ በማድረግ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ
አድራጐት ለፀረ ሶሻሊስት ዓላማዎቹ የሚገ
ለገል አፍራሽ ክስተት ነው ። ይህን ክስተት
የመታገሉ ተግባር እውነተኛ ፍትሕ የሰፈነ
በት ኅብረተሰብ ለመገንባት ከሚደረገው
ጥረት ጋር በጽኑ የተሳሰረ ነው ። አፍራሽ
ክስተቶችን ሳይታገሉ ለፍትሕ ኅብረተሰብ
ወይም ሶሻሊዝምን ለመገንባት ማሰብ ባዶ
ምኞት ከመሆን አያልፍም ። አፍራሽ ክስተ
ቶችን ለመታገል ደግሞ ለምንነታቸው ምክ
ንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ውስጣዊ አወቃ
ቀር ፤ ከሌሎች ነገሮች ጋር ያላቸውን
መስተጋብራዊ ግንኙነት በመመርመር
አጠቃላይ ባሕርያቸውን ማወቅ ያስፈል
ጋል ። አፍራሽ ክስተቶች ላዕላይ መዋቅራ
ዊና ኅሊናዊ ባሕርይ ካላቸው ሁኔታዎች
የሚመነጩ ብቻ ሳይሆኑ ቁሳዊና ማኅበራዊ
መሠረት ያላቸው በመሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎ

ችም ለምንነታቸውና ለዕድገታቸው ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። አፍራሽ ክስተቶች ባላቸው የተወሳሰበ ባሕርይ የተነሣ እነርሱን ለመከላከል ብሎም ለማስወገድ የሚደረግ ትግል እንዲሁ ባለብዙ ፈርጅና እያሌ ስልቶችን የሚከተል ነው ።

የኢምፔሪያሊዝም ፕሮፓጋንዳ በአገሮች ውስጥ የሚታዩትን ድክመቶች ፡ እንቅፋቶች ፡ ችግሮች በጥቅሉ ለዕድገት አፍራሽ የሆኑ ክስተቶችን መሠረት በማድረግና በእነርሱ በመጠቀም የሚሰራጭ በመሆኑ የመከላከሉ ቀዳሚ ጥረት በአገር ውስጥ ያሉትን አፍራሽ ክስተቶች መዋጋት መሆን ይኖርበታል ። የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ተሸካሚ የሆኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እየተወገዱ በሄዱ መጠን የኢምፔሪያሊስቶች ፕሮፓጋንዳ ሰሚ ጆሮና ተቀባይ አዕምሮ እያጣ ወደ ባዶ ጩኸት እየተለወጠ ይሄዳል ።

የዕድገትን አፍራሽ ክስተቶች መዋጋት ማለት ከሁሉ በፊት ምርትንና ምርታማነትን ማዳበር ፡ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ማሻሻል ፡ የፍትሕ ግንኙነት እየሰፈነ እንዲሄድ ማድረግ ፡ በአጠቃላይ አገሪቷ ለዕድገቷ የቀየሰችውን የማኅበረ ኢኮኖሚ የልማት ዕቅዶች በተግባር ለመተርጎም ብርቱ ጥረት ማድረግ ማለት ነው ። ይህ ደግሞ በማኅበራዊ ሕይወት የሚታዩ አፍራሽ ክስተቶችን ማለትም ሳይሠሩ መብላትን ፡ ጠባብ ስሜትን ፡ በሥልጣን መባለግንና ቢሮክራሲያዊነትን፡ ወዘተ የመሳሰሉትን አፍራሽ ክስተቶች ለመዋጋት በሚያስችሉ ወቅታዊና ተጨባጭ በሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎች መታገዝ ይኖርበታል ። የነዚህ እርምጃዎች ቀዳሚ ዓላማ ደግሞ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ አጥፊውን ለመቅጣት ብቻ ሳይሆን አፍራሽ ክስተቶቹ ለዘለቄታው እንዲወገዱ፡ ዳግም እንዳይፈጠሩና እንዳይባዙ መከላከል መሆን ይኖርበታል ። ከዚህም ባሻገር አፍራሽ ክስተቶችን ለመዋጋት የተወሰዱትን እርምጃዎች በየወቅቱ ለሕዝብ በማሳወቅ የሕዝቡን ሥነልቡና ፡ ሥነ ምግባርና ፓለቲካዊ አቋም መቅረፅና ማጠናከር ያስፈልጋል ። እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማሳወቅ ሕዝቡ በአመራር ላይ ጽኑ እምነት እንዲኖረው ፡ የዜግነት ስሜቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ይረዳዋል። የዚህ ዓይነቱ ሕዝባዊ መንፈስ መፈጠሩ ደግሞ በፊናው የባዕድ ፕሮፓጋንዳን ለመቋቋም ሁኔታውን ምቹና ቀላል ያደርገዋል ።

የቡርዧውን ፕሮፓጋንዳ ጨምሮ አፍራሽ ክስተቶችን ለመከላከል ፡ ብሎም ለማስወገድ እስካሁን ያመለከትናቸው ተግባራት ሕዝቡ ከተግባራዊ ሕይወቱ ተምሮ ለተሻለ ሕይወትና ትግል እንዲዘጋጅ የሚረዱ ቢሆንም አዲሱን ኅብረተሰብ ከመገንባት ዘላቂ ግብ አኳያ በቂ አይሆኑም። ስለዚህም ከነዚህ ተግባራት በተጨማሪ ሥርዓት የያዘ የትምህርትና የርዕዮተዓለም ሥራ ተጠናክሮ መካሄድ ይኖርበታል።

በተለይም የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ዒላማ የሆነው ወጣቱ ትውልድ ለሥራ አክብሮት፡ ለእናት አገሩ ፍቅር እንዲኖረው ፡ ሰው በሰው ለማይበዘበዝበትና ፍትህ ለሰፈነበት ኅብረተሰብ ግንባታ ጠንክሮ እንዲንቀሳቀስ ፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት እንዲጨብጥና የምርምር ፍላጎቱ እንዲጐለብት የሚያስች

ለው የትምህርት ሥርዓት ሊዘረጋለትና በርሱም ተኰትኩቶ ሊያድግ ይገባል ። ትምህርት ቤቶችም በትምህርት መሣሪያነት አዲሱን ዜጋ ለመቅረጽ የሚችሉ ተቋሞች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተጠናከረ ትኩረት ያሻቸዋል ።

ከማስተማር ተግባር ጋር የተቀናጀና ራሱን የቻለ የርዕዮተዓለም ሥራ በስፋት ማካሄድም በጣም አስፈላጊ ነው ። የርዕዮተዓለም ሥራ ሲባል በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ርዕዮተዓለማዊ ፋይዳዎችን መመሥረት ፣ ማስረጨትና ወደቁሳዊ ኃይል መቀየር ወይም ማኅበራዊ አካባቢን* መለወጥ ማለት ነው ። በመሆኑም ይህ ተግባር ሁለት የማይነጣጠሉ ጥንድ ተግባራትን ማለትም በአንድ በኩል ማኅበራዊ አካባቢን በመለወጥና በዚህም ለውጥ አማካይነት ሰብዕናን መቅረፅ ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሰዎችን ንቃተኅሊና በመለወጥ ብሎም ማኅበራዊ ተሳትፎአቸውን በብቃት በማጐልበት ማኅበራዊ አካባቢያቸውን እንዲለውጡ ማዘጋጀትንና ማነሣሣትን የሚያገ፣ ነው ።

በመሠረቱ ማኅበራዊ አካባቢ ግለሰቦችን በመቅረፅ ያለው ሚና ግለሰቦች ከአካባቢያቸው ማኅበራዊ ልምድን በመቅሰማቸው በጥቅሉ በግለሰቦችና በአካባቢያቸው መካከል በሚተላለፉ መረጃዎች የሚገለፅ ነው ። ይህ ልምድን የመቅሰም ወይም መረጃን የመለዋወጥ ሂደት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚከናወን ነው ። ግለሰቡ በቀጥታ ከአካባቢው ጋር በሚያደርገው መስተጋብራዊ ግንኙነት አማካይነት ማኅበራዊ ልምዶችን ያካብታል ። ስለአካባቢው የራሱን ግንዛቤ ይቀርጻል ። በግለሰቡና በአካባቢው መካከል የሚኖረው ቀጥተኛ ግንኙነት በአመዛኙ በግብታዊ ሂደት የሚፈጸም ነውና ለምንከተለው የዕድገት ፈለግ ጠቃሚ ወይም ጐጂ ሊሆን ይችላል ። ይሁንና በአገሪቱ ያለው ኅሊናዊ ሁኔታ ይህን ግብታዊ ሂደት በርዕዮተዓለም ሥራና በትምህርት ሊያርቀው ይችላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ሥርዓት በመዘርጋት ፣ የርዕዮተዓለም ሥራ በማካሄድ ፣ ማኅበራዊ አስተዳደርን በማደራጀትና ሕዝቡን በንቃት በማሳተፍ ወዘተ. ማኅበራዊ አካባቢው በተደራጀና በቅድሚያ በታቀደ ዓላማ ግለሰቡን መቅረጽና መለወጥ ይችላል ። እነዚህ ተግባራት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ቢሆንም የርዕዮተዓለሙ ሥራ ዐቢይ ቦታ ይይዛል ። የርዕዮተዓለም ሥራ በማኅበራዊ አካባቢና በግለሰብ መካከል ባለው መስተጋብራዊ ግንኙነት ላይ መመሥረትና ይህንንም መስተጋብራዊ ግንኙነት ለመቆጣጠር ፣ በተፈለገው አቅጣጫ ለመምራት ፣ ለመለወጥና ለማሳደግ መቻል ይኖርበታል ። በዚህ ረገድ የሚከናወን የርዕዮተዓለም ሥራ በአንድ በኩል ማኅበራዊ አካባቢን ለመለወጥ ምን መደረግ እንዳለበት ማቀድ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበራዊ አካባቢው በተራው ከርዕዮተዓለም ሥራ የሚጠይቀውን የአሠራር ሥርዓት ፣ የሥልትና የዘዴ ጥያቄዎችን አስተውሎ ለተጨባጭ ሁኔታው በሚመጥን መልኩ ለውጥ ማድረግን ይሻል ።

* ማኅበራዊ አካባቢ ሲባል ቁሳዊ ምርትን ፣ ማኅበራዊ አስተዳደርን ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ፣ ግንኙነቶችን ፣ የሰው ዘር መራባትን አካቶ የያዘና በውስጡም በርካታ ንዑስ ክፍሎች ያሉት ማኅበራዊ ሥርዓት ነው ።

የርዕዮተዓለም ሥራ ማኅበራዊ አካባቢን ለመለወጥ እንዲቻል ሰብአዊ ኃይልን በማንቀሳቀስ ላይ ብቻ ሳይሆን አፍራሽ ክስተቶችንና የቡርዧውን ፕሮፓጋንዳ በመከላከል ፡ በመቋቋምና በማጋለጥ ፡ የንድፈሐሳብ ፡ የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ተግባራት ላይ በስፋት ማተኮር ይኖርበታል ። በተለይም የቡርዧውን የኀሊና ጥቃት ለመቋቋም አጸፋ ፕሮፓጋንዳ ሊደራጅ ይገባል ።

አፀፋ ፕሮፓጋንዳ ስንል የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ሕዝብ ላይ የሚያስከትለውን ያላሰለሰ መርዘኛ ጥቃት ለመቋቋም ፡ ብሎም የኢምፔሪያሊስቱን ፕሮፓጋንዳ ስትራቴጂና ታክቲክ ለማጋለጥ በማቀድ የሚደራጅና የሚካሄድ የፕሮፓጋንዳ ሥርዓት ነው ። በመሆኑም አፀፋ ፕሮፓጋንዳ የመቋቋምና የማጋለጥ ሁለት መሠረታዊ ተግባራት ይኖሩታል ።[26] እነዚህ ሁለት ተግባራት እርስበርሳቸው የተያያዙ ሲሆኑ በዚህ የግንኙነት ሂደት ውስጥ ቀዳሚውን ቦታ ይዞ የሚገኘው የመቋቋም ተግባር ነው ።

የመቋቋሙ ተግባር ዐቢይ ዓላማ ሕዝቡ መደባዊ እምነትና በዓላማው ፅናት እንዲኖረው ማስቻል ሲሆን የተግባር ክልሉም መላውን የማኅበራዊ ንቃተኅሊና መልኮች በዚህ መንፈስ መቅረፅና ጠንካራ ሥነልቡናዊ ዝግጁነት እንዲኖር ማድረግ ነው ።

የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ ሌላው ተግባር የቡርዧውን ፕሮፓጋንዳ ማጋለጥ ነው ። ቡርዧው በተለያዩ ስልቶች አማካይነት ቀይም ብሎ ያሰራጫቸውን አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ነጥሎ በማውጣት የተዛቡና ከእውነት የራቁ መሆናቸውን በተጨባጭ መረጃዎች ማሳየት ፡ የአቀራረባቸውን መሰሪ ስልቶችና የፕሮፓጋንዳቸውን ፀረ ሕዝብ አቋም ማጋለጥ ነው ።

በመሠረቱ የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ ስልቶች ኢምፔሪያሊዝም ለሚያሰራጫቸው የፕሮፓጋንዳ መልዕክቶች በበቂ ዝግጅትና በተፋጠነ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ማስቻል ይኖርባቸዋል ። የዚህ ዓይነቱ አሠራር ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ደግሞ ከፍተኛ ብቃትን ይጠይቃል ። በአፀፋ ፕሮፓጋንዳ ተግባር ውስጥ ዋናው ቁም ነገር በተገቢ ሳይንሳዊ ጥናትና ዝግጅት ላይ ተመሥርቶ የቡርዧውን ቅጥፈት ፡ የአቀራረብ ስልቱንና ዘዴዎቹን በበቂ ማስረጃ ማጋለጥ መቻል ነው ። ሕዝቡ የቡርዧውን የርዕዮተ ዓለም ዝበት (መዛባት) እንዲገነዘብና በቂ የውጊያ ትጥቅ እንዲኖረው በማድረግ ሥልት ማተኮሩ ጥረቱን ፍሬያማ ያደርገዋል ።

አፀፋ ፕሮፓጋንዳ ዘወትር በሳይንሳዊ ትንታኔ ላይ የተመሠረተ ፡ መደባዊ ወገናዊነት ያለው ፡ በተከታታይ የሚደረግ ፡ የአጥቂነት አቋም የያዘና ብቁ ዝግጅት የሚሻ በመሆኑ የፓርቲ የቅርብ አመራርና ክትትል የሚያስፈልገው ውስብስብ ተግባር ነው ።

የፕሮፓጋንዳ ሥራችን የሰፊውን ሕዝብ ንቃተኅሊና ከቡርዧው የሥነልቡና ጥቃቶች መከላከል ብቻ ሳይሆን ሰፊው ሕዝብ ርዕዮተዓለማዊ ትጥቁን እንዲያጎለብትና ራሱን በብቃት ወደሚከላከልበት ደረጃ እንዲሸጋገር ማስቻል ይኖርበታል ። ለዚህም ፕሮፓጋንዳችን በቅርፁ ላይ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በይዘት ፡ ሥርዓት ባልያዘው የንቃተኅሊና ክፍል ላይ ሳይሆን ሥርዓት በያዘው (በሎጂካዊ) እውቀቱ ላይ ሊያተኩር ይገባል ። ይህ ማለት ግን ሥርዓት ያልያዘው የሰዎች ንቃተሕሊና ፣ የሰዎች የስሜት ዓለም በፕሮፓጋንዳ ተግባር ውስጥ አያገለግልም ወይም ልንገለገልበት አይገባም ማለት አይደለም ። እንዲያውም ያለሰብአዊ ስሜቶች እውነትን ለመፈለግ የተደረገ ጥረት ከቶውም የለም ፣ ሊኖርም አይችልም ።[27] ስሜቶችና ዝንባሌዎች በኅብረተሰብ በተለይም በሰፊው ሕዝብ የዕለትተዕለት ግንዛቤዎች ፣ አስተሳሰቦችና ልማዶች ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በማስተዋል በሳይንሳዊ ጥናት ላይ ተመርኩዞ በአግባቡ መገልገል ያስፈልጋል ። በመሆኑም የፕሮፓጋንዳ ሥራችን የሕዝቡን ስሜት የሚኰረኩሩ ሥልቶችን መርጦ በእነርሱ የሚጠቀም ፣ የተደራሲያኑን ፍላጐት በሚገባ ያጤነ ፣ ተአማኒነትና ተቀባይነት ያለው ፣ ወቅቱን የጠበቀ ፣ ዘወትር አዳዲስ መረጃዎችን የያዘ ፣ የተደራሲያኑን ውስጣዊ ጥንቅር የመረመረና በምላሽ መረጃ ትንተና የሚገለገል መሆን ይኖርበታል ።

ከዚህም በላይ የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ውጤታማ እንዲሆን በመገናኛ ብዙኃን ውስጥ የተሰማራው የሰው ኃይል በየወቅቱ የሙያና የርዕዮተ ዓለም ብቃቱ እንዲጐለብት ፣ ስለአዳዲስ ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ጉዳዮች የቅርብ መረጃ እንዲያገኝና ነገሮችን የሚገመግምበት ሥነዘዴያዊ ዕውቀቱ እንዲጐለብት ተገቢ እገዛ ሊደረግለት ይገባል ። ይህ ብቻም አይደለም ፣ በመገናኛ ብዙኃን የተለያዩ ዘርፎች መካከል ያለው ልዩነትና አንድነት በትክክል ታውቆ የተቀናጀና ሥርዓት የተከተለ ተግባር እንዲፈፅሙ ማስቻል ፣ የፕሮፓጋንዳው ሥራ ውጤታማነት የሚመዘንበት መስፈርት አውጥቶ ዘወትር የራስን የፕሮፓጋንዳ ሥራ ውጤታማነት መመዘን ያስፈልጋል ። አሠራራችን ሳይንሳዊነትን እየተከተለ በሄደ ቁጥር በሀቅ ላይ የተመሠረተው ፀረ አድኅሮት ፕሮፓጋንዳ አሸናፊ እየሆነ ይሄዳል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. የኮሚኒስታዊ ትምህርት መዝገበ ቃላት ፡ (ሶፊያ ፣ የፓርቲ ሕትመት ፣ 1985 ቡልጋሪያኛ) ገጽ 20.
2. ከላይ በተጠቀሰው ፣ see, *Social Psychology and Propaganda* (Moscow: Progress Publishers, 1985), P.38
3. ኤን. ዮርዳኖቭ ፣ የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ —ንድፈ ሐሳብና ተግባር (ሶፊያ ፣ 1976 ፣ ቡልጋሪያኛ) ገጽ 41; See, *A Modern Dictionary of Sociology* (New York: Barnes & Noble Book, 1979), P.318.
4. See, Mshvenieradze V., *Political Reality and Political Consciousness* (Moscow: Progress Publishers, 1985), P.218
5. ኤም ቼካስ ፣ ፕሮፓጋንዳ ዳብሯል (ሞስኮ 1968 ወደ ቡልጋሪያኛ የተመለሰ) ገጽ 55; See *Encyclopedia of Social Science* (New York: Macmillan 1957) Vol. 11, PP. 521-522
6. See, *International Encyclopedia of Social Sciences* Vol. 2, P. 579.

7. See, Mschvenieradze V. Op. Cit. PP. 214-219.
8. See, *Social Psychology and Propaganda*. Op. Cit. P.219.
9. Ibid., P.212.
10. የዘመኑ የርዕዮተዓለም ትግል (ሶፊያ ፡ የፓርቲ ሕትመት ፡ 1985 ቡልጋሪያኛ) ገጽ 448 – 449.
11. See, Volkogonov D., Op. Cit. pp. 96-97.
12. የዘመኑ የርዕዮተዓለም ትግል ፡ ገጽ 450; See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. PP. 212 - 213.
13. See, Volkogonov D. Op. Cit. P.138.
14. Ibid. P. 147.
15. Ibid. P. 125.
16. See Mshvenieradze V. Op. Cit., P. 219; See, *Political Terrorism*, (Moscow: Progress Publishers, 1983), PP. 260-268.
17. See, Paul M.A Linevarger, *Psychological War*, (Washington Infantry Journal Press, 1948;) See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. PP. 217-218; See, *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 21, P.269.
18. See, Mshvenieradze V. Op. Cit. 235; *International Encyclopedia of Social Sciences*, Vol. 13, P.49. See Harry Could, *Marxist Glossary*, (San Francisco: Proletarian Publisher, 1948) P. 73.
19. See, *Scientific Communism*, (Moscow: Progress Publishers, 1982) P. 325; Volkogonov D.
20. See, Volkogonov D.Op. Cit. P.99.
21. መሠረታዊ ወታደራዊ ሲየሟዎች መፍቻ መዝገበ ቃላት (ሞስኮ ፡ ወታደራዊ ሕትመት፡ 1965)
22. See, Volkogonov D. Op. Cit. P. 106.
23. See, Volkogonov D. Op. Cit. P. 107.
24. Ibid., P. 111.
25. See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. P. 200.
26. የኮሚኒስታዊ ትምህርት መዝገበ ቃላት ፡ ገጽ 124
27. V.I.Lenin Collected Works, Vol. 20, P. 260.

የድኅረ–ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ

ከበላይነህ አሰጉ

በምሥራቅ ኢትዮጵያ የመንደር ምሥረታ እንቅስቃሴ የተጀመረው በየካቲት ወር 1977 ነው ። የመንደር ምሥረታው በተፋፋመ ሁኔታ ተካሂዶ አብዛኞዎቹ በተለይ በግብርና በሚተዳደሩት አካባቢዎች የተመሠረቱት መንደሮች በ1977 እና በ1978 በተካሄዱት ሁለት ዙር ዘመቻዎች የተጠናቀቁ ናቸው ። በዚህም መሠረት ከየካቲት 1977 እስከ መጋቢት 30 1980 ባለው ጊዜ በስምንቱ ደጋማ አውራጃዎች ፡ በ34 ወረዳዎች ፡ ቀድሞ የነበሩ 12,394 መንደሮች በ3,686 አዳዲስ መንደሮች ተሰባስበዋል ። በእነዚህ መንደሮች 502,834 ቤቶች ተሠርተው 526,093 አባወራና 2,055,830 ቤተሰብ በድምሩ 2,581,923 ገበሬዎች በመንደር ተሰባስበዋል ። *

ገበሬው በመንደር የተሰባሰበው ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎችን ማግኘት እንዲችል የአኗኗሩን ሁኔታ ማመቻቸት መሆኑ ይታወቃል ። ከዚህ አኳያ እስካሁን ባለው ጊዜ የሚታየው የለውጥ አዝማሚያ ምን ይመስላል? የገበሬው ሕይወት እየተለወጠ ነው ወይ? ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የክልሉን ሁኔታ እንቃኛለን ። በእርግጥ ሁለትና ሦስት ዓመት ብዙ ለውጥ የሚጠበቅበት ጊዜ አይደለም ። አንዳንድ የዕድገት ፍንጭ ለማየት የማይስችል ነው ማለትም አይቻልም ። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከመሞከራችን በፊት እስኪ በብሔራዊ የመንደር ምሥረታ ኮሚቴ የተገለጹትን የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም ዓላማዎች እንመልከት ።

የመንደር ምሥረታ ዓላማዎች

1. ለገጠሩ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎት

* የሐረርጌ ገበሬ ከትናንት እስከ ዛሬ ፡ ከላይ የተጠቀሰው ፡ ገጽ 35.

መስከረም

* ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና

* የድኅረ—ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ

* የፖሊቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈ ሐሳብና የተግባር ዕውቀት

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 9 ቁጥር 30
ታኅሣሥ 1981

መስከረም

ቅጽ 9 ቁጥር 36
ታኅሣሥ 1981

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና 9
  በላቸው ሙሉጌታ

* የድኅረ—ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ 35
  በላይነህ አስጉ

* የፖሊ. ቴክኒክ ትምህርት ለተመጣዘነ የንድፈ ሐሳብና
  የተግባር ዕውቀት 53
  ደስታ ወዳጅ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

ሰላም ፡ ለዕድገት መሠረታዊ ዋስትና

ባለፉት የአብዮት ዓመታት በሀገራችን ፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ተጽዕኖ በማስወገድ ለአዲስ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት ለመጣል በርካታ ተጨባጭ እርምጃዎች ተወስደዋል ። በልዩ ልዩ መልክ የሀገራችንን ህልውና ለመቀናቀን የተሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመቋቋም ተችሏል ። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ መብቱ በእኩልነት የሚከበርበትን ፡ ከኋላቀርነት በመላቀቅ ለብልፅግና የሚበቃበትን ሥርዓት እውን ለማድረግ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍሏል ፡ ጉልህ ታሪካዊ ውጤቶችን ለመጨበጥ በቅቷል ። ይሁን እንጂ በጀመረው የማኅበራዊ ዕድገት ጉዞ እርምጃውን እንዳያፋጥን በሰሜን በኩል የገጠመው ሰላምና አንድነቱን የሚፃረር ሁኔታ ጋሬጣ ሆኖበት ቆይቷል ።

በክልሉ የሀገራችንን ህልውና የሚፈታተነው ጦርነት የቱን ያህል ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት መሥዋዕትነት እንደጠየቀ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተገልጿል ። በተለይ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ባቀረቡት ሪፖርት እንደገለጹት በመከላከያ ረገድ ብቻ እንኳን የሚደረገው እጅግ ከፍተኛ ወጭ ሁኔታውን በግልጽ ያሳያል። በሪፖርቱ እንደተመለከተው "የመከላከያን በጀት ብንመለከት በ1966 105.8 ሚሊዮን ብር የነበረው በ1981 1 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ደርሷል ። …በ1980 የመከላከያ ወጭ ያለው ድርሻ ከጠቅላላው ምርት ውስጥ 15 በመቶ ፡ ከመደበኛ በጀት 50 በመቶ ፡ ከጠቅላላው ገቢ 54 በመቶ ደርሷል ።" በዚህ መልክ በቀጥታ ለመከላከያ ከሚደረገው ወጭ ሌላ በዐረ አንድነት ቡድኖች የሚፈርሱ ተቋሞችን ፡ የሚወድሙ ልዩ ልዩ የአገልግሎት መስጫ አውታሮችንና ንብረቶችን መልሶ ለማቋቋም ፡ ለመጠገንና ለመተካት የሚወጣው ገንዘብ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው ። ይህም ብቻ አይደለም ። ችግሩ ባለባቸው አካባቢዎች ለሚገኙት ዜጎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማድረስ የሚደረገው ጥረትና ወጭም እጅግ ከባድ ነው ።

እንደሚታወቀው በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ በኤርትራ ክልል ያለው ችግር በአብዮቱ ዓመታት የተፈጠረ አይደለም ። ይልቁንም ኤርትራ እንድትገነ

ጠል የማድረግ ባሕርዩ መሠረት እንዲያጣ የተደረገው በአብዮቱ ነው ። በተለይ በፊውዳሉ አገዛዝ ዘመን በክልሉ የነበረው እንቅስቃሴ ፀረ ፊውዳል ነው በሚል በውስጥም ሆነ በውጭ የተወሰኑ የተራማጆች ድጋፍ እንደነበረው የሚዘነጋ አይደለም ። ሆኖም የመላ ኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የእኩልነትና የፍትሕ ጥያቄ የሚያካትተው ሀገር አቀፍ አብዮት ሲቀጣጠል በኤርትራ ያለው እንቅስቃሴ ምንነት ይፋ ወጣ ። በእንቅስቃሴው ውስጥ በተሰለፉት መካከልም መጠየቂያ ግድ ሆነ። በተፈጠረውም ቅራኔ ውስጥ አቋማቸው ታፍኖ የመገንጠልን ጠባብ ዓላማ እንደፍጹማዊ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ አድርገው የያዙት የበላይነትን ሊይዙ በቅተዋል።

እነዚህ የመገንጠል ዓላማ የሙጢኝ ያሉትና ይህንኑ ለማስፈጸም ጦርነትን ዋንኛ ምርጫቸው ያደረጉት ወገኖች ለጭፍን ዓላማቸው ድጋፍ ለማስገኘት አመች የመሰላቸውን የፖለቲካ አቋም ሲለዋውጡ ቆይተዋል ። ቀደም ሲል ያደናግሩበት የነበረውን የፀረ ፊውዳል አቋም ከላይ እንደተጠበቀው አብዮቱ ፉርሽ አድርጐባቸዋል ። የብሔር ጥያቄ በሚልም ለረጅም ጊዜ ለማሳመን ሞክረው ነበር ። አልተሳካላቸውም ። በቀይ ባሕር አካባቢ አረባዊነት ጐላ ብሎ ስለሚታይ ምናልባት ዐረባዊ ነን በማለት ከኢትዮጵያ ልዩ መምሰል ተቀባይነት ያስገኝ ይሆናል በሚልም ብዙ ተሞክሯል ። በመጨረሻም ሌላው ሁሉ ሳያዋጣ ሲቀር ጣሊያን በክልሉ በቅኝ ገዢነት ለተወሰነ ጊዜ ያደረገውን ቆይታ ምክንያት በማድረግና ግዛቱን የኢትዮጵያ ታሪክ ገሸሽ ለማድረግ በመሞከር ለማደናገር ይጥራሉ ። “ቀድሞ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት የነበረች ኤርትራ እንደገና በኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ሥር ወደቀች ፡ ስለዚህም ትግላችን ፀረ ቅኝ አገዛዝ ነው” ይላሉ ። የኤርትራ ክልል በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች እንደተፈለገ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ተቀጥፎ ለተወሰነ ጊዜ የመቆየቱ ጉዳይ የማያጠያይቅ ቢሆንም፡ ይህ ግን የክልሉን ታሪክ ምን ያህል ከኢትዮጵያ ታሪክ ጨርሶ የተለየ ሊያደርገው “እንደቻለ” በተለይ ከተጨባጩ ሁኔታ ይበልጥ ሊያሳምን የሚችል አይኖርም ። እርግጥ የመገንጠሉ ዓላማ እንዲሳካላቸው የሚፈልጉ ወገኖች በአንዳንዶች ዘንድ የፈጠሩት ውዥንብር በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

በአጠቃላይ የጦርነት ሁኔታ ባስከተለው አለመረጋጋትና ተገንጣዮቹ ለጠባብ ዓላማቸው በሕዝብ መካከል መቃቃር እንዲፈጠር ባደረጉት ያልተቋጠበ ሙከራ በርካታ ዜጎች በየባዕድ አገሩ ለስደት መዳረጋቸው ይታወቃል ። ብዙዎቹ ከሀገራቸው ውጭ ከማኅበራዊ ኑሮ ተገልለው መብታቸው በሕግ የማይከበርበት የሰቀቀን ሕይወት መግፋታቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው። አልፎ አልፎ በመጠኑ በኢኮኖሚ የቀናቸው ሊኖሩም ቢችሉ በባዕዳን መካከል የሚደርስባቸው ተጽዕኖ የሚያዝናና አይደለም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ጊዜ እየሄደ ፡ ትውልድ እያለፈ ትውልድ የመተካቱ አዝማሚያ በየባዕድ ሀገሩ ምን

ዓይነት ዜጎችን እያፈራልን ነው የሚለው ጥያቄ እጅግ የሚያሳስብ ነው ። ሁሉም የሚያምረው ያለጥርጥር በሀገር ነው ። ባህል ፡ ቋንቋ ፡ እምነት ፡ በአጠቃላይ የእራስ ማንነት ሊከበር የሚችለው በእራስ ሀገር ነው ። የስደት ሕይወት የሚያስከትለው ጉዳት በተሰደደው ዜጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በሀገርና በወገንም ነው ። ከዚህ አንፃር በተለይ በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በኩል የደረሰው ጉዳት የቱን ያህል የከፋ እንደሆነ የተሠወረ አይደለም ።

የኤርትራ ተገንጣዮች ያንኑ ጠባብ ዓላማቸውን ዳር ለማድረስ ያልፈጸሙት ድርጊት የለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት እንዳይደርስባቸው በእሩቁ ለመከላከል በነበራቸው ፍላጐት ትግራይ ክልል ውስጥ መሰላቸው የሆነ ቡድን መፍጠራቸው አንዱ አድራጐታቸው መሆኑ ይታወቃል ። የእነርሱ ዓላማ ኤርትራን መገንጠል ሲሆን አብዮቱን ከራሳቸው ራቅ አድርገው ለመገደብ በነበራቸው ምኞት በትግራይም ለፈጠሩት ቡድን ያሸከሙት ግብ “ሐርነት ትግራይ” ወይም ትግራይን ነፃ ማውጣት የሚል ነበር ። በዚህም የማይመስል ዓላማ ምክንያት የብዙ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ደም በከንቱ እንዲፈስ እየተደረገ ነው።በእርግጥ የዚህ የማይመስል ዓላማ ተቀባይነት በማግኘት ከቶውንም እንደማይሆን ሲታይ ትግራይ ውስጥ የሽብር ተግባር የሚያካሂደው ቡድን የተወሰነ አካሉን “የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ” (ኢሕዲን) የተሰኘ ካባ በማልበስ ወደጐንደርና ወደወሎ የመሳብ ሙከራ ከጀመረ ውሎ አድሯል ። በቅርቡ ደግሞ ይባስ ብሎ በእራሱና “ኢሕዲን” በሚለው ፍጡሩ መካከል ስምምነት ላይ ተደርሶ “የጋራ ግንባር” ፈጥረናል ብሎ ለፍፏል ። “ግንባሩ” የሚመራበት “ፕሮግራም” ነው ብሎ ባወጣውም ውስጥ በተራ ቁጥር 13/ሀ/ የኤርትራን መገንጠል እንደሚደግፍ በግልፅ አመልክቷል ። ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል በሚመለከትም አቋሙ “ዋናው ቅራኔ የብሔር ቅራኔ ነው ።” በሚል ብሔረሰቦችን ማቃቃርና በዓላማ አንድነት የአብዮታቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው ።

በሌላ በኩልም ይሄው “ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ” (ሕወሐት) ነኝ የሚለው ቡድን ቀደም ሲል በሚያዝያ 1980 “ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ” (ሕግሐኤ) ወይም “ሻዕቢያ” ነኝ ከሚለው ቡድን ጋር ባወጡት መግለጫ ኤርትራ እንድትገነጠልና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ ብሔረሰቦች ደግሞ በየራሳቸው ጠባብ አቋም እንዲሰለፉ ለማድረግ የሚታገሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል ። በዚሁ መግለጫ ላይ “ሕወሐት” ነኝ ባዩ እራሱን የኤርትራን መገንጠል ደጋፊ የሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካይ አስመስሎ አቅርቧል ።

እነዚህ ቡድኖች በቅርጻቸውና ከየራሳቸው ጠባብ ፍላጐት አንፃር ልዩነት ሊኖራቸው ቢችልም በመሠረታዊ ዓላማቸው አንድ ናቸው ። ይሄውም በተለየ

አቀራረብ የኢትዮጵያን አንድነት ለመናድ መረባረብ ነው ። በራሳቸው አቅም የተቻላቸውን ያህል ጥፋት ከመፈጸማቸውም ሌላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን በእራሱ እንዲታገል ይገፋፋሉ ። እነሱው ሰላምን እየወከሉና የሀገርን ኢኮኖሚ እያደቀቁ መልሰው ሕዝብን "ለችግር ተዳረክ" ብለው ያፌዛሉ ። በአንድ በኩል በሕዝብ ጥቅም ላይ ጦርነት እየከፈቱ በሌላ በኩል ሕዝቡ እንዳይቋቋማቸው "ለጦርነት ለምን ትዳረጋለህ" ብለው ያዘኑለት ለመምሰል ይሞክራሉ ።

እነርሱም ምንም ሊሉና የሚቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ ላይመለሱ ይችላሉ ፡፡ ወሳኙ ግን ያለጥርጥር ሕዝብ ነው ። የእነርሱም ብርታት ከተለያዩ ፀረ አብዮትና ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ከሚያገኙት ድጋፍ ሌላ ሕዝብን ከማዘናጋ ትም ጭምር የሚመነጭ ነው፡፡ ዋንኛ ዐራቸው ማንነታቸውን ሕዝብ ጠልቆ መረዳት መቻሉ ነው ። ይህ የሕዝብ ግንዛቤ እየዳበረ የመጣ ሲሆን ቀድሞ በፊውዳሉ አገዛዝ ዘመን ተቃውሞ ተቀስቅሶ ከነበረበት የኤርትራ ቆላ በትርቡ በኢትዮጵያዊነት በመጽናት ለክልሉ የራስገዝ ደረጃ ይሰጠው ዘንድ ለጓድ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያም የቀረበው ጥያቄም በባሕርዩ የሕዝብን ፍላጐት የሚያንፀባርቅ እንደሆነ መገመት አያዳግትም ። ጥያቄው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና በአጠቃላይ በሕዝብ ፍላጐት መሠረት ለክልሉ ችግር በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ ማስገኘት እንደሚቻል እምነት ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው ፡፡ ይህ እምነት እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢ መልስ ከማስገኘት ሌላ ዓላማ የሌለው እንደመሆኑ በሰላም አግባብ ያለው ውጤት ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ ዛሬ የሦስተኛው ዓለም ወይም የታዳጊ አገሮች ክስተት እንጂ በዕድገት በገፉት ሀገሮች ጊዜ ያለፈበት ጉዳይ ከሆነ ቆይቷል ፡፡ በእርግጥ በዕድገት በገፉት ሀገሮች ውስጥም ሆነ በመካከላቸው ቅራኔ የለም ወይም አብቅቷል ማለት አይደለም ፡፡ ነገር ግን የቅራኔ አፈታት ሥልታቸው በአብዛኛው መሥዋዕትነቱ በቀለለ በሰላማዊ መንገድ በመሆኑ የከፋ ጉዳት አያደርስም ፡፡ የታዳጊ ሀገር ሕዝቦችም ያለጥርጥር ምርጫቸው ሰላም ነው ፡፡ በዚህ መንፈስ አብዮታችን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ላለው ችግር መፍትሔ ለማስገኘት በሰላማዊ መንገድም የተደረገው ጥረት በጣም ሰፊ ነው ። ይሁን እንጂ ተገንጣዮች ለተደረገው የሰላማዊ መፍትሔ ጥረት ሁሉ አፍራሽ ትርጉም በመስጠትና ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ሳይቀበሉ ቀርተዋል ፡፡ ይልቁንም "ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል"

እንደሚባለው የበለጠ ጥፋት እየፈጸሙ መልሰው በተለይ በውጪው ዓለም ለአብዮታችን የተዛባ ግምት ለማሰጠት ይሯሯጣሉ ። ነገር ግን እነርሱ እንደሚሉት ሳይሆን ባለፉት ዓመታት በተግባር እንደታየው የአብዮታችን ዓላማ ማኅበራዊ ዕድገት ማስገኘት ነው ። ለዚህ ዓላማው ተፈጻሚነት ደግሞ ያለጥርጥር መሠረታዊ ዋስትና ሰላም ነው ። ስለዚህ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ በየሉበት ለአብዮታችን የሰላምና የዕድገት ዓላማ ተግባራዊነት የኀብረት ጥረታቸውን ማጠናከራቸው አጅግ አስፈላጊ ነው ።



7. See, Mschvenieradze V. Op. Cit. PP. 214-219.
8. See, *Social Psychology and Propaganda*. Op. Cit. P.219.
9. Ibid., P.212.
10. የዘመኑ የርዕዮተዓለም ትግል (ሶፊያ ፡ የፓርቲ ሕትመት ፡ 1985 ቡልጋሪያኛ) ገጽ 448 – 449.
11. See, Volkogonov D., Op. Cit. pp. 96-97.
12. የዘመኑ የርዕዮተዓለም ትግል ፡ ገጽ 450; See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. PP. 212 - 213.
13. See, Volkogonov D. Op. Cit. P.138.
14. Ibid. P. 147.
15. Ibid. P. 125.
16. See Mshvenieradze V. Op. Cit., P. 219; See, *Political Terrorism*, (Moscow: Progress Publishers, 1983), PP. 260-268.
17. See, Paul M.A Linevarger, *Psychological War*, (Washington Infantry Journal Press, 1948;) See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. PP. 217-218; See, *Great Soviet Encyclopedia*, Vol. 21, P.269.
18. See, Mshvenieradze V. Op. Cit. 235; *International Encyclopedia of Social Sciences*, Vol. 13, P.49. See Harry Could, *Marxist Glossary*, (San Francisco: Proletarian Publisher, 1948) P. 73.
19. See, *Scientific Communism*, (Moscow: Progress Publishers, 1982) P. 325; Volkogonov D.
20. See, Volkogonov D.Op. Cit. P.99.
21. መሠረታዊ ወታደራዊ ስያሜዎች መፍቻ — መዝገበ ቃላት (ሞስኮ ፡ ወታደራዊ ሕትመት፣ 1965)
22. See, Volkogonov D. Op. Cit. P. 106.
23. See, Volkogonov D. Op. Cit. P. 107.
24. Ibid., P. 111.
25. See, *Social Psychology and Propaganda*, Op. Cit. P. 200.
26. የኮሚኒስታዊ ትምህርት መዝገበ ቃላት ፡ ገጽ 124
27. V.I.Lenin Collected Works, Vol. 20, P. 260.



የድኅረ-ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ

ከበላይነህ አሰጉ

በምሥራቅ ኢትዮጵያ የመንደር ምሥረታ እንቅስቃሴ የተጀመረው በየካቲት ወር 1977 ነው ። የመንደር ምሥረታው በተፋፋመ ሁኔታ ተካሂዶ አብዛኞዎቹ በተለይ በግብርና በሚተዳደሩት አካባቢዎች የተመሠረቱት መንደሮች በ1977 እና በ1978 በተካሄዱት ሁለት ዙር ዘመቻዎች የተጠናቀቁ ናቸው ። በዚህም መሠረት ከየካቲት 1977 እስከ መጋቢት 30 1980 ባለው ጊዜ በስምንቱ ደጋማ አውራጃዎች ፡ በ34 ወረዳዎች ፡ ቀድሞ የነበሩ 12,394 መንደሮች በ3,686 አዳዲስ መንደሮች ተሰባስበዋል ። በእነዚህ መንደሮች 502,834 ቤቶች ተሠርተው 526,093 አባወራና 2,055,830 ቤተሰብ በድምሩ 2,581,923 ገበሬዎች በመንደር ተሰባስበዋል ። *

ገበሬው በመንደር የተሰባሰበው ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎችን ማግኘት እንዲችል የአኗኗሩን ሁኔታ ማመቻቸት መሆኑ ይታወቃል ። ከዚህ አኳያ እስካሁን ባለው ጊዜ የሚታየው የለውጥ አዝማሚያ ምን ይመስላል? የገበሬው ሕይወት እየተለወጠ ነው ወይ? ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የክልሉን ሁኔታ እንቃኛለን ። በእርግጥ ሁለትና ሦስት ዓመት ብዙ ለውጥ የሚጠበቅበት ጊዜ አይደለም ። አንዳንድ የዕድገት ፍንጭ ለማየት የማያስችል ነው ማለትም አይቻልም ። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከመሞከራችን በፊት እስኪ በብሔራዊ የመንደር ምሥረታ ኮሚቴ የተገለጹትን የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም ዓላማዎች እንመልከት ።

የመንደር ምሥረታ ዓላማዎች

1. ለገጠሩ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎት

---

* የሐረርጌ ገበሬ ከትናንት እስከ ዛሬ ፡ ከላይ የተጠቀሰው ፡ ገጽ 35.

ሰጪ ድርጅቶችን በየአካባቢው እንዲደራጁና ኅብረተሰቡም እንዲጠቀምባቸው ለማድረግ ፡

2. የገጠሩ ሕዝብ አብሮ እየኖረ በኅብረት የመሥራት ባህሉን እንዲያዳብር ለማስቻልና ችግሮቹን በአካባቢው ለመፍታት በራስ የመተማመን ስሜቱን ለማጉልበት ፡

3. የገጠሩ ሕዝብ ለንቃተ ኅሊናው መዳበር ከሚያስተምሩት አካሎች ጋር ለሚኖረው ግንኙነት አመች ሁኔታ ለመፍጠር በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ፡ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፉን ለማረጋገጥ ፡

4. ለአካባቢ ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ለግልም ሆነ ለጋራ ንብረት መጠበቅ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ፡

5. መሬትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋልና የተፈጥሮ ሀብት ልማትንና ጥበቃን በተሻለ መንገድ ለመምራት ፡

6. የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግና የገጠሩን ኑሮ ለመለወጥ ፡ ገበሬው ከሳይንሳዊ አሠራር ዘዴዎችና ከቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር የሚተዋወቅበትን ሁኔታ ለመፍጠር ፡

7. ገበሬው በግል መፈጸም የማይችላቸውን እንደ መንገድና የግድብ ሥራ የመሳሰሉትን የመሠረተ ልማት ሥራዎች በጋራ እንዲያከናውንና እንዲጠቀምባቸው ለማድረግ ፡

8. በገጠርና በከተሞች መካከል ከብዝበዛ ነፃ የሆነና የተስተካከለ የሸቀጥ ልውውጥ ሥርዓት የሚሰፍንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንደሆነ ስለመንደር ምሥረታ የወጣው መመሪያ ይገልጻል ።

በእርግጥ ስለመንደር ምሥረታ ዝርዝር መመሪያ የወጣውና ብሔራዊ የመንደር ምሥረታ ኮሚቴ የተቋቋመውም በሐረርጌ የመንደር ምሥረታው እንቅስቃሴ በአብዛኛው ከተገባደደ በኋላ ነው ። ይሁን እንጂ ክፍለ ሀገሩ ራሱ በዚህ ቅደም ተከተልና አገላለጽ አይሁን እንጂ መንደር መመሥረት ሲጀምር የነደፈው ዓላማ ነበር ። በክፍለ ሀገሩ የተከናወነው የመንደር ምሥረታ ዓላማም የገበሬውን ኢኮኖሚያዊ ፡ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት መለወጥ ነበር። የመንደር ምሥረታ ብሔራዊ ኮሚቴ ከተቋቋመና አንድ ወጥ መመሪያ ካወጣ ወዲህ የመንደር ምሥረታው እንቅስቃሴ መከናወን የጀመረውና በመከናወን ላይ ያለውም ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሚያስችል ሥልትና ዕቅድ ነው ። ቀድሞ የተመሠረቱትም ቢሆን ዕድገታቸው የሚመዘነው እነዚህን ዓላማዎች እውን ለማድረግ በሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው ። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም አንድ ሁለት ብሎም ባይሆን እነዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የሐረርጌ መንደር ምሥረታ ያስገኘውን ጠቀሜታና መሻሻል አለባቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች መጠቆም ይሞክራል ።

የገበሬው ሕይወት ከማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በበለጠ ለአካባቢ ተጽዕኖ በተለይ ለመሬት ይዞታና አጠቃቀም የተጋለጠ ነው ። በመሬት በአግባቡ መጠቀምና አለመጠቀም ሕይወቱ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል ። ቀድሞ በነበረው መልክ ተበታትኖ ሲኖር የእርሻ ቦታው ፡ የመኖሪያው ፡ የደኑና የግጦሹ ተለይቶ ስለማይታወቅ የእርሻው ማሳ ሰብሉ ሲነሣ ለግጦሽ ይውላል ፡ ደኑ ውስጥ ከብት ይለቀቃል ፡ ከብቱ ሳሩን እስከመጨረሻ ሲግጥና ሲረጋግጥ አዳዲስ ብቅ ብቅ የሚሉ ዛፎች ሲሰባበሩ ደኑ ይራቆታል ። መሬቱም ለአፈር መሸርሸር ይጋለጣል ። ለእነዚህ ጠቀሜታዎች ተለይቶ የሚታወቅ ክልልም አልነበረም ።

ዛሬ ግን ሁኔታው ይህ አይደለም ። በገለምሶ ፡ ሂርናና ኩምቦልቻ ባደረግነው ቅኝት ልዩነት አይተናል ። በወጣ ገባው ደጋማ አካባቢ በየተራራና ኮረብታው ጥግ ችምችም ያለው መንደር ጨረቃ መስሎ ፡ ከበላዩ ያለው ከፍታ ሥፍራ አረንጓዴ ደን ለብሶ ፡ ከፊት ለፊት ያለው ሜዳማ ቦታ በበቆሎና ማሽላ ሰብል ተሸፍኖ ፡ ወንዛወንዝና ረግረግ ቦታዎች ከብቶች ተለቀውባቸው ሲታይ የገጠሩን ውበት ማድነቅ ግድ ይሆናል ። ገና መንደር ሲመሠረት ከመንደር ፋይዳዎች አንዱ በተፈጥሮ አካባቢ በዕቅድ ለመጠቀም ተብሎ ሲነገር ጠቀሜታውን ከመገመት ባሻገር ውበቱን መገመት አስቸጋሪ ነበር ። በተለይ በበጋው ወቅት አካባቢው ሁሉ ደርቆ ፡ አፈሩ ተጋልጦ ሲታይ ከመንደሩ አሠራር በቀር ክልሉ የሚደነቅበት ነገር ነበር ለማለት ያዳግታል ።

ተጣቦ ለሚኖረው የሐረርጌ ደጋማ አውራጃዎች ገበሬ ባላቸው መሬት በዕቅድና በሥርዓት ከመጠቀም ፡ አፈሩ እንዳይሸረሸር ፡ የተመናመነው ደን እንዳያልቅ ከመንከባከብ ሌላ አማራጭ አልነበረውም ።

በደን ልማቱ በኩል ሐረርጌን በአርአያነት ከሚታዩ ክፍላተ ሀገር ውስጥ መመደብ ይቻላል ። በዕድገት በኅብረት ጊዜና በ1971 የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ወቅት ተጀምሮ ተራሮችን ደን ለማልበስ የተደረገው ጥረት በመንደር ምሥረታው ተጠናክሮ ቀጥሏል ። በአሁኑ ወቅት በየትኛውም ደጋማ አውራጃና ወረዳ ሲዘዋወሩ መጠኑ ይብዛ ይነስ እንጂ የደን ልማት የሌለበት የለም ማለት ይቻላል ። ከሸዋ ወደ ሐረር ሲሄዱ አሰበ ተፈሪ ከተማ እንደደረሱ አጠገቡ ያለውን ተራራ ማየት ለደኑ ልማት እንቅስቃሴ ማስረጃ አንድ ብሎ ይጀመራል። ከዚያ በኋላ በፈለጉት አቅጣጫ ወደ አውራጃዎችና ወረዳዎች ከተጓዙ የእያንዳንዱ ተራራ አናት አረንጓዴ እየለበሰ መሆኑን መመስከር ይቻላል ።

ከነዚህ መካከል በከፍተኛ ደረጃ በወበራ አውራጃ ፡ በሜታ ወረዳ ፡ በግብርና ልማት የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ዘርፍ የሚካሄደውን የላይኛው ሁርሶ ተፋሰስ ፕሮጀክት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ። ከአዲስ አበባ ቁልቢ ሊገቡ ጥቂት ሲቀር ጥቅጥቅ ባለ የባሕርዛፍ ደን ውስጥ ይታለፋል ። ትንሽ እንደሄዱም በስተግራ በኩል ወዳለች አንዲት ኮረብታ የሚያስወጣ ግራቀኝ በመቃ የታጠረች ቀጭን መንገድ አለች ። የመንገዷ ግራና ቀኝ በዛፍ ተሞልቷል ። ጠይቆ የመረዳት ልምድ የሌለው ሰው ምናልባት መናፈሻ ይሆናል ብሎ ያልፋል ። በዚያ አካባቢ የዚያ ዓይነት መናፈሻ ይኖራል ብሎ መገመት ያዳግታል። ካለው የሕዝብ ብዛት አኳያ ሲታይ ።

መናፈሻው ውስጥ የገባ ቁም ነገር ታዝቦ ይወጣል ። በተለያዩ ወቅቶች የጎበኙት ሰዎች የተከሉት ዛፍ ትልልቅ ሆኖ አጠገባቸው በቆርቆሮ ላይ የተካዮቹ ስም ተጽፏል። መሀል ላይ አንዲት ጎጆ አለች ። እውስጧ ልዩ ልዩ ቻርቶች ይታያሉ ።

የፕሮጀክቱ ዓላማ ፡ የተጀመረበት ጊዜ ፡ እስካሁን ያከናወነው ተግባርና ያጋጠሙ ችግሮች በእነዚህ ቻርቶች ላይ ተዘርዝረዋል ።

የላይኛው ሁርሶ ተፋሰስ ፕሮጀክት የተ

ጀመረው በ1973 ነው ። የፕሮጀክቱ ሥራ የሚካሄደው በግብርና ልማትና በዓለም የምግብ ድርጅት ነው ። የግብርና ልማት የቴክኒኩን ሥራ ሲያከናውን የዓለም ምግብ ድርጅት ለጉልበት ሥራ የሚከፈል ምግብ ያቀርባል ። የፕሮጀክቱ ክልል 11.800 ሄክታር ሲሆን ፤ በክልሉ 15 ገበሬ ማኅበራት ይገኛሉ ። መሬቱ ገደላማ በመሆኑና ባለመጠበቁ በአብዛኛው ተጎድቷል ። በዚህ ላይ የአንድ ቤተሰብ የእርሻ ይዞታ 0.6 ሄክታር በመሆኑ ከፍተኛ የእርሻ መሬት ማነስ አለ ። የደን ምንጣሮው ፣ ቃጠሎው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመምጣቱ ሁኔታው ካልተገታ ውጤቱ አስከፊ እንደሚሆን ታመነበት ። ለዚህ ነው ይህ ፕሮጀክት ሊጀመር የቻለው ።

የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ የአፈር መሸርሸርን ፣ የመሬት አጠቃቀምና የተፈጥሮ ዝናብ ብክነትን በመቆጣጠር የተጎዳውን መሬት እንዲያገግም ማድረግ ነው ። ለዚህ ተግባር በቅድሚያ አፈሩን ለመከላከል እርከን እየተሠራ ነው ። የእርከን ሥራው በተጠናቀቀባቸው ክልሎች ችግኝ እየተተከለ ተራራውና ሸንተረሩ ደን እየለበሰ ነው ።

በዚህ መልክ መሬቱ ተጠብቆ አፈሩ በዝናብ ውሃ መታጠቡ ካቆመ በኋላ ወይ ድሬዳዋ ባለው ሜዳማ ቦታ አናት ላይ ግድብ ይሠራና የእርሻ ልማት ይጀመራል ። ይህ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ተግባራዊ እስኪሆን ከወዲሁ የተሠሩ ሥራዎች እንኳን አመርቂ ውጤት እያስገኙ ነው ። በፕሮጀክቱ ዕድሜ 11.593.350 የልዩ ልዩ ዛፍ ችግኞች በአብዛኛው ባሕርዛፍ ተተክሏል ። በመንገዱ ግራ ቀኝና በተለይ ኩረብታው ላይ ወጥተው ሲመለከቱ የዚህ ውጤት በጉልህ ይታያል ። በ1980 ብቻ 1.800.000 ችግኝ ተተክሏል ። ቀደም ሲል የተተከለው ባሕርዛፍና ለየገበሬው የታደለው የፍራፍሬ ዛፍ ደርሶ ለጥቅም መዋል መጀመሩ ገበሬውን አበረታትቶታል ። በአዲስ ደን ውስጥ ሳር በቅሏል ። ይህንን ለምለም ሳር ገበሬው በነፃ አጭዶ እንዲጠቀም ማድረጉም ገበሬውን ደኑ ለራሱ ጥቅም የለማ አድርጎ እንዲንከባከብ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ ነው ።

ለገበሬው ቀጥተኛ ጠቀሜታ የሚሰጡ ተግባራትም በፕሮጀክቱ ይከናወናሉ ። የገጠር መንገድ ሥራ ፣ ኩሬዎችን በማጉልበት ለመጠጥና ለከብቶች ማዘጋጀት ፣ ሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎችን ማቋቋም ፣ ለከብት መኖ የሚሆኑ የልዩ ልዩ ሳር ዝርያዎችን አራብቶ ለገበሬው ማደል አንዳንዶቹ ናቸው ።

ከነዚህ አንዱ ለጋምቤላ ገበሬ መንደር የገባው የውሃ ቧምቧ ነው ። ጋምቤላ ገበሬ መንደር ከመንገዱ 5 ኪሎ ሜትር ርቆ ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ መንደር ነው ። ከመንደሩ ወደ ቁልቢ ለመምጣት ቀጥ ያለ ዳገት ነው ። በአካባቢው ወራጅ ውሃም ሆነ ምንጭ የለም ፤ በክረምት እንጂ ። በበጋ ውሃ የሚቀዱት ዳገቱን ወጥተው ከመንገድ ዳር ከምትገኝ አንዲት ምንጭ ነበር ። በወቅቱ ያን 5 ኪሎ ሜትር ዳገት ወጥቶ ውሃ መቅዳት ከሚያስከትለው ድካም ባሻገር ምንጯ ላለችበት መሬት ባለቤት ለበጋ ውሃ ማሸላ ይገብሩ እንደነበር ማወቅ ተችሏል ። በችግሩ የተነጣ ይገኛቹ ሴት ልጆቻቸውን ለሚስትነት ሲጠየቁ ለጋምቤላ አካባቢ ወንድ አይድሩ እንደነበረ ይነገራል ። ገላ መታጠብ የሚቻለው በክረምት ብቻ ነበር ይባላል ።

ዛሬ ግን ሁኔታው ተቀይሯል ። ይህቺው ምንጭ ተገንብታ በቧምቧ የተወሰነ ርቀት ትሄድና 30,000 ሊትር ማጠራቀም የሚችል ገንዳ ውስጥ ትጠራቀማለች ። ከዚያ አምስቱን ኪሎ ሜትር በቧምቧ ትወርድና ለሦስት መንደሮች በቢርካ ትታደላለች ።

ቧንቧውን ተከትሎ የገጠር መንገድ ተሠርቷል ። የጋምቤላ ገበሬ በዕውን የሕይወት ተሐድሶ አግኝቷል ።

ገበሬው በመንደር በመሰባሰቡም እንደ ቀድሞው በፈለገበት አቅጣጫ እየሄደ ደን መመንጠሩ ቆሟል ። ጥቅሙንም በተጨባጭ እያየው ነው ። በዚህ መልክ በተለያየ ቦታ የተጀመሩት የደን ልማት ፕሮጀክቶች የሚያበረታቱና ተስፋ የሚሰጡ ናቸው ። ይህ ሲባል ግን በአንዳንድ ቦታ በአየሩ (በዝናብ) ችግርም ይሁን ከዘሩ በርካታ ያደገ ጥድ በተለይ የውጭ ዘር ደርቆ መታየቱ ተጠንቶ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ ሆኖ ታይቷል ። በደን ምንጣሮውም በኩል ወደ አጋዴን መንገድ ያለውን የግራር ቁጥቋጦ እየመነጠሩ ከሰል ማክሰሉ ፤ በጨርጨር አውራጃ የተመነጠረውን ደን እንደገና ለማልማት ብርቱ ጥረት እየተደረገ በተቃራኒው በአሰቦት ተራራ ያለውን የተፈጥሮ የጥድ ደን እየመነጠሩ በየመንገዱ ዳር የሚሸጡ ሰዎች በብዛት መታየታቸው ከወዲሁ ካልተገታ የጠፋውን ስናለማ ያለውን የሚያጠፋ ቀበኛ እየተበራከተ ስለሚሄድ ሊታሰብበት ይገባል ።

በሐረርጌ ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚደርሰው የእርሻ መሬት በጣም አነስተኛ መሆኑ ተጠቅሷል ። ይህቹኑ መሬት በዕቅድ ተጠቅሞ ምርትን ለማሳደግ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር ያለው አማራጭ አንድን ማሳ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ከማረስ አልፎ ከአንድ ጊዜ በላይ ምርት እንዲሰጥ ማድረጉ ነው ። በክፍለ ሀገሩ ያለው የዝናብ ሁኔታ ለዚህ አያመችም ። ያለው አማራጭ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ነው ። በሐረርጌ በመስኖ ሊለማ የሚችል 40,000 ሄክታር መሬት እንዳለ ሲገመት ከዚህ ውስጥ እስካሁን የለማው 15,915 ሄክታር ብቻ ነው ።* ሁኔታውን ለማሻሻልና ምርትን ለመጨመር በቀጣና ግብርና ልማትና በዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች አማካይነት በአሁኑ ወቅት ከ1,520 ሄክታር በላይ ማልማት የሚችሉ የበርካታ ትናንሽ ግድቦች ሥራ እየተካሄደ ነው ። **

በዚህ በኩል በመከናወን ላይ ካሉት ተግባራት ሁለቱን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል ። ከጂጂጋ ምሥራቅ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚከናወነው የኤልባይህ የግድብ ሥራ ፕሮጀክት አንዱ ነው ። የፕሮጀክቱ ዓላማ የኤልባይህን ሸለቆ በመስኖ ማልማት ነው ። ግድቡ የሚሠራው በአፈር ሲሆን ሥራው የሚካሄደው በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ነው ። ይህ 12.000.000 ብር ይፈጃል ተብሎ የተገመተው ግድብ ሲጠናቀቅ 7,000,000 ሜትሪክ ኩብ ውሃ ሊይዝ ይችላል ። ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ 500 ሄክታር መሬት በመስኖ ለማልማት ይቻላል ።

ሌላው የቢዮ ግድብ ሥራ ፕሮጀክት ነው ። ይህ በግብርና ሚ ር የገጠር መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ዘርፍና በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም አማካይነት ከጣሊያን መንግሥት ጋር በመተባበር የሚ

* የሐረርጌ ገበሬ ከትናንት እስከ ዛሬ ፣ ከላይ የተጠቀሰው ፤ ገጽ 24.

** ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 26.

ሥራው የግድብ ፕሮጀክት ከጂጂጋ 15 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው ። ግድቡ ሲጠናቀቅ 1.3 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ይይዛል ። በዚህ ውሃ 168 ሄክታር መሬት ማልማት ይቻላል ።

እነዚህ ሁለቱም ግድቦች የሚያጠራቅሙት ውሃ የሚገኘው ከወንዝ ወይም ከምንጭ አይደለም ። በአካባቢው የሚዘንበው ዝናብ ከሚወርድበት ሥፍራ የሚቋጥሩት ነው ። አካባቢውን በዓይን ሲቃኙ የተባለውን ያህል ውሃ የሚያስገኝ ጉርፍ ይመጣል ለማለት ያስቸግራል ። ግን በቢዮ ግድብ አንድ ቀን ለአሥራ አምስት ደቂቃ ከዘነበ ዝናብ የተጠራቀመ ነው ብለው ያሳዩን መጠን ወዲያው ሐሳባችንን አስቀየረ ። ሥራው ጨርሶ በአካባቢው ያልተለመደ ነው ማለትም አይደለም ። አሁን በባለሙያ ተጠንቶ በሰፊው ተያዘ እንጂ በሁለቱም ቦታዎች የአካባቢው ነዋሪ ከጥንት ጀምሮ ትንንሽ ኩሬዎች እየቆፈረ ለበጋ ውሃ ያጠራቅማል ። እንዲያውም አንዳንዱ ሀብት ያለው ግለሰብ በድንጋይ ዙሪያውን ገንብቶ ውስጡን በሲሚንቶ ሊሾ ያደርግና የዝናብ ውሃ በቦይ ወይቢያ እንዲገባ አድርጎ ያጠራቅማል ። እንዲህ ዓይነት ማጠራቀሚያ የሠራ ግለሰብ የማይነጥፍ ለም አገኘ ማለት ነው ። በአንድ ግለሰብ አባባል "ነዳጅ አገኘ" ማለት ነው ። ግንቧ በቁልፍ ትጠበቃለች ። በጋው ሲመጣ እያንዳንዱ ሰው በውድ ዋጋ በስፍር ይገዛል ። ለከብትማ ከየት ተገኝቶ ። ጂጂጋ አካባቢ በበጋው አንድ ከብት አንድ ጊዜ ለማጠጣት ሃያ አምስት ሣንቲም ድረስ የሚከፈልበት ጊዜ አለ ። የዚህ አካባቢ ገበሬ በመጠነኛ እርሻና በከብት እርባታ የሚኖር ነው ። በአሁኑ ወቅት የአካባቢው ገበሬ በመንደር ተሰባስቧል ። ሁሌ የሚያንሣው ችግር የውሃ ነው ። በጋ በመጣ ቁጥር ከብቶቹን ይዞ መንከራተት ነው ። በአካባቢው መጠነኛ እርሻ አለ። ዝናብ በጥሩ መጠን በተገኘ ዘመን ደህና ሰብል ያገኛል ። ብዙውን ጊዜ ግን የዝናቡ መጠንም ሆነ ወቅቱ አስተማማኝ አይደለም ። በመሆኑም ገበሬው በሕይወቱ የሚመኘው ነገር ቢኖር የማያቋርጥ የውሃ ምንጭ ማግኘት ነው ። ኤልባይህና ቢዮ ለዚህ ምላሽ እንዲሰጡ የታቀዱ ናቸው። ከነዚህ ግድቦች በሚገኝ ውሃ አካባቢውን በመስኖ እያለሙ ገበሬውን አትክልትና ፍራፍሬ እንዲተክል ማስለመድና ለከብቱም ውሃ ማስገኘት አንድ እርምጃ ወደፊት ነው ። ቀንድ ብቻ እየቆጠሩ ብዙም ዋጋ የማያወጡ ከብቶችን ይዞ ከመንከራተት ወደ ዘመናዊ እርባታ ለማሸጋገርም በር ይከፍታል ። ሌሎች በአቅራቢያው ያሉ አካባቢዎችም የእነዚህን ግድቦች ውጤትና ለእነሱም ሊደርስ የሚችለውን የነገውን ተስፋ በጉጉት እያሰቡት ነው ። የግድቦቹ እሴት በሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ብቻ የሚለካ ሳይሆን የአካባቢውን ገበሬ በአንድ ቦታ ተረጋግቶ እንዲኖር የማድረጉ ሥነ ልቦናዊ ፋይዳም በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

ኤልባይህና ቢዮ ገና በመሠራት ላይ ያሉና ለክርሞ ለፍሬ እንደሚበቁ የሚታሰቡ ናቸው ። ሌሎች በርከት ያሉ ትናንሽ የመስኖ ፕሮጀክቶች ፍሬ አስገኝተዋል ። ከእነዚህ አንዱ በሀብሮ አውራጃ ፣ ቁኒ ወረዳ የሚገኘው የቡርቃ መስኖ ፕሮጀክት ነው ። ይህ ፕሮጀክት ከሐጂዲን ምንጭ የሚወጣውን የሚዳግዱን ወንዝ በመጥለፍ 160 ሄክታር ለማልማት የታቀደ ፕሮጀክት ነው ። በግብርና የገጠር መሠረተ ልማትና በአካባቢው ሕዝብ ትብብር የተሠራው ይህ ፕሮጀክት የወልዲያ ተኩማ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበርን እርሻ ያለማል ። በአምራቾች ያልተጠቃለሉ ገበሬዎችም ተጠቅመውበታል ።

በአካባቢው የ1979 — 80 የበልግ ዝናብ በማነሱ የብዙው ገበሬ በቆሎ ደርቆ ነበር ። በዚህ ፕሮጀክት የሚጠቀመው ክልል ግን ከምንጊዜውም የተሻለ ሰብል ነው ያገኘው ። የመኸሩም ዝናብ ዘግይቶ ስለመጣ የሌላው ገበሬ እርሻ ዘግየት ብሎ ሲዘራ በዚህ ክልል ጤፉ በወቅቱ ሊዘራ የቻለው ፕሮጀክቱ በመኖሩ ነው ።

የወልዲያ ተኩማ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በዚሁ መስኖ የአትክልት እርሻ ጀምሮ በአንድ ዓመት 20,000 ብር ገቢ አግኝቷል ። የአካባቢው ገበሬ ለእርሻ ሊውል በማይችል ክልል በመንደር በመሰባሰቡና ሜዳማው ስፍራ ለእርሻ በመተው የመስኖው ፕሮጀክት አመርቂ ውጤት እያሳየ ነው ። የእዚህ ግድብ መጠን ትንሽ ከተጨመረ የበለጠ ለማልማት የሚያስችል በቂ ውሃ አለው ።

በግድብና በወንዝ ጠለፋ ከሚከናወነው ባሻገር የውሃ መሳቢያ ፓምፕ በማስገባት የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴም ከትናንትናው የገበሬ እርሻ ጋር ሲነፃፀር ብዙ ሊባልለት የሚያስችል ነው ። በዚህ መልክ በ6 አውራጃዎች ፣ በ14 ወረዳዎች 142 የውሃ ፓምፖች ተተክለው ፣ 17,724 ገበሬዎች የሚጠቀሙበት 2,607.5* ሄክታር መሬት በመስኖ እየለማ ነው ። በመንደር ምሥረታው ሳቢያ ገበሬውን ለምርት ዕድገት በማንቀሳቀስ ጉልበቱንና ገንዘቡን አቀነባብሮ የተሠራው የልማት ሥራ ቀላል አይደለም ። ጥረቱ ይበል የሚያሰኝ ነው ።

በመስኖ ከመጠቀሙ ጐን በክፍለ ሀገሩ ለገጠሩ ነዋሪ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለማዳረስ የተደረገው ጥረትም ቀላል አይደለም ። የገጠሩ ሕዝብ በመንደር በመሰባሰቡ ምንጭ በማጐልበት ፣ በቧምቧ በመሳብ ፣ ጥልቅ ጉድጓዶችን በመቆፈር ፣ ከጣሪያ ላይ ውሃ በማጠራቀም በርካታ የገጠሩ ነዋሪ ንፁህ ውሃ እንዲያገኝ ተደርጓል ። ቀድሞ ኅብረተሰቡ ተበታትኖ ይኖር በነበረ ጊዜ አልፎ አልፎ የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች ቢኖሩም በርቀት የተነሣ ሊጠቀም የሚችለው የሕዝብ ቁጥር ያነሰ ነበር ። በአጠቃቀም ረገድ የቅርብ ክትትል ስለማይደረግ የመበላሸት ዕድሉም ከፍ ያለ ነበር ። በአሁኑ ወቅት ግን የውሃው ጉድጓድ የሚቆፈረው ፣ ቢርካው የሚሠራው ፣ ቧምቧው የሚገባው እመንደር ውስጥ በመሆኑ ከነዋሪው እይታ ውጭ አይደለም ። ርቀቱም ብዙ ስለማይለያይ ጠቅላላው የመንደር ነዋሪ በእማካይ መጠቀም ይችላል ።

በውሃ አቅርቦት በኩል ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል ። ከጂጂጋ ወደ ቆላው በማንኛውም አቅጣጫ የሄደ ሰው የውሃ ችግር በጉልህ ያያል ። ወራጅ ወንዝ ስለሌለ ውሃ የሚገኘው አንዳንድ አካባቢ ከተቆፈሩ ኤላዎች ** ነው ። ውሃ የማምጣት ድርሻ የተጣለባቸው ሴቶችና ሕፃናት ከሩቅ መንገድ በአህያ ጭኖ ማመላለስ እጅግ አድካሚና አሰልቺ ነው ። በዚያ ላይ ኤላው በከብት ስለሚረጋገጥና ውሃውም አንድ ቦታ ተጠራቅሞ ስለሚቆይ እጅግ ቆሻሻ ነው ። ከጂጂጋ ወደ ጭናቅሰን መንገድ ሲኬድ ወደ ቀኝ ታጥፎ አንድ መረር የሚባል ሸለቆ አለ ። ወደ ቱርአኖድ ገበሬ

---

* የሐረርጌ ገበሬ ከትናንት እስከ ዛሬ ፣ ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 25·

** ኤላ በበጋ የሚሆን የዝናብ ውሃ የሚጠራቀምበት ኩሬ በክልሉ የሚጠራበት ቃል ነው ።

መንደር ለመሄድ ይህን ሸለቆ ስናቋርጥ የአካባቢውን የውሀ ችግር በጉልህ ተመለከትን ። ጥልቀቱ ሁለት ሜትር ገደማ የሚሆን አንድ ሰፊ ኩሬ ተቆፍሮ ውሃ ተጠራቅሟል ። በየተወሰነ ደረጃ መቆሚያ አለ ። ዙሪያውን አህዮች ተደርድረዋል ። ሴቶች ተቀምጠው ተራቸውን ይጠብቃሉ ። አንድ ሰው እየቀዳ ውሃ ያቀብላል ። ተረኛ ሴቶች እየተቀበሉ አህያቸው ላይ በተጫኑ ቀርበታ፣ ላስቲክ፣ ወይም ጀሪካን ይጨምራሉ። አንዳንዱ አመለኛ አህያ ውሃው እየተቀዳ ይሮጣል ፣ ይቁነጠነጣል ። ትግል ነው ። ይህን ሁሉ ችግር አልፈው ይዘው ሲሄዱ በተለያዩ እክሎች የውሃው መፋሰስ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም ችግር ነው ።

በዚህ ሁኔታ ይጠቀሙ ከነበሩ መንደሮች አንዱ የጌልቦብ ቀበሌ መንደር ነው ። የጌልቦብና ሌሎችም በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ቀደም ሲል በተለይ በበጋው ውሃ የሚያገኙት ከጅጅጋ ወይም ከመረር ነበር። እነዚህ ቦታዎች በ20 – 30 ኪሎ ሜትር ይርቃሉ ። የሚጠጣ ውሃ ፍለጋ ይህን ያህል መንገድ መጓዝ አድካሚነቱ ግልጽ ነው ። ዛሬ ግን የጌልቦብ ሁኔታ ተለውጧል ። በአካባቢው ለሦስት መንደሮች (ጌልቦብ ፣ መካኒሳ ኡባህ ፣ በባሌ) የሚያገለግል ጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሮ ውሃ ወጥቷል ። አንድ ማጠራቀሚያ ተሠርቶ ለሦስቱም መንደሮች መቅጃና ከብት ማጠጫ ለየብቻው ተሠርቷል ። የጌልቦብ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር የሆኑት ሐጂ ኢማም መሐመድ እንደገለፁት በዚያ መንደር ለውሃ ፍለጋ የነበረው መንከራተት ዛሬ ተረት እየሆነ ነው ።

በዝናብ እየወረደ ያለምንም ቁጥጥር ይፈስ የነበረውን የጎርፍ ውሃ ገድቦ በማቆየት በበጋ ወቅት መጠቀም አንዱ ዘዴ ሲሆን በሐረርጌ መንደር የተጀመረውና ምናልባትም ውሃ ለሌላቸው እንስተኛ ከተሞችም ሊጠቅም የሚችለው ሌላ ዘዴ ከቤት ጣሪያ ቆርቆሮ የሚፈሰውን ውሃ ማጠራቀም ነው ። ይህ ሲባል ቶሎ የሚታሰበን በበርሜል ፣ ወይም በሌላ መያዣ ማጠራቀሙ ይሆናል ። መጠኑም ቢሆን አስተማማኝ አለመሆኑ ይታየናል ። ሐረርጌ ገጠር ያየነው ግን ከዚህ ለየት ያለና በብዙ ቦታ መሞከርም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በወበራ አውራጃ ከደደር 6 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ለጋ ጨፌ የምትባል መንደር አለች ። አክስፋም በሚባል ድርጅት ድጋፍ የተሠሩ ብዙ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸው ሁኔታዎች ተመቻችተዋል ። የእርሻ መሣሪያዎች የሚሠሩበትና የሚጠገኑበት ሥፍራ፣ ለመንደሩ ነዋሪዎች የሚያገለግል በዲናሞ የሚሠራ የኤሌክትሪክ መብራት ፣ የአካባቢው ገበሬዎች አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበርና የክልሉ አኢሴማ ገቢውን በጋራ የሚጠቀሙበት የእህል ወፍጮ አለ ። እነዚህ አገልግሎቶች እንደሁኔታው በሌሎች መንደሮችም የሚታዩ ሲሆኑ ለየት ብሎ የተመለከትነው የውሃ ማጠራቀሚያው ጉዳይ ነው ። አስረጂአችን የውሃ ማጠራቀሚያችን ይህ ነው አለና አንድ ቤት መሰል ነገር አሳየን ። ከሱቁና ከእርሻ መሣሪያዎች መጠገኛ ቤት ጣሪያዎች ወደዚህ ቤት የተዘረጋ አሸንዳ ይታያል ። የቤቱ ግድግዳ በሲሚንቶ የተለሰነ ነው ። ላዩ ቆርቆሮ ለብሷል ። ከወደ ስሩ አንድ ቧምቧ ይወጣና የተወሰነ ርቀት ላይ መቅጃ ተበጅቶለታል ። ከጣሪያው አጠገብ ማስተንፈሻ ቧንቧ አለው ። ሲያዩት ቀላል ግን ብዙ ቦታ ያላየነው ነው ። ለመሆኑ ምን ያህል ውሃ ይይዛል አልናቸው ። 76,000 ሊትር ይይዛል አሉን ። ዝናብ ዘንቦ ውሃው እንዳይባክን ጥሩ ወጥመድ ነው ።

በዚህ መልክ በርካታ የንፁህ ውሃ ማግኛ ዘዴዎችን መጥቀስ ይቻላል ። ስለጠቀሜታውም አንዲት ፋጡማ አሊሾ የምትባል ባለትዳር ፣ የአንድ ልጅ እናትና በግምት የሃያ ዓመት ወጣት የምትሆን የነገረችን ጥሩ ማስረጃ ነው ። ፋጡማ በጨርጨር ፣ አዳልና ጋራ ጉራቻ አውራጃ ፣ በጩቢሌ ወረዳ የሚንሮ መንደር ነዋሪ ነች ። መንደሯ ከሂርና አሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች ። መንደሯ የተመሠረተችበት አካባቢ በጣም ገደላማና ወጣ ገባ ነው ። ቀደም ሲል ከ5 – 7 ኪሎ ሜትር ርቀት እየመጡ ውሃ የሚቀዱበት አንዲት ትንሽ ምንጭ አለች ። ምንጯ ያለችው ገደላማ ቦታ ላይ ስለሆነ መተላለፊያው አንድ ብቻ ነው ። ከብቱም ፣ ሰውም ፣ የሚጠጣውና የሚሻገረው በዚያችው ነው ። በአሁኑ ወቅት በቀይ መስቀል የማቴሪያል አቅርቦት ፣ በግብርና መሠረተ ልማት የቴክኒክ እርዳታና በገበሬው የጉልበት ሥራ ምንጯ በድንጋይና ሲሚንቶ ተሠርታ በቧምቧ ሜዳማ ቦታ እንድትወጣ ተደርጋለች ። ሜዳማው ቦታ ላይ የመጠጥ ውሃ መቅጃ ፣ የልብስ ማጠቢያና የከብቶች ማጠጫ ገንዳ ተለይቶ ተሠርቷል ።

ፋጡማን ያገኘናት ልብስ ስታጥብ ነው። እለፍ ብሎ ካለው ቧምቧ የ35 ዓመቷ ወ ሮ ስመኝ ታደሰ ውሃ ይቀዳሉ ። ስለ መንደሩና ቀድሞ ውሃ ያገኙ ስለነበረበት ሁኔታ ካነጋገርናቸው በኋላ የቀድሞውንና የአሁኑን የውሃ አጠቃቀም ልዩነት ፋጡማን ጠየቅናት ። ፋጡማ ቀና ብላ ፈገግ አለችና ፣ "እንዴት ትጠይቁኛላችሁ?" አለችን ። ግልጽ ነው በሚል መልክ ። ከዚያም በማከታተል "ድሮ የምንቀዳው ቅድም ካያችኋት ምንጭ ነበር ። ከብት የሚጠጣው እዚያችው ነበር ። እዚያው እግራችንን እንታጠባለን ። ልብስም የምናጥበው እዚያችው ነው ። አሁን ግን እንደምታዩት ሁሉም ተለይቶ ተሠርቶልናል ። ውሃውም በቧምቧ መጥቶ ስለሚፈስ አይደፈርስም" አለችንና እጥቧን ቀጠለች ።

ነገሩ ይኸው ነው ። ንፁህ የመጠጥ ውሃ ማግኘት ለጤና ያለው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም ። ብዙ የሆድ ውስጥ በሽታ የሚመጣው ከተበከለ ውሃ ነው ። በገጠርም ሆነ በከተማ ፣ በልዩ ልዩ የአንጀት በሽታ የሚሰቃዩ ሕፃናትንም ሆነ አዋቂዎችን ከችግሩ ለመገላገል አንዱ ንፁህ ውሃ የማዳረሱ ጉዳይ ነው ። ለዚህ በገጠሩ የመንደር ምሥረታው በፈጠረው አመቺ ሁኔታ የተጀመረው ጥረት ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ። ከዚሁ ጋር አብሮ ግን በብዙ ወጭና ልፋት የተቋቋሙ ቧምቧዎች በሥርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ስለእንክብካቤና ስለጥገና ማስተማሩም አብሮ መጠናከር ይኖርበታል ። አንዳንድ ቦታ አካባቢው ጨቅይቶ ይታያል ፣ አንዳንዱ ቦታ ቧምቧው ተበላሽቶ ውሃው በከንቱ ይፈሳል ። ሞተሮች ተበላሽተው ለመጠገን ብዙ ጊዜ የሚወስድባቸው ሁኔታዎችም አሉ። የመንደር ምሥረታው አንዱ ፋይዳ የገጠሩን ሕዝብ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ማስተዋወቅ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተገቢው ዕውቀት ደረጃ በደረጃ መሠራጨቱን ማረጋገጥ የተጠናከረ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል ።

ከመንደር ምሥረታ ዓላማዎች አንዱ የገጠሩ ሕዝብ በኢንዱስትሪ ውጤቶች የሚጠቀምበትንና ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር የሚተዋወቅበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነው ። ከዚህ አኳያ በአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካይነት በነዳጅ የሚሠራ የእህል ወፍጮ ፣ በአገልግ

ሎት ሱቆች አማካይነት የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ነው ። በሐረርጌ መንደር ምሥረታው ከተጀመረበት ከየካቲት 1977 እስከ 1979 መጨረሻ ብቻ 60 በነዳጅ የሚሠሩ የእህል ወፍጮዎች መንደሮች አካባቢ መተከላቸው ካለው ሁኔታ አኳያ በዚህ በኩል የተሰጠውን ትኩረት የሚጠቁም ነው ።*

በሕዝብ ሱቅ አገልግሎትም በኩል ገበሬው በአንድ አካባቢ በመሰባሰቡ ሱቁን ለማደራጀትም ሆነ የተገኘውን ሸቀጥ በወቅቱና በአግባቡ ለማከፋፈል ካለፉት ሁኔታዎች የተሻለ እንቅስቃሴ ይታያል ። ሸቀጣ ሸቀጥ ፍሊጋ ብዙ መንገድ መሄድም እየቀረ ነው ። ቢሆንም በተለይ በየአውራጃው ከተቋቋሙት የኢትዮጵያ ሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት መጋዘኖች ወደ የአገልግሎት ሱቆች ለማድረስ በተራ ጥበቃ የሚባክነው ጊዜና በዚሁ ሳቢያ ለዕቃ ገገርዎች የሚከፈለው አበል መጠን ፡ ዕቃውን አስጭኖ ለመውሰድ ለግል ባለመኪናዎች የሚከፈለው የማጓጓዣ ሒሳብ ከፍተኛነት ያስከተለው የዋጋ ንረት በአንዳንድ ሸቀጥ ዋጋ ላይ በጉልህ ይታያል ። እነዚህ ችግሮች እንዲፈጠሩ የሚያደርጉ የመጠቃቀም ሁኔታዎችም ግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል ። በመሆኑም የገጠሩን ሕዝብ ኑሮ ለመለወጥ ኃላፊነት በተሰጣቸው ወገኖች በኩል የተጠናከረና የተቀናጀ ሐቀኛ ጥረት ይጠበቃል።

በትምህርት ቤት ፡ በክሊኒኮችና በሙዓለ ሕፃናት በኩል የተደረገው ጥረትም በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ከመንደር ምሥረታው በኋላ ከ1977 — 80 ባለው ጊዜ ብቻ በአዲሶቹ መንደሮች 25 ክሊኒኮችና 100 ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ ተሠርተዋል ።** እነዚህ አኃዞች በእራሳቸው ብቻ ብዙም ላያመለክቱ ይችላሉ ። ገበሬው ተበታትኖ ይኖር በነበረ ጊዜ ይህን ያህል ቢሠራም እንኳን የተጠቃሚው ቁጥር አነስተኛ ነው ። ዛሬ ግን ገበሬው በመንደር ተሰባስቦ በሚገኝበትና በቅርበት እያንዳንዳቸው ለሁለትና ሦስት መንደሮች አገልግሎት በሚሰጡበት ሁኔታ ጠቀሜታቸው ይበልጥ ስፋት አግኝቷል ። ከዚህ በተጨማሪ በገጠራቱ ኢትዮጵያ ሙዓለ ሕፃናት ተሠርተው ዕድሜአቸው ለመደበኛ ትምህርት ያልደረሱ ሕፃናት የአብዛኞዎቹ የገጠር ሕፃናት ዕጣ ሆኖ ከቆየው እረኝነትና ልዩ ልዩ የግብርና ሥራ በፊት በሙዓለ ሕፃናት ፊደልና ቁጥር ሲማሩ ፡ ዕድል አጋጥሟቸው በኩልታፋ ልሳናቸው መዝሙር ሲዘምሩ መስማትና ማየት የሚያስደስት ነው ። በሐረርጌ ገጠር ብዙም ባይሆን በዚህም በኩል ያለው ጥረት የሚናቅ አይደለም ።

ሙዓለ ሕፃናት ከተቋቋመባቸው መንደሮች አንዱ በወበራ አውራጃ ፡ በሜታ ወረዳ የምትገኘው የዱ.ዩ.ዩ. ኤላ ቁጥር 4 መንደር ናት ። መንደሯ የተመሠረተችው በ1978 ነው ። ከመንደር ምሥረታ በኋላ በ1979 አንድ ሙዓለ ሕፃናት ተቋቁሞ ከመጋቢት 1/80 ጀምሮ ሕፃናትን ያስተምራል ። ዕድሜአቸው ለመደበኛ ትምህርት ያልደረሰ 136 ሕፃናት በዚህ ሙዓለ ሕፃናት ይማራሉ። ሶሬያ ኢብራሂምና ሙሉነሽ ጥሩነህ የተባሉ ሁለት ወጣቶች ከዚያው ክልል ተመልምለው ኮምቦልቻ ተልከው በሙዓለ ሕፃናት አስተማሪነት ሠልጥነው እዚያው ተመልሰው ያስተምራሉ ። ሕፃናቱ ዕድሜአቸው ለመደበኛ ትምህርት ሲደርስና ፊደልና ቁጥር ሲለዩ እዚያው ወዳለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገባሉ ። ይህም የመንደር ምሥረታው የፈጠረው አመች ሁኔታ ነው ።

በኤክስቴንሽን (በግብርና ዘዴ) አገልግሎትና በከብት ሕክምና ረገድ የመንደር ፋይዳ ጉልህ ውጤቶች እየታዩበት ነው ። በገጠሩ የሚመደቡ የግብርና ባለሙያዎች ጥረታቸው እንደቀድሞው የተበታተነ አይደለም ። በፕሮግራም በተያዘ ቀንና ሰዓት ገበሬውን ሰብስቦ ማስተማር ይቻላል ። በሙከራ ጣቢያዎችና በችግኝ ጣቢያዎች አማካይነት በተወሰኑ ቦታዎች የዘመናዊ አስተራረስን ጠቀሜታ ማሳየት ካለፈው ጋር ሲነፃፀር በጣም ቀሏል ። አንድ መንደር ውስጥ አንድ ቦታ በማመቻቸት የሁሉንም ነዋሪ ከብቶች ማከም ተችሏል ። እንደቀድሞው ብዙ መንገድ ማጓጓዝና የሥራ መዝረክረክም አይኖርም ። ከየገበሬው ተመልምለው መጠነኛ ሥልጠና ባገኙ አገናኝ ገበሬዎች አማካይነት በመንደሩ የሚደርስ ማንኛውም ችግር ፡ የከብት በሽታና የመሳሰለው በአስቸኳይ ለባለሙያ ይነገራል ። አቅም በፈቀደ መጠን በአፋጣኝ እርምጃ ይወሰዳል ። በየአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚታየው ዘመናዊ ከብት እርባታ ፤ ዘመናዊና ባህላዊ ንብ እርባታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ የኤክስቴንሽን አገልግሎትም መስፋፋት ውጤት ነው ። በሐረርጌ በአሁኑ ጊዜ ፡ “በ28 ማኅበራት 249 ዘመናዊና 117 የባህል ቀፎ ያላቸው 28 የንብ እርባታ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል ።”* ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በተለይ ዘመናዊ ቀፎ ወደ ገጠር ማስገባቱና ገበሬው እንዲለምድ ማድረጉ ሊበረታታ የሚገባው ጅምር ነው ። የተሰባሰበን ገበሬ ለማስተማር የሚኖረው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም።

ለገበሬው የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማጠናከር ከሚደረጉ ሙከራዎች አንዱ ከጅጅጋ 33 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚካሄደው በምሥራቅ ቀጣና ግብርና ልማት የዋንኬ በጎች ማራቢያና ማሻሻያ ፕሮጀክት ነው ። በጠቅላላው ሐረርጌ 18 ሚሊዮን እንስሳት (ልዩ ልዩ ዓይነት) እንደሚገኙ ሲገመት ፡ ከዚህ መካከል አራቱ ሚሊዮን በጎች ናቸው ። በተለይ በቆላማው አካባቢ የሚረቡት የዋንኬ በጎች ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን የእነዚህም ዝርያ ለውጭ ገበያም ይቀርባል ።

ሆኖም ያለው የበግ አረባብ ዘዴ ዘመናዊና የተጠና ባለመሆኑ አርቢው የተፈለገውን ውጤት ማግኘት ካለመቻሉም በላይ በግጦሽ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል ። በመሆኑም በ2,000 ሄክታር መሬት ዘመናዊ የዋንኬ በግ እርባታ በማካሄድ የዋንኬ በግ ዝርያዎችን ዶርፐር ከሚባሉ ከዚምባቡዌ ከመጡ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል አሁን ያለውን 31 ኪሎ ግራም የዋንኬ በግ የቁም ክብደት ወደ 60 ኪሎ ግራም ከፍ ለማድረግ ፡ በዚህ ረገድ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርቢው ለመስጠትና በአረባቡም ሆነ በግጦሽ መኖ በክልሉ ጥናት ለማካሄድ ይህ ፕሮጀክት ተቋቁሟል ። የዶርፐር ዘሮች የቁም ክብደታቸው ከ67 — 87 ኪሎ ግራም የሚደርስ ሲሆን

* የመንደር ምሥረታ በሐረርጌ ፡ ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 20·

** ዝኔ ከማሁ ።

* የሐረርጌ ገበሬ ከትናንት እስከ ዛሬ ፤ ከላይ የተጠቀሰ ገጽ 26·

በአብዛኛው መንታ የመውለድ ባህርይ አላቸው ። ችግርንም የመቋቋም ዐቅማቸው ከፍተኛ ነው ።

ከፕሮጀክቱ ባለሙያዎች እንደተገለፀው የገበሬው በመንደር መሰባሰብ በጐቹን በማዳቀል የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠትም ሆነ የዲቃላዎቹን ባህርይ ለመቆጣጠር አመች ሁኔታ ይፈጥራል ። በተበታተነ ሁኔታ ግን እንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ሊሞከር አይቻልም ባይባልም አስቸጋሪነቱ የጐላ ነው ።

ገበሬውን በመንደር ከማሰባሰቡ ጠቀሜታዎች አንዱ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በገጠሩ ለማስፈን አመቺ ሁኔታ መፍጠሩ ነው ። በአብዮቱ ጊዜ ከዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ እንስቶ በገጠሩ የአገልግሎትና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለያዩ ቦታዎች ተቋቁመዋል። በተለይ በ1971—72 በተካሄደው የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ወቅት በርካታ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መቋቋማቸው ይታወቃል ። በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው በአርአያነት የሚጠቀሱ ማኅበራት በዚያን ጊዜ የተቋቋሙ ናቸው ።

ይሁን እንጂ የማኅበራቱ ዕድገት ፣ በብዛትም ሆነ በይዘት የተፈለገውን ያህል ነው ማለት ያስቸግራል ። ለገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት አለመፋጠን በርካታ ምክንያቶች የሚጠቀሱ ሲሆን ከምክንያቶቹ አንዱ የገበሬው ተበታትኖ መኖር ለማደራጀትና ለማስተማር አለመመቸቱ እንደሆነ ይነገራል ። በአሁኑ ወቅት ካለፉት የአብዮት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ፣ ገበሬው በመንደር መሰባሰቡ ባስከተለው አመቺ ሁኔታ ምክንያት ብቻ በሐረርጌ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት የተሻለ እንደሆነ ታይቷል። ከ1968 እስከ 1977 ባሉት አሥር ዓመታት 7,803 አባላት ያሏቸው 143 የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ብቻ ሲቋቋሙ፡ ከ1978 እስከ 1980 ባሉት ሦስት ዓመታት ብቻ የአባላቱ ብዛት ወደ 28,983 ሲደርስ ማኅበራት 304 መድረሳቸው ለአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት የመንደር ምሥረታው ያበረከተውን አስተዋጽኦ ያሳያል ። በየዓመቱ ያለውን ዕድገትም ከሚከተለው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል ።

በጥቅሉ ሲታይ አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም የገበሬው በመንደር መሰባሰብ በኤክስቴንሽን አገልግሎት ፣ በንፁህ ውሃ ፣ በክሊኒክ ፣ በትምህርት ፣ በደን ልማት ወዘተ. ጐላ ያለ ውጤት አስመዝግቧል ። ከእነዚህ ሁሉ ባላነሰ መንደር በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወት ያስከተለው የሥነ—ልቦና ለውጥም ቀላል አይደለም ። ቀድሞ ገበሬው ተበታትኖ በሚኖርበት ሁኔታ ሰው ሲታመምና ሲሞት ፣ ወይም ሌላ ደስታም ሆነ ችግር ሲያጋጥመው የእርስ በርስ ግንኙነት መጥፎ ባይሆንም በጣም አመች ነበር ለማለት ያዳግታል ።

ዛሬ ግን አንድ ሰው ቤት ሐዘን ቢደርስ ፣ ቢሠረግ ፣ ሰው ቢታመም መንደረተኛው በሞላ ወዲያውኑ ይሰማል ። ሁሉም እንደየአቅሙ በገንዘብ ፣ በጉልበት እገዛ ያደርጋል። አንዳንድ መንደሮች እንዲያውም ለሠርግና ለሀዘን በእድር መልክ ተደራጅተው የተወሰነ ገንዘብ ያዋጣሉ ። መንደረተኛው ተሰባስቦ ሠርጉንም ሆነ ሐዘኑን በጋራ ይወጣሉ ። ይህን አስመልክቶ በወበራ አውራጃ በሜታ ወረዳ ፣ የዱ.ዩ.ዩ. ሌላ ቁጥር 4. መንደር ነዋሪ የሆኑት የ60 ዓመቷ

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ዕድገት በየዘመኑ (በየዓመቱ)*

ተ.ቁ	ዓ.ም	ብዛት	የአባላት ብዛት	የእርሻ በሬዎች ብዛት	የመሬት ይዞታ በሄክታር
1	1968	3	180	42	135
2	1969	5	168	72	153
3	1970	12	435	287	497
4	1971	18	810	502	952
5	1972	73	3,650	1,005	2,136.82
6	1973	94	4,778	2,613	7,473
7	1974	96	4,885	2,663	7,589.94
8	1975	112	5,719	3,410	8,790
9	1976	130	6,803	4,217	11,893.22
10	1977	143	7,803	5,104	13,368.15
11	1978	190	12,358	7,440	18,464.13
12	1979	255	23,366	11,402	30,057.13
13	1980	304	28,983	12,161	36,593.04

አዛውንት ወይዘሮ ፋጡማ ዩሱፍ አሊ ያጫወቱን ሁኔታውን በግልጽ ያሳያል ። ወ/ሮ ፋጡማ 11 ልጆች ወልደው ዘጠኙ በሕይወት አሉ ። አንዱ ልጃቸው በሚሊሺያ ሠራዊት ዘምቶ ኤርትራ ነው ያለው ። አራቱ በአካባቢያቸው ሲኖሩ ሌሎች አግብተው የተለያየ ቦታ ሄደዋል ። ወይዘሮ ፋጡማ እንደሚሉት ብዙ ልጆች አሳድገዋል ፣ ድረዋል ፣ ሌሎችም ብዙ ሠርጎች አይተዋል ። በዕድሜአቸው ሙሉ ግን መንደር ከተመሠረተ ያዩት ሠርግ ከሁሉም የደመቀና ደስ የሚል ነበር ። “ቀድሞ ተበታትነን ፣ እያንዳንዳችን ዙሪያችንን አጥረን ነበር የምንኖር ። አሁን ግን ቤታችንን ከፍት ብንተው እንኳን የሚያሰጋ ነገር የለም ። ጐረቤቱ በቅርብ ተጠራርቶ ሊደርስ ስለሚችል የሚያስፈራም ነገር የለም ። በሕይወቴ ብዙ ሠርግ አይቼአለሁ እኔም ድሬአለሁ ። እዚህ መንደር ያየሁት ሠርግ ግን ከሁሉም የደመቀና ደስ የሚል ነበር ። መንደረተኛው ሁሉ ምግብና ወተት እየያዘ ነበር የሚመጣው ። ባለቤቶቹ በጣም ትንሽ ነው ያወጡት ። ወጣቱ ተሰባስቦ ይዘፍናል። አዛውንቶች ይጫወታሉ ፣ ጸሎት ያደርሳሉ። በጣም የደመቀና ደስ የሚል ነበር ።”

ሀዘንም ሲደርስ ይኸው ነው ። የተወሰነው የቀብሩን ሥነ—ሥርዓት ይከታተላል። የተወሰነው ደግሞ የሚበላ የሚጠጣ ያዘጋጃል ። በእድር ስኳርና ወተት ይመጣል ። ሆጃው (ሻይ) ይዘጋጃል። ባለቤቶቹ ከሀዘኑ በስተቀር ብዙም የሚያሳስባቸው ነገር የለም ።

* የሐረርጌ ገበሬ ፣ እላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 38

በአዲሶቹ መንደሮች የመንደሩ ነዋሪ፡
ከሕፃን እስከ ሽማግሌ ይተዋወቃል ። በጨ
ጥታ ፡ በውይይት ፡ በደስታ ፡ በመከራ
ችግሩን ይካፈላል ። ቀድሞ በተንተን ብሎ
ይኖር የነበረው ዛሬ የአንድ መንደር ነዋሪ
ነቱ የፈጠረው ስሜት ቀላል አይደለም ።
ሕፃናት አንድ ትምህርት ቤት ይማራሉ ።
ከአንድ ምንጭ ወይም ቧንቧ ውሃ ይቀ
ዳሉ። አንድ መስክ ላይ እየተጫወቱ ያድ
ጋሉ ።

እናቶች ከምግብ አዘገጃጀትና ከቤት
አያያዝ ጀምሮ አንዱ ከሌላው ለመማማር
አመች ሁኔታ ተፈጥሯል ። በገበሬው ቤት
በገዛግና በቁም ምድጃ አጠቃቀም ፡ በቤት
ውስጥ ክፍፍል ወዘተ. የሚታየው መማ
ማር ወደፊት ለሚታሰበው ዕድገት መነሻ
ነው ።

አረጋውያን ሲታመሙ በቅርቡ ይጠያየ
ቃሉ ፡ ከሥራ ውጭ አብረው እያወጉ
ያመሻሉ ። በእነዚህ ሁኔታዎች የተነሣ
በመካከላቸው የሚፈጠረው የመተባበር
ስሜት ቀላል አይደለም ።

በገጠሩ ነዋሪ የእርስ በርስ ግንኙነት
ቀድሞ ላላ ያለ ስለነበር በተለይ በዝቅተኛ
የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ጐሳዎች መካከል
የጐሳ ግጭትም በብዙ ቦታዎች ይከሰት
እንደነበር ይታወቃል ። አሁንም ገና ያልተ
ወገዱላቸው አካባቢዎች አሉ ። ይህ ከኋላ
ቀርነት የመነጨ ጥላቻ ለተባበረ ዕድገት
ማነቆ ከመሆኑ ባሻገር የተለያዩ የአገርና
የሕዝብ ጠላቶች በልዩ ልዩ አጋጣሚ ሲጠ
ቀሙበት ኖረዋል ። አንዱን ጐሳ በሌላው
ላይ በማስነሣት እርስ በርስ ማጣላት ፡
ማስዘረፍ ፡ ማጋደል ፡ በዚያ አመካኝቶ
የፈለጉትን ለማግኘት መጣር የተለመደ
ዘይቤ ሆኖ ቆይቷል ። አንዱ ጐሳ በሌላው
ላይ የጥላቻና የንቀት ስሜት እንዲያድርበት
በማድረግ እርስ በርስ እንዳይጋቡ ፡ አብ
ረው እንዳይኖሩ ይፈጸም የነበረው ተንኰል
ለብዙ ችግሮቻችን መንሥኤ ሆኖ ቆይ
ቷል።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ
ያለው የመንደር ምሥረታ ይህንን ሁኔታ
በመለወጥ ረገድም አስተዋፅኦ እያደረገ
እንደሆነ ይታመናል ። ተራርቆ መኖር
አንዱ ሌላውን ለማወቅ አያስችልም ።
የተቀራረበ ግንኙነት ከሌለ መግባባት አይ
መጣም ። አብሮ መሥራት ፡ መገበያየት ፡
በሀዘንና በደስታ መካፈል ፡ ልብ ለልብ
ያቀራርባል ፡ መተዋወቅና መግባባት ይፈ
ጠራል ። ጥላቻና መጠራጠር እየቀረ መጋ
ባት፡ መዋለድና መዛመድ ይመጣል ።

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የማይግባቡ ጐሳ
ዎች በመቀራረብ ላይ ከሚገኙባቸው መን
ደሮች አንዱ በጅጅጋ አውራጃ የሚገኘው
የኤል አህማር ሐልገሪ ቀበሌ መንደር ነው።
ኤልአህማር ሐልገሪ 1,315 ነዋሪዎች ያሉ
በት መንደር ሲሆን የተመሠረተው በ1978
ነው ። ከዚያ በፊት በገበሬ ማኅበሩ 9
ትናንሽ መንደሮች ሲኖሩ ነዋሪው እርስ
በርሱ በብዛት አይተዋወቅም ነበር ። አለመ
ተዋወቅ ብቻም አይደለም ። በአካባቢው
የሚኖሩት የግሪ ጐሳዎችና የጀርሶ ጐሳዎች
ናቸው ። በሁለቱ መካከል ጥላቻ አለ ።
በጥላቻው የተነሣ እርስ በርሳቸው በየጊ
ዜው ይዋጋሉ ፡ ይዘራረፋሉ ። ከሱማሊያ
የሚመጡ ሰርጎ ገቦች በዚሁ ጥላቻ በመጠ
ቀም ሁለቱን ጐሳዎች በ1976 አጋጭተዋቸ
ዋል ። በመካከላቸው ከአራት ወር በላይ
የፈጀ መራራ ጦርነት ተካሂዷል ። ብዙ
ሰው ሞቷል ። ቤቶች በብዛት ተቃጥለዋል።
ለአምስት ገበሬ ማኅበር እንዲያገለግል የተ
ቋቋመው የአገልግሎት ሱቅ ተዘርፏል ፡
ተቃጥሏል ። ቀደም ሲል የተቋቋመ የውሃ
ጉድጓድ እንኳን በሥርዓት መጠቀም አልተ
ቻለም ። ግማሹ ነዋሪ ጠፍቶ ወደ ጐረቤት
አገር ሲሄድ ግማሹ ወደ ከተማ ተሰደደ ።

በአሁኑ ወቅት ግን ሁኔታው ለየት ያለ
መልክ እየያዘ ነው ። እነዚህ ጠበኞች
በአንድ መንደር ተሰባስበው ልጆቻቸው
በአንድ ትምህርት ቤት እየተማሩ ፡ በአንድ
መስክ እየተጫወቱ ፡ ከአንድ ጉድጓድ ውሃ
እየቀዱ ፡ ከአንድ ሱቅ እየሸመቱ ፡ በአንድ
ስብሰባ ላይ ስለጋራ ጉዳያቸው እየተወያዩ
አብረው ይኖራሉ ። በሁለቱ ጐሳዎች መካ
ከል በልዩነት ቦታ አንድነት ፡ በጥላቻ
ፋንታ ፍቅር ፡ ከመዋጋት ይልቅ መተባበ
ርና መተዛዘን ጠቃሚ መሆኑ ከጊዜ ወደ
ጊዜ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል ። አንዱ
ስለሌላው በርቀት የነበረው ግምት ቀስበ
ቀስ እተለወጠ ይሄዳል ። በዚህ መልክ
ረዘም ላለ ጊዜ አብረው ሲኖሩ ሙሉ
በሙሉ መግባባትና መፈቃቀር እንደሚ
መጣ ግልጽ ነው ።

ከላይ እንደተገለጸው በመንደሮች ከሚ
ታዩ የማኅበራዊ ሥነ ልቦና ለውጦችና
በአንዳንዶቹ እየተቋቋሙ ጥቅም ላይ ከዋ
ሉት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎ
ቶች ሌላ የወደፊቱ ገጠር ሕይወት ምን
ሊመስል እንደሚችል የሚጠቁሙ ሞዴል
መንደሮችም በርካታ ናቸው ። ከሞዴል
መንደሮች እንደ ዲሮ አዲስ ዓለም መንደር
ናት ፡ ዲሮ በሀብሮ አውራጃ ፡ ሀብሮ ወረዳ ፡
ከገለምሶ 14 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምት
ገኝ መንደር ናት ። የዲሮ መንደር የእህል
ወፍጮ ፡ ክሊኒክ ፡ እስከ 5ኛ ክፍል
ትምህርት የሚሰጥበት አንደ ኛ ደረጃ
ትምህርት ቤት ፡ የሕዝብ ሱቅ ፡ 11
ማከፋፈያ ያለው የውሃ ቧምቧ አላት ።
በመንደርተኞቹ መካከል ብዙም ባይሆን
ለንፋስ መከላከያ የሚሆኑና ለአካባቢው
ውበትና ግርማ የሚሰጡ ዛፎች ተተክለ
ዋል። ከብዙ መንደሮች በተለየ መልክ
የውሃ መቅጃው ቢርካ በአጥር ተከልሎ
በቁልፍ ነው የሚጠበቅ ። እመንደሯ በደረ
ስንበት ወቅት ክሊኒኩ ለሕፃናት ፀረ
ስድስት ክትባት የሚሰጥበት እለት ነበር ።
ቀድሞ ለትንሽ ሕመም ገለምሶ ወይም
መቻራ ይወሰዱ የነበሩት የዲሮ አዲስ
ዓለም ነዋሪዎች ዛሬ እደጃቸው ሕክምና
ያገኛሉ ።"እኔ በሕይወቴ እንኳንስ ክት
ባት ፡ ታምሜ የመታከም ዕድል ገጥሞኝ
አያውቅም" የምትለዋ የ20 ዓመቷ ከድጃ
መሐመድ ያሲን ልጇን ስታስከትብ አገኘ
ናት ። በሷ ዕድሜ አሁን ልጇን አስከትባ
በምትከላከላቸው ዓይነት በሽታዎች ስንቱ
ሕፃን ተቀስፏል ። እሷ ግን ተደራጅቶና
ተሰባስቦ መኖር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ
ከአዲሱ መንደር እያገኘች ነው ።

ዲሮና ሌሎች ሞዴል መንደሮች የነገ
ውን ገበሬ ሕይወት ገጽታ ይጠቁሙናል ።
ይሁን እንጂ በሞዴሎች ላይ ማተኮሩ የተ
መጣጠነ ዕድገት ለማምጣት ከሚኖረው
ፍላጎት አኳያ መጠኑ ይኖርበታል ። ከብዙ
ሞዴሎች ይልቅ አገልግሎቶች በተለያዩ
መንደሮች ለማዳረስ መሞከሩ ጠቀሜታው
የተሻለ ላይሆን አይቀርም ። አንዱ መንደር
ውሀ ሲያገኝ ሌላው ትምህርት ቤት ፡ ደግሞ
ሌላው ክሊኒክ እያለ ዕድገቱን ቢጠብቅ
ሁሉንም ማዳረስ ባይቻል ማቃመስ ይቻ
ላል ።

ጉብኝም ሲሄድ ሁልጊዜ ወደትወሰኑ
ሞዴል መንደሮች ለመውሰድ የሚታየው
ሙከራ ሞዴል ላይ በመተኮሩ የተነሣ ነው።
ተደጋግሞ የመጣ ጉብኝ ወይም አጥኚ

እነዚያኑ የሚያውቋቸውን መንደሮች በተደጋጋሚ እንዲያዩቸው ሲጋበዝ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው ጉልህ ለውጥ በጥርጣሬ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል ። ሌሎች መንደሮችም ቢሆኑ አለመጎብኘታቸው ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን መበረታታት ሊያሳጣቸው ይችላል ።

ስለ ሐረርጌ መንደር ዘርዘር አድርገን እንደገለጽነው የዚያ ክልል ገጠር ያለጥርጥር ለውጥ እያሳየ ነው = ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ ተፈጥሯል = ይህ ማለት ግን ድክመት የለበትም ማለት አይደለም = እንደሚታወቀው በመንደር ምሥረታው ወቅት በሐረርጌ የተቀየሰው አሠራር ስምንቱ የደጋ አውራጃዎች በአራት ቀጣናዎች ተከፋፍለው እያንዳንዱ ቀጣና በክፍለ ሀገሩ ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የቅርብ ክትትል ተግባሩን ማከናወንና ይኸው አሠራር እስከ ወረዳ እንዲወርድ ማድረግ ነበር= ይህንኑ አሠራር የክልሉ የገበሬ ማኅበር የገበሬውን የእርሻ ሥራ ለመከታተልና ለመቀስቀስ ሲጠቀምበት ቆይቷል = ከዚህ በተረፈ ግን እንደቀድሞው መንደር የተመሠረተበትን ዓላማ በትክክል ተግባራዊ የማድረግና ድክመቶችን የማረም የጎላ ጥረት አይታይም = በዚህም የተነሣ የሚታዩ ድክመቶች አሉ =

መንደር ሲመሠረት ከታቀዱ ዓላማዎች አንዱ ገበሬው በአንዲት ክፍል ከከብቶቹ ጋር አብሮ እየኖረ እዚያው አብስሎ የሚመገብበትን ሁኔታ መለወጥ ነው = በወቅቱ ቤቶቹ እንዲከፋፈሉ ፡ ማድቤት እንዲሠራ ፡ መጸዳጃ ቤት እንዲቆፈር ተደርጓል = ይሁን እንጂ በጊዜና በማቴሪያል እጥረት የተነሣ የተወሰኑ ቤቶች በዚህ ረገድ በይደር ቀርተው እንደነበረ ይታወቃል = የመንደር ምሥረታው ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት እነዚህን ከሚሉት ቤቶች በተጨማሪ በየዓመቱ በዕቅድ እየተያዘ የተጓደለውን ለማሟላት ጥረት እንደሚደረግ ተገምቶ ነበር ። ነገር ግን አልፎ አልፎ በታሰበው መልክ እንዳልተፈጸመ ወይም ለመፈጸም ትኩረት እንደሌለ ይታያል ። በክፍለ ሀገሩ በ1980 37,851 ማዕድ ቤቶች ለመሥራት ታቅዶ 11,569 ተሠሩ ፤ 31,352 መፀዳጃ ቤቶች ለማሠራት ታቅዶ 15,744 መሠራቱና 50,547 የቆሻሻ ጉድጓዶች ለማስቆፈር ታቅዶ 13,410 መቆፈሩ ቀላል ግምት የማይሰጠው ቢሆንም በመንደር ምሥረታው ወቅት የነበረው ትኩረት ለመቀነሱ አንድ ጠቋሚ ምልክት ነው ። በእርግጥ በዚሁ ዘመን በጉተራ ሥራና በወንዝ ጠለፋ ከዕቅድ በላይ ሲከናወን ፤ በምንጭ ማጐልበት ረገድ ከታቀደው 99% ግብ መምታቱም ተገቢ ግምት የሚሰጠው ክንውን ነው ።

በጓሮ አትክልትም በኩል በተለይ በሰብል ወቅት በብዙው ገበሬ ጓሮ በቆሎና ማሽላ ለምልሞ ከሚታይ በቀር በአትክልት፣ በቋሚ ተክሎች ፤ በፍራፍሬም ሆነ በሌሎች ዛፎች ልማት ያለው እንቅስቃሴ ጉልህ አይደለም ። ቆላማው አካባቢ በዝናብ እጥረት ያመካኛል ። ለደጋውና ወይናደጋው ግን የጥረት ማነስ ካልሆነ ሌላ ምክንያት ሊሰጥ አይችልም ። ዛሬ የግብርና ልማት ሠራተኞች በቂ ነው ባይባልም ከምንጊዜውም የበለጠ ወደ ገጠሩ ገብተዋል ። በየቦታው የችግኝ ጣቢያዎች ይታያሉ ። እነዚህን አጠናክሮ ለገበሬው የዕለት ተዕለት ጥቅም የሚውሉ ዛፎችን ፤ በተለይም የፍራፍሬ ዛፎችን ችግኝ እያፈሉ ማዳረስ የሚኖረው ጠቀሜታ ቀላል አይሆንም ። ገበሬው ላለበት የማገዶና ለቤት ሥራ ችግር ሊውል ይችላል ። የፍራፍሬ ዛፍም ከሆነ ከቤት ጠቀሜታ አልፎ ለገበያም ሊቀርብ ይችላል ። ሐረርጌ በፍራፍሬ የምትታወቅ በመሆኑ ምርቱ ሲጨምር ለኢንዱስትሪ ውጤትም ሊታሰብ ይችላል ። በሌላ በኩልም ገበሬው ቋሚ አትክልትና ዛፍ እየተከለ በሄደ መጠን ከመሬት ጋር ይበልጥ ይቆራኛል ። አለበለዚያ ለረጅም ጊዜ በቀድሞ መኖሪያው ጓሮ የነበረን ዛፍ እየናፈቀ ከአዲሱ መንደር ጋር ያለው ቁርኝት የላላ ሊሆን ይችላል ።

አንዳንድ በተለይ ከብት አርቢዎች በሚበዙበትና የጎሳ ግጭትም አልፎ አልፎ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች በግጭቱ ፤ በውሃ እጥረት ፤ የቅርብ ክትትል ወዘተ. በማነሱ ምክንያት መንደሮቹ በጣም ቀዝቅዘው ሰው የሌለባቸው የሚመስሉበትም ሁኔታ ለጊዜው አሳሳቢ ባይመስልም ይታያል ። ከሸዋ ገና ሐረርጌ ክልል ሲገቡ በተንጣለለ ሜዳና በቁልቋል ቁጥቋጦ ውስጥ ከሚታዩ መንደሮች አንዳንዶቹ በዚህ ረገድ የሚጠቀሱ ናቸው ። የእነዚህ መንደሮች ነዋሪዎች በከፊል አራሽ ፤ በከፊል ከብት አርቢ ናቸው ። በተለይ ከብት አርቢዎቹ በአካባቢው የውሃ እጥረት ስላለ ከብቶቻቸውን ይዘው ወደአርባ ወንዝና አዋሽ ድረስ ይሄዳሉ ። ከፊሎቹ በዚያው የሚቀሩም አሉ ። በአንዱ መንደር እንደነገሩን ወደ ኢረርና ሀብሮ ሄደው ያልተመለሱም አሉ ።

ከነዚህ መንደሮች አንዱ የድሬ ቃሉ መንደር ናት ። የአዋሽን ቆላማ አካባቢ አቋርጦ እንደተወጣ ከሚታዩ መንደሮች አንዱ ናት ። በጧት ስለደረስን የተወሰኑ ሰውና ከብት በመንደር እንዳለ ተመልክተን እንጂ ፀሐይ ሲሞቅ በጣም ጭር ስለሚልና በመንደሩ ውስጥ ከትንንሽ ቤቶችና ቁጥቋጦ በስተቀር ምንም ስለማይታይ ኦና ይመስላል ። የመንደሯ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር የሆኑት አሊዮ ቦሩ ጨላ እንደገለፁልን በአካባቢው ያለው ትልቅ ውሃ የአርባ ወንዝ ሲሆን እሱም 15 ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል ። በተለይ በበጋው ከብቶችን ወደዚያ መውሰድ ያስፈልጋል ። በወንዙ ዳርቻ ትንሽ ማሽላም ይዘራል ። ስለዚህ በተለይ በበጋው ብዙው ሰው ከብቱን ይዞ ወደዚያ ነው የሚሄድ ። መንደሩ ሲመሠረት 218 አባወራዎች ነበሩ ። በአሁኑ ወቅት ግን ያሉት 180 አባወራዎች ናቸው። ሌሎች ሰዎች ለቀው ሄደዋል ።

በመንደሯ የልማት እንቅስቃሴ አይታይም ። ገበሬዎቹ በራሳቸው የውሃ ማጠራቀሚያ ኩሬ ለመቆፈር ሞክረዋል ። እሱም በጣም ትንሽ ነው ። ውሃም አልያዘም ። አካባቢው ብዙ ከብቶች የሚገኙበት ነው ። የከብቱ ፍግ በየቦታው ተቆልሎ ይታያል ። በአጠቃላይ ግን የአካባቢው ልማት የተፈጥሮ ተጽዕኖ ቢኖርም የተሻለ ሊሆን ይችል ነበር የሚል እምነት አሳድሮብናል ።

በአካባቢው ሌላም መንደር አለ ። መጠነኛ እርሻ ከመኖሩ በስተቀር ሁኔታው ያው ነው ። ቤቶቹ ትንንሽ ናቸው ። እነሱም እየፈራረሱ ነው ። ከእነዚያ ውስጥ የሚወጣው የበግና የፍየል መጠን ሲታይ አብሮ ማደር ለምን ማለቱ ቀርቶ ለሁሉም በቅቶ ሰውም ያስተኛል ወይ ያሰኛል ።

በእርግጥ ኅብረተሰቡን ከቆየበት ልማድ ወደ ሌላ ለማሸጋገር የሚጠይቀው ጥረት ቀላል አይደለም ። እንዲህ በአጭር ጊዜ የሚፈለገው ውጤት ሁሉ ይጨበጣል ተብሎም አይታሰብም ። በለውጥ ሂደት ውስጥ ድክመቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉም ከመነሻው ይታመናል ። ዋናው ቁም ነገር በተገኙ መልካም ውጤቶች መወሰን ሳይሆን ያለማቋረጥ ለድክመቶች መፍትሄ መፈለግ ነው።

በሐረርጌ ገጠር ከመንደር ምሥረታ ጋር

በተያያዘ የሚታየው ለውጥ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው ። ለትምህርታዊነቱ ተፈጹባጭ ማስረጃ ከሚሆኑ ምክንያቶች አንዱ በመንደር ምሥረታው ወቅት በነበረው ቅስቀሳ ጠፍተው ወደ ጐረቤት አገር የሄዱ እንኳን ለውጡን እየሰሙ ተመልሰው መምጣታቸው ነው ። በዚህ መልክ ከተመለሱት መካከል ኤልአህማር ሐልገረ ቀበሌ መንደር ዱይዴ ኤላ ቁጥር 4 መንደር ያገኘናቸውን አደም ኢማም ሙሐመድ እና ሀሰን ዑመር የተባሉትን አነጋግረን ነበር ።

አደም ዒማም ሙሐመድ የ26 ዓመት ወጣት ነው ። “መንደር ከተመሠረተ በየሁለት ቤቶች መካከል ድንኳን ተተክሎ በወታደር ይጠበቃል ። ዙሪያው ይታጠርና ሁለት በር ብቻ ይኖራል ። ከብት ይወረሳል ። ወተት አንድ ቦታ ይሰበሰብና አንዳንድ ኩባያ ብቻ በቀን ይሰጣል” እየተባለ ይነገር በነበረው ቅስቀሳ ተወናብደው ከብቶቻቸውን ሸጠው ወደ ጐረቤት አገር ከገቡት አንዱ አደም ነው ።

ሌላው በዚህ ቅስቀሳ ተወናብዶ የሄደው ሀሰን ዑመር ነው ። ሀሰን ሁመር ከባለቤቱ ጋር ነው የሄደው ። የሀሰንን ኩብለላ መራራ ያደረገበት ነፍሰ ጡር የነበረች ሚስቱ ከመንገድ ላይ ወልዳ ሕፃኑ መሞቱ ነው ። በዚህ መልክ የሚሄዱ ሰዎችን ለማስተናገድ በሃይማኖት ድርጅቶች ፡ “አሸሀዱ” የሚባል መጠለያ ተዘጋጅቶ ይቀበል ነበር ። በርካታ ወገኖቻችን ተታለው ከሄዱ በኋላ እዚያ ያለው ኑሮ እንደተነገራቸው ሳይሆን መራራ ሆነ ። በዚህ ላይ ከተመለሳችሁ ትገደላላችሁ ፡ መኖሪያ አታገኙም እያሏቸው ብዙ ቆዩ ። በኋላ ግን በልዩ ልዩ ሁኔታ ሲከታተሉ ያለው እውነታና የሚነገራቸው የማይገናኝ ሲሆንባቸው ወደአገራቸው እየተመለሱ ገቡ ። ዛሬ በአዲሱ መንደር ያለው አዲስ ሕይወት ተቋዳሽ እየሆኑ ነው ። የመንደር ሕይወት በታቀደው ዓላማ መሠረት ያላሰለሰ ትኩረት ከተደረገበትና ከተተጋበት ፋይዳው ከቶ አጠያያቂ ሊሆን አይችልም ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈሐሳብና የተግባር ዕውቀት

ደስታ ወዳጆ

ሕዝባችን ከኋላቀር አኗኗር ፡ ከጉታች አስተሳሰብና አሠራር ተላቆ ለተደላደለ ዕድገት የሚበቃው ትምህርትን መሥሪያ አድርጐ በመጠቀም ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ትምህርት የአሮጌውን ሥርዓት ቅሪቶች በማፍረስና የአዲሱን ሥርዓት አካሎች በመገንባት ረገድ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የማፍረስና የመገንባቱ ተግባር በራሱ በትምህርትም ላይ ሲከናወን ነው ።

የአሮጌው ሥርዓት ትምህርት ፡ ቅርጽና ይዘት በሥርዓቱ መሣሪያነትና ነፀብራቅነት ያረጀ በመሆኑ ልንገነባ ከምንፈልገው ሥርዓተ ማኅበር ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም ። በመሆኑም አሮጌውን በአዲስ ለመተካት በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል ። ሆኖም ከግባችን አኳያ ገና ብዙ ይቀረናል ።

የምንገነባው አዲስ ሥርዓት የዜጐችን ሁለገብ ጥረትና ዕድገት የሚጠይቅ ነው ። ዜጐችን ለዚህ ለማብቃት ደግሞ አዲሱን ትውልድ በትምህርት ማነጽ ያሻል ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለሁለገብ ግንባታችን አስፈላጊ የሆኑትን ዜጐች ለማፍራት የፖሊቴክኒክ ትምህርትን አስፈላጊነትና ተግባራዊነት ማብራራት ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊነትና አመጣጥ

1· አጭር ትርጉም

የተለያዩ ሰዎች ለትምህርት የተለያዩ ትርጉሞችን ይሰጣሉ ። አንዳንዶቹ ትምህርት የዕውቀት ማግኛ ሂደት ነው ይላሉ ። ሌሎቹ ደግሞ ትምህርት የዕውቀት ማግኛ ሂደት ውጤት ነው በማለት ያቀርባሉ ። የመጀመሪያው የመማር ማስተማር ውጤትን የሚዘነጋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሂደቱን የማይገነዘብ ነው ። የሁለቱንም ድክመቶች ያስወገደው ትርጓሜ “ትምህርት የተቀነባበረ (Systematized) ዕውቀትና ክህሎት (Skill) የማግኛ ሂደትና ውጤት ነው ”[1] ይላል ። የፖሊቴክኒክ ትምህርት ትርጉም በዚህ አጠቃላይ የትምህርት ትርጉም ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ቢሆ

Proudly Brought to You

By

www.binyamhk.wordpress.Com

ዋጋው ብር 1.25

B.S.P.P



መስከረም

* ርዕዮተዓለምን በማዛባት የፕሮፓጋንዳ ሚና

* የድኅረ—ምንደራ ገጽታ በምሥራቅ ኢትዮጵያ

* የፖሊቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈ ሐሳብና የተግባር ዕውቀት

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 9 ቁጥር 36

ታኅሣሥ 1981

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ለተመዛዘነ የንድፈሐሳብና የተግባር ዕውቀት

ደስታ ወዳጅ

ሕዝባችን ከኋላቀር አኗኗር ፡ ከጐታች አስተሳሰብና አሠራር ተላቆ ለተደላደለ ዕድገት የሚበቃው ትምህርትን መሥሪያ አድርጎ በመጠቀም ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ትምህርት የአሮጌውን ሥርዓት ቅሪቶች በማፍረስና የአዲሱን ሥርዓት አካሎች በመገንባት ረገድ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የማፍረስና የመገንባቱ ተግባር በራሱ በትምህርትም ላይ ሲከናወን ነው ።

የአሮጌው ሥርዓት ትምህርት ፡ ቅርጽና ይዘት በሥርዓቱ መሣሪያነትና ነፀብራቅነት ያረጀ በመሆኑ ልንገነባ ከምንፈልገው ሥርዓተ ማኅበር ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም ። በመሆኑም አሮጌውን በአዲስ ለመተካት በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል ። ሆኖም ከግባችን አኳያ ገና ብዙ ይቀረናል ።

የምንገነባው አዲስ ሥርዓት የዜጎችን ሁለገብ ጥረትና ዕድገት የሚጠይቅ ነው ። ዜጎችን ለዚህ ለማብቃት ደግሞ አዲሱን ትውልድ በትምህርት ማነጽ ያሻል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለሁለገብ ግንባታችን አስፈላጊ የሆኑትን ዜጎች ለማፍራት የፖሊቴክኒክ ትምህርትን አስፈላጊነትና ተግባራዊነት ማብራራት ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊነትና አመጣጥ

1· አጭር ትርጉም

የተለያዩ ሰዎች ለትምህርት የተለያዩ ትርጉሞችን ይሰጣሉ ። አንዳንዶቹ ትምህርት የዕውቀት ማግኛ ሂደት ነው ይላሉ ። ሌሎቹ ደግሞ ትምህርት የዕውቀት ማግኛ ሂደት ውጤት ነው በማለት ያቀርባሉ ። የመጀመሪያው የመማር ማስተማር ውጤትን የሚዘነጋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሂደቱን የማይገነዘብ ነው ። የሁለቱንም ድክመቶች ያስወገደው ትርጓሜ "ትምህርት የተቀነባበረ (Systematized) ዕውቀትና ክህሎት (Skill) የማግኛ ሂደትና ውጤት ነው"[1] ይላል ። የፖሊቴክኒክ ትምህርት ትርጉም በዚህ አጠቃላይ የትምህርት ትርጉም ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ቢሆ

ንም ካፒታሊስቱም ሆነ ሌሎቹ ሶሻሊስት ያልሆኑ ሀገሮች ከሚከተሉት የትምህርት ስልት በዓይነቱ የተለየ መሆኑ የሚገለጽበት የራሱ የሆነ ተግባራዊ ትርጉም አለው።

ይህ የሚገለጸው ት ቤቶችን ከምርት ተቋማት ጋር እያቀናጁ በማቋቋምና ተማሪዎች የተወሰነ ጊዜ በምርት ተቋሙ በመገኘት በምርት ሥራ ላይ እየተሳተፉ የምርት ክህሎትን ፡ የሥራ ዲሲፕሊንንና የሠራተኛውን የቀን ተቀን ተግባራዊ ሕይወት እንዲማሩ በማድረግ ነው ።

ፖሊ የሚለው ቃል ፖሊ (Pole) ከሚል የግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ብዙ ማለት ነው ። በዚሁ መሠረት የፖሊቴክኒክ ትምህርት ስንል የብዙ ቴክኒኮች ትምህርት ወይም ብዙ መስኮችን ያቀፈ ትምህርት ማለታችን ነው ። በሌላ አገላለጽ በተወሰነና ጠባብ በሆነ የሙያ ትምህርት ፋንታ አንድ ሰው ስለልዩ ልዩ ቴክኒክና ሥራ አጠቃላይና መሠረታዊ ዕውቀትና ክህሎት የሚያገኝበት የትምህርት ስልት ነው ። በመሆኑም የፖሊቴክኒክ ትምህርት፡ ትምህርት ቤቶችን ከምርታማ ሥራዎች ጋር የሚያያይዝና የሳይንስንና የቴክኖሎጂን አጠቃላይ ዕውቀት የሚያስጨብጥ ነው ። [2]

ይህ ትምህርት ከቴክኒክ ሥራዎች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተማሪዎች በተለያዩ መልኮች ወደተለያዩ የማምረቻና የሥራ ድርጅቶች በመሄድ በሥራው ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። የትምህርቱም ዓላማ በሁሉም የሥራ መስኮች የመሥራት ልምድን ፡ መሠረታዊና አጠቃላይ ዕውቀትንና ክህሎትን ለሁሉም ተማሪዎች ማስገኘት ነው ። ለምሳሌ ትራክተር መንዳትን ፡ ልዩ ልዩ ማሽኖችንና ተሽከርካሪዎች ማንቀሳቀስን ፡ በእርሻ ቦታዎች በመገኘት ውጤታማ የሆኑ ሥራዎች መሥራትንና ሌሎች ልዩ ልዩ የምርትና የአገልግሎት ተግባራት ማከናወንን የሚያጠቃልል ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው ፡ ችሎታቸውና ዝንባሌያቸው ለወደፊቱ የሚሠማሩበትን የሙያ ዓይነትና መስክ ከወዲሁ መገንዘብና መምረጥ ይችላሉ ። ባጭሩ የፖሊቴክኒክ ትምህርት 1 ስለሠራተኞች ሙያና ሥራ የተወሰነ ዕውቀትና ልምድ ለተማሪው የሚያስገኝ ፡ 2 ተማሪው ለሥራ ልዩ ፍቅርና ክብር እንዲኖረው የሚያደርግ፡ ስለብሔራዊ ዕድገትና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ሂደት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያገኝና በሶሻሊስት የሥራ ሞራሊቲ እንዲታነፅ የሚያደርግ ፡ 3 በጋራ (በወል) የመሥራት ልምድ እንዲያገኝና ከዚሁ የሚገኘውን ትርፋማ ውጤት እንዲገነዘብ የሚያስችል ነው ። [3]

2· አስፈላጊነቱና አመጣጡ

የፖሊቴክኒክ ትምህርት በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ በሰፊው ሥራ ላይ ውሏል ። በእነዚህ ሀገሮች የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድ ነው? የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊ ነው ስንል ቀድም ሲል የነበረው የትምህርት ይዘት ፡ የአሰጣጥ ስልትና ክንዋኔው የተሟላ አይደለም ወይም አርጅቷል ፡ ወይም ከእነዚህ ሀገሮች የዕድገት ፍላጎት ጋር የማይጣጣም ነው ማለታችን ነው ። ነገር ግን አሮጌው የትምህርት ስልት ለማርጀቱ ምን ማስረጃዎች አሉ ? ከሚል መንደርደሪያ መነሣቱ ተገቢ ነው ። የትምህርት ውጤት የሚለካው በሂደቱና በውጤቱ መጠን ብቻ ሳይሆን ከሁሉም በላይ ኢኮኖ

ሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ባለው ሚና ነው። ከዚህ መሠረተ ሐሳብ ተነሥተን ት/ቤቶች ወጣቱን ትውልድ የሚያዘጋጁት ለምንድነው ? ከውጤቶቻቸው ምን ያህሉ ለምርታማነት ወይም ለምርት ኃይልና ኢኮኖሚ ዕድገት ውለዋል ? በሌላ አባባል ባንድ ሀገር የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና በሚሠለጥነው የሰው ኃይል መካከል ምን ያህል መጣጣም አለ? ወይም ደግሞ ባንድ በተወሰነ ጊዜ ባንድ ሀገር ውስጥ የሚካሄደው ትምህርት የተፈለገውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በዓይነትም ሆነ በመጠን አስገኝቷል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሣት በሂደት ላይ ያለው የትምህርት ስልት ያለበትን ችግርና በአዲስ መተካት የሚያስፈልገው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው ።

ሰዎች የሚያድጉትና የሚኖሩት በሁለት ታላላቅ አካባቢዎች ውስጥ ነው ። አንደኛው፣ ተፈጥሮአዊ አካባቢ (መሬት፣ አፈር ፣ አየር ፣ የፀሐይ ብርሃን ፣ ጨለማ ፣ ደን ፣ ውኃ፣ የዱር እንስሳት ወዘተ.) ሲሆን ሁለተኛው ፣ ማኅበራዊ አካባቢ (ግለሰብ ፣ ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ ፣ መንግሥት፣ ብሔረሰብ፣ ወዘተ.) ነው ። ሰዎች መኖርና ማደግ የሚችሉት ከሁለቱም ጋር በሚፈጥሩት ተግባራዊና ንድፈ ሐሳባዊ ግንኙነት ነው ። ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተፈጥሮን በሚጠቅማቸው መልክ ለመለወጥና በተገኘውም ለውጥ ተጠቃሚ ለመሆን ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል ። ዛሬ የተደረሰበት የሰው ልጅ የዕድገት ደረጃ የተገኘው በረጅም ጊዜ እንቅስቃሴና ትግል ውስጥ ሰዎች በፈጠሩት ቁሳዊና ኅሊናዊ ሀብት ነው ። እንደየሥርዓተማኅበሩ ባሕርይ ይለያይ እንጂ ከኅሊናዊና ክህሎታዊ ሀብት አንዱ የሆነው ትምህርት በዚህ ሂደት ውስጥ የነበረውና ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ።

ትምህርት ሰዎች በአካባቢያቸው የሚገኘውን ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ክስተት በሚገባ እንዲረዱ ፣ የተፈጥሮንና የኅብረተሰብን ሕግጋት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ፣ በዚሁ ግንዛቤያቸው ላይ ተመሥርተው የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ ለውጦችን እንዲያራምዱና የምርት ኃይሎችን ዕድገት ማፋጠን እንዲችሉ የሚያደርግ መሣሪያ ነው ። በተጨማሪም ኅብረተሰቦች በተለያዩ ታሪካዊ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ ሲያልፉ የሚያካብቱትን ልምድና ቅርስ በማስቀመጥና በማስፋት ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፉበት ፣ አዲሱም ትውልድ የአሮጌውን ሥርዓት ቅርስና ዕውቀት ተቀብሎ በተራው የራሱን አዳዲስ ልምዶችና ግኝቶች በማከል የተሻለ ኅብረተሰብ ለመመሥረት የሚችልበት መሣሪያም ነው ።

በትምህርት ዓለም ውስጥ ትልቁ ነገር ሰው ነው ። የሂደቱ አከናዋኝ ወይም አድራጊና (Subject) ተደራጊ (object) ፣ በሌላ አገላለጽ ዕውቀት ሰጭውና (መምህር) ፣ ተቀባዩ (ተማሪ) ሰው ነው ። የመጀመሪያው ተፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል የሚያፈራ ኃይል ሲሆን ሁለተኛው በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ በማኅበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ ፣ በፖለቲካዊና ባህላዊ መስኮች ረገድ ከተቀረው ኅብረተሰብ የተሻለ ድርሻ እንዲያበረክት ሲባል በተወሰነ ዕውቀትና ክህሎት የሚሠለጥን ወይም የሠለጠነ የሰው ኃይል ነው ። ከዚህ አኳያ የትምህርት መሠረታዊ ግብ ወጣቱን ትውልድ በርዕዮተ ዓለማዊና በሳይንሳዊ ዕውቀት በማነፅ ማኅበራዊና (Socialize)ምርታማ ማድረግ ነው ።

ይሁን እንጂ ትምህርት በዚህ መልኩ በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ ያለው ሚና እንደየሥርዓተማኅበሩ ባሕርይ የሚለያይ ነው ። ማንኛውም ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ከተደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር በተለያዩ አካላት የሚዋቀር ነው ። ከእነዚህ ውስጥ ዋንኞቹ መሠረትና (basis) ላዕላይ መዋቅር (Superstructure) ናቸው ። ትምህርት እንደየሥርዓተማኅበሩ ባሕርይ በመሠረት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ተግባርን ለማከናወንና በላዕላይ መዋቅር ውስጥም በርዕዮተዓለም መሣሪያነት የሚያገለግል ነው ። በርዕዮተዓለማዊ ሚናው የሚያንፀባርቀው የኅብረተሰብን የምርት ግንኙነት ሲሆን በኢኮኖሚያዊ ተግባሩ ደግሞ ኅብረተሰቡ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ያመለክታል ። በእነዚህ ሁለት ሚናዎቹ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት የሚወሰነውም በሥርዓተማኅበሩ ባሕርይ ነው ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ትምህርት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ሚና በላዕላይ መዋቅር ውስጥ በርዕዮተዓለም መሣሪያነቱ ካለው ሚና ዝቅ ያለ ነው ። በዚህ ዓይነት ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ የሚቀረጽ ትምህርት የተሟላና የተመዛዘነ ስብዕናን መፍጠር አያስችልም ። ለዚህ ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል ።

አንደኛው ፣ እንዲህ ባለ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የተወሰኑ የሥራ ዓይነቶችን የሚያጋንን፣ ሌሎችን ደግሞ የሚያንኳስስ መሆኑ ነው ። የግል የምርት መገልገያ መሣሪያና ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ በአእምሮታዊና በጉልበት ሥራ መካከል ልዩነትና ርቀት ጎልቶ ይታያል ። ችግሩ ልዩነቱና ርቀቱ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ የሥራ ዓይነቶች የሚሰጠው ግምት የተለያየና ተቃራኒ መሆኑም ነው ። በኢኮኖሚ የበላይ የሆነው በዝባዥ መደብ በፖለቲካና በርዕዮተዓለምም የበላይ ነው ። በዚህ ምክንያት አእምሮታዊ ሥራ ዋጋና ክብር ያለው ፣ የግለሰቦችን ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ የሚጠይቅና የምርጥ ሰዎች ተግባር ሆኖ ስለሚታይ በዕድገት ሂደት ውስጥም ታሪክ ሠሪ ፣ ወሳኝና ቀዳሚ ኃይል በመሆን ይተርባል ። ባንፃሩ የጉልበት ሥራ የማይም ወይም የዝቅተኛ ኅብረተሰብ ክፍል ተግባር ሆኖ ይወሰዳል ። ከዚህ አኳያ ትምህርት በርዕዮተዓለም መሣሪያነቱ (በላዕላይ መዋቅር አካልነቱ) እጅግ የገነነና የጐላ ሚና ሲኖረው በኢኮኖሚ ውስጥ ግን ዝቅተኛና ውስን ድርሻ ይይዛል ።

ሁለተኛው ፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ባለው የምርት ግንኙነት ምክንያት የግለሰብ ችሎታዎች የሚዳብሩት ውስንና ጠባብ በሆነ መንገዶች መሆኑ ነው ። ግለሰብ በብዙ መንገዶች ሊዳብሩ የሚችሉ ችሎታዎች አሉት ። ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ሕጎችን ጠንቅቆ ለማወቅ በአእምሮው መብሰል አለበት ። ይህ ግን ብቻውን የተሟላ ስብዕናን አያስገኝለትም ። ያገኘውን ዕውቀት ወደተግባር ለመተርጐም እንዲችል ከምርት ሥራ ጋር መለማመድ ይኖርበታል። የአእምሮ ዕውቀቱን ከተግባራዊ ልምዱ ጋር አቀናጅቶ ለመሥራት አካላዊ ብቃት ፣ የሞራልና የሥነልቡና ዝግጅት ሊኖረው ይገባል ። የእነዚህ ሁኔታዎች ቅንጅት ለተሟላ ስብዕና መገኘት መሠረታዊ ጉዳይ ነው ። ነገር ግን ብዝበዛ ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ትምህርት እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎች አሟልቶ የሚገኝ ግለሰብ አይፈጥርም ። ይልቁንም በግለሰቡ ውስጥ የሚቀረጹት የሚቃረኑ እስተሳሰቦች (በአእምሮታዊ ዕውቀቱ ተግባርን ወይም በተግባር የአእምሮውን ዕውቀት የሚቃረን ይሆናል)

ናቸው ።

ከላይ እንደተገለጸው በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚቀረጸው ትምህርት ባጠቃላይ መልኩ በተግባርና በንድፈ ሐሳብ ፣ በአእምሮታዊና በጉልበት (በምርት) ሥራ መካከል ልዩነትን እንጂ አንድነትን ፣ ርቀትን እንጂ ቅርበትን የሚፈጥር አይደለም ። እርግጥ በጣም ውስን በሆነ መስክና መልክ (በተለይ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር) በሁለቱ መካከል አንድነትና ውህደት መፈጠሩ የሚካድ አይደለም። ትምህርት በዚህ መልኩ ባብዛኛው ጠቀሜታ ባለው የምርት ተግባር ላይ መዋል የጀመረው በካፒታሊዝም ውስጥ ነው ። ይህም ያለምክንያት አልነበረም ፣ አይደለምም ። በነባራዊ ማኅበረ—ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አኳያ ቡርዧው የሠራተኛውን መደብ ጉልበት በመበዝበዝና የተፈጥሮ ሀብቶችን በመሻማት የትርፍ ማጋበስ ዓላማውን የሚያሳካው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች መጠቀም ሲችል ብቻ ነው ።

ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ ትምህርት ሳይንሳዊ ዕውቀት የሚሰጥበት ሂደት ነው። ሳይንስ ደግሞ ባዳዲስ ግኝቶች ትምህርትን የሚያዳብር ከመሆኑም ሌላ ሳይንሳዊ ዕውቀቶች በቁሳዊ ውጤቶች የሚገለጹበትን ተጨባጭ መንገድና ስልት የሚያሳይ ነው ።[4] ባጭሩ የትምህርት ልዩ ተግባር ሳይንሳዊ ዕውቀትን መቀበልና በተግባር መተርጐም የሚችሉ ሰዎችን ማሠልጠን ሲሆን የሳይንስ ተግባር ደግሞ ለትምህርት መዳበር አዳዲስ ግኝቶችን መፍጠር ነው ።

ሁለቱም የሚገናኙበት የጋራ መሠረት ተግባር (ሥራ) ነው ። የሳይንስ መሠረታዊ ዓላማ የሥራን ምርታማነትና ውጤታማነት ማዳበር ነው ፣ የትምህርት ደግሞ በሳይንሳዊ ዕውቀት ታንፀው ምርታማና ውጤታማ የሚሆኑ ሰዎችን ማስገኘት ነው። በዚሁ መልኩ ነው ትምህርት በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ ከምርት ሥራዎች ጋር መቆራኘት የጀመረው ። ይሁን እንጂ የምርት ግንኙነቱ መሠረት የግል ይዞታ ሆኖ እስከቆየ ድረስ ሥርዓተማኅበሩ ትምህርትንና የምርት ሂደትን በተሟላ መልኩ ማቀራረብና ማዋሃድ (ምክንያቱም የተሟላ ስብዕና ያለው ሰው ስለሚፈጥር ውስን ሆኖ መቆየቱ ይመረጣል) አይችልም ። ይልቁንም በዲበአካላዊ (metaphysical) ስልቱ (ከአካላዊና ቁሳዊ ሁኔታ ባሻገር በረቀቀ ሁኔታ ላይ በማተኮር ስልቱ) ልዩነታቸውንና ርቀታቸውን የሚያጐላ ነው ።

የሥራ ሂደት የተቀናጀና (Integrated) የተቀነባበረ (Systematized) ነው ። ቅንጅትና ቅንብር ደግሞ አንድ የሥራ ሂደት ወይም ሥርዓት የተዋቀረባቸውን አካላትና (ኃይሎች ፣ ነገሮች ፣ ክስተቶች) የእነዚህን አካላት ውስጣዊ ተዛምዶ ወይም ዲያሌክቲካዊ ግንኙነትን የሚያመለክቱ ናቸው ። ይህንን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የማይረዳና ዲበአካላዊ ስልትን የሚከተል ትምህርት አለ ። በአኳያውም በዲያሌክቲካዊ ስልት በመጠቀም የግንኙነቱን ትክክለኛ ባሕርይና ሕግ የሚያመለክት ትምህርት አለ ። የመጀመሪያው ስልት በነገሮች የውጭ ገጽታ የተናጠልና ተናክአታዊ (mechanical) ግንኙነት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ሁለተኛው በነገሮች ምንነት፣ ሁለንታዊና ውስጣዊ ግንኙነት ላይ የሚያተኩር ነው ።

ብዝበዛ ባለባቸው ሀገሮች ውስጥ የትምህርት መሠረታዊ ስልት ዲበአካላዊ ነው ። የዚህ ዓይነቱ የትምህርት ስልት በሥራ ላይ ባዋለባቸው ሀገሮችና ሥርዓተማኅበራት

ውስጥ በተለያዩ ሥራዎች መካከል በሚፈ
ጠረው ልዩነትና ርቀት የተንግ ሰዎች ለተ
ሻለ የትምህርት ስልት መታገላቸው የግድ
ነው ። በመሆኑም የፖሊቴክኒክ ትምህርት
የተከሰተው በሰዎች በጐ ፍቃድና ፍላጐት
ሳይሆን አስገዳጅ በሆኑ ማኅበራዊ ሁኔታ
ዎች ምክንያት ነው ።

ፊውዳሊዝም ተወግዶ ካፒታሊዝም በተ
ተካበት ጊዜ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገትና
ተጽዕኖ ምክንያት ትምህርት በምርት ሂደት
ውስጥ ያለው ሚና ጉልህ እየሆነ መጣ ።
በማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ግፊት ምክንያት
በ16ኛው ፡ በ17ኛውና በ18ኛው
ምዕት ዓመታት በርካታ ፈላስፎች ንድፈሐ
ሳብ ከተግባር ጋር መገናዘብ እንዳለበት
አበክረው ገለጹ ። በተለይም እንግሊዛዊያኑ
ቶማስ ሞርና ፍራንሲስ ቤከን ፤ ፈረንሳዊው
ቶማስ ካምፖኒላ የተጣጣመና የተስተካከለ
የኅብረተሰብ ሥርዓት ለማምጣት ለሕፃና
ትም ሆነ ለአዋቂዎች አእምሮታዊና አካላዊ
ትምህርት መስጠት እንደሚያስፈልግ አመ
ልክተዋል ።[5] በት ቤቶችና በሰዎች ሕይ
ወት መካከል የነበረው ልዩነትና ርቀትም
እንዲወገድ አሳስበው ተመሳሳይና አንድ
ወጥ ትምህርት ለሁሉም መዳረስ እንዳለ
በት ገልጸዋል ። ፈረንሳዊው ቻርለስ ፋዩርና
እንግሊዛዊው ሮበርት አውንም ለአዲስና
ለተሻለ ኅብረተሰብ መመሥረት የትምህር
ትና የሥራ መገናኘት አስፈላጊ የሆነ
ቅድመ ሁኔታ ነው በማለት አስተምረ
ዋል ።[6] በተለይ አውን በላናርክ (አሚሪካ)
በነበረው ፋብሪካ ውስጥ ት ቤትንና የም
ርት ሥራን ለማዋሐድ የሚያስችል መርህ
ተግባራዊ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። በእርግጥ
የእነዚህ ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች የትምህ
ርት ጽንሰሐሳብ በወቅቱ ተራማጅ ቢሆ
ንም ከተምኔታዊ የኅብረተሰብ አመለካከታ
ቸው ጋር የተያየዘ በመሆኑ ከሐሳብ ወደ
ተግባር ሊሸጋገር አልቻለም ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት ማርክስና ኤንግ
ልስ ከነሱ በፊት የነበረውን ተራማጅ የት
ምህርት ሐሳብ ከአርጌውና ከኋላቀሩ ለይ
ተው በመውሰድ ከሳይንሳዊ የኅብረተሰብ
አመለካከታቸው ጋር በማገናዘብ ፖሊቴክ
ኒክ ትምህርት ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገት
አስፈላጊ መሆኑን ገለጹ ። የፖሊቴክኒክ
ትምህርት ጽንሰሐሳብን ለመጀመሪያ ጊዜ
የተጠቀሙበት ማርክስና ኤንግልስ ነበሩ ።
ማርክስና ኤንግልስ የፖሊቴክኒክ ትምህር
ትን አስፈላጊነት የገለጹትም በዲያሌክቲ
ካዊ ቁስአካላዊነት ላይ በመመሥረት የቡር
ዧውን ኢዲያሌክቲካዊ አመለካከት በመሄ
ስና ኢሳይንሳዊነቱን በማጋለጥ ነው ።

ሰዎች በምርት ሥራ ሂደት ውስጥ ይለወ
ጣሉ ፣ ያድጋሉ ። ለኅብረተሰብ ማደግ
እንቀሳቃሹ ኃይል የማምረት ተግባር ነው።
የምርት ኃይሎች ዕድገት ደግሞ ለሥርዓተ
ማኅበራት መለወጥና ወደላቀ ደረጃ ማደግ
ምክንያት ናቸው ።[8] በሌላ አገላለጽ ማርክ
ስና ኤንግልስ የፖሊቴክኒክ ትምህርትን
አስፈላጊነት ያመለከቱት የሰው ሕልውናና
ዕድገት መሠረት ሥራ ነው ከሚል መሠረ
ታዊ ጉዳይ ተነሥተው ነው ። በመሆኑም
በእነርሱ እምነት ማንኛውም የሰው ንቃት
፣ ዕውቀት ፣ ጥበብ ፣ ክህሎት ፣ እምነትና
እንቅስቃሴ ሥራን የሚያዳብር ፣ ወደላቀ
ደረጃ የሚያሸጋግርና ይበልጥ ፍሬያማና
ትርፋማ ሊያደርገው የሚችል መሆን አለ
በት ።

ማርክስና ኤንግልስ ይህን አዲስ የትምህ
ርት ጽንሰሐሳብ ያገኙት ከበጐ ፈቃድ
በመነሣሣት ሳይሆን በነበሩበት ማኅበረ
ኢኮኖሚያዊ ባሕርይ አኳያ ከቀመሩት የፍ

ልስፍና ፣ የኢኮኖሚና የታሪክ ሳይንስ በመነሻት ነው ። ክሩፕስካያ ማርክስ ስለፖሊቴክኒክ ትምህርት ሐሳብ አመጣጥና አስፈላጊነት ያስተማረውን ስታብራራ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ሐሳብና አስፈላጊነት የመነጨው በዘመናችን ከሚታየው የማያቋርጥ ለውጥና ዕድገት ካለው የቴክኖሎጂ ግስጋሴና ይህን ዕድገት ከሚገዙት ተጨባጭና ነባራዊ ሕጎች ነው [9] በማለት ገልጻለች ።

የዘመኑ እንዱ ባሕርይ የሆነው የከባድ ኢንዱስትሪ መስፋፋት ሠራተኛው ሁለንተናዊ ስብዕናው የተሟላ እንዲሆን በፖሊቴክኒክ ትምህርት የሠለጠነ ማለትም በማንኛውም ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ መሣሪያዎችን ማንቀሳቀስ የሚችልና የምርት ሥራን ሂደት አጠቃላይ ባሕርይ የሚያውቅ እንዲሆን ይጠይቃል ።

በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ “ፖሊቴክኒክ” የሚለው ቃል በወታደራዊ ተቋሞች ፣ ለሕዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋሞችና በኢንዱስትሪ ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች የቴክኒክ ሥልጠናን መስጠት ለሚችል አዲስ ዓይነት ትምህርት ቤት መጠሪያ ሆነ ። በ19ኛው ምዕት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ የፖሊቴክኒክ ት ቤቶች በብዙ የአውሮፓ ሀገሮች ውስጥ ተቋቁመው ነበር።[10] ነገር ግን በብዝበዛ ላይ በተመሠረተው የካፒታሊስት ምርት ግንኙነት ምክንያት የተሟላ ባሕርያቸውን መያዝ አልቻሉም ።

ማርክስና ኤንግልስ ይህን አስመልክተው ሰፊ ጥናት በማድረግ ማብራሪያ ሰጥተዋል ። ኢንዱስትሪ መስፋፋት ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ቁሳዊ ምርት የማስገኘቱ ሂደት መፋጠንና የማያቋርጥ መሆን ሠራተኛው ራሱንና ቤተሰቡን ማኖር የሚያስችለውን ሥራ ላለማጣት በየጊዜው የሚያድገው የፋብሪካዎች የምርት ሥራ ሂደት የሚጠይቀውን ሙያ ማግኘትና ከሚመጣው ለውጥ ጋር አብሮ በመለወጥ የማምረት ችሎታውን ማሳደግ አለበት ። ችግሩ የሚመነጨው ግን ከአዳዲስ የምርት መሣሪያዎችና ሂደቶች ጋር ከመተዋወቁ ሳይሆን እጅግ ውሱንና ጠባብ በሆኑ ሙያዎች ብቻ ከመወሰኑ ነው ።

አሠሪው ካፒታሊስት ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስና ሕልውናውንም ለማረጋገጥ ሲል ሠራተኛው የማምረት ክህሎትና ችሎታ እንዲኖረው ለማድረግ ተገደደ ።

ካፒታሊስቱ ሠራተኛው ከአዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች ጋር የሚተዋወቅበትና አዳዲስ የማምረት ዕውቀትንም መገብየት የሚችልባቸው ት/ቤቶችን ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ትምህርት ቤቶች አንድ የተወሰነ ሙያ ለማስጨበጥ በሚያስችላቸው መልክ እንዲደራጁ አደረገ ።[11] የትምህርቱም ስልት ካፒታሊስቱ 1) ምርታማና ውጤታማ የሚሆን ሠራተኛን ፣ 2) ሳይንስና ቴክኖሎጂን በይበልጥ የሚያሳድግ ባለሙያንና 3) ለሥርዓቱ ቅንና ታማኝ የሆኑ ኃይሎችን የሚያፈራበት ነው ።[12]

በዚህ መልክ በተገኘው የሠለጠነ የሰው ኃይል አማካይነት ፋብሪካዎች ተስፋፉ ፣ ማሽኖችም ፈጣን ለውጥና ዕድገት አደረጉ፣ ከዚሁ ጋር የሥራ ክፍፍሉ በጣም እየጠበበ መጣ ። አንድ ሠራተኛ በአንድ በተወሰነ የማሽን ክፍል ብቻ ተወስኖ እንዲሠራ ተገደደ ። ይህ የሠራተኛውን ችሎታና ክህሎት ከማጥበቡም ሌላ ሥራውንም እጅግ የሚያስለች አደረገ ። የሠራተኛውን አካላዊና አእምሮታዊ ዕድገት የሚያቀጭጭ ፣ ምርታማነቱንም የሚቀንስ ሆነ ። አመለካከቱንም ውስንና የማሽኑ አንድ አካል ብቻ እንዲሆን አደረገው ።

ከዚህ ዓይነቱ የትምህርት ስልት የተገኘው የሠለጠነ የሰው ኃይል በተለያዩ የሕይወት መስኮች መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የማያገናዝብ በመሆኑ ባብዛኛው የአእምሮ ሥራን ፤ አልፎ አልፎም የቴክኒክ ሥራን ከሚገባው በላይ የሚያጕላ ይሆናል ። ትልቅ ግምት የሚሰጠው ለቢሮና ለወረቀት (ለአእምሮ) ሥራ ስለሆነ ከልዩ ልዩ የምርት ሥራና ሂደት ጋር የሚደረገው ግንኙነት ባብዛኛው በቀላጠ ብቻ የሚወሰን አስተዳደራዊ ግንኙነት ነው። የአእምሮ ሥራ የምርት ሂደት ዋነኛ አካል መሆኑ ቀርቶ ከሂደቱ ውጭ ያለ ባዕድ አካል ሆኖ አመራር ይሰጣል ፤ አሠራርን ያደረጃል ። ባንፃሩ የጉልበት ሥራና ተግባር ልዩ የሆነና የጠለቀ ዕውቀት የማይሹ ወይም በልምድ ብቻ የሚገኙ በማስመሰል ዝቅ ያደርጋቸዋል ። ለማናቸውም ሙያ ነክና የጉልበት ሥራ ያለው አስተሳሰብ ይኸው ነው ። ሁለተኛው ደግሞ በታሪክ ውስጥ በጣም ጕልቶ የሚታይ ባይሆንም የቴክኒክ ክህሎትን በማጋነን አእምሮታዊ ሥራን ዝቅ ያደርጋል ። የዚህ ዓይነቱ የሰው ኃይል ምርታማነትን ለማሳደግ ፤ የፈጠራ ችሎታንና የቴክኒክ አቅምን ለማዳበር ያለው ሚና ዝቅተኛ ነው ። የትምህርቱ ስልት በብዙ መልኮች ሊዳብሩ ይችሉ የነበሩ ችሎታዎቹን የገታበት መሆኑንም አይረዳም ። ከዚህ መሠረታዊ ችግር የመነጩ ችግሮች ብዙ ናቸው ።

በዚህ ዓይነቱ ትምህርት የሚቀረጹት ዜጎች መማርን የሚመለከቱት የኅብረተሰብ ዕድገትን ለማፋጠን የሚረዳ ዓይነተኛ መሣሪያ አድርገው ሳይሆን ለራሳቸው (ለግለሰቡ) ልዩ ጥቅም የማስገኛ መንገድ አድርገው ስለሆነ ለኅብረተሰቡ የሚያበረክቱት ድርሻ የሚያስመካ አይሆንም ። ከኅብረተሰቡ ስለሚከፈላቸው ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ፤ አገልግሎት ስለሚሰጡ ብቻም የሚከፈላቸው ይመስላቸዋል ። የሚያሳስባቸው የሚያገኙት ጥቅም መጠንና ዓይነት እንጂ ከሚያገኙት አንፃር ለኅብረተሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አይደለም ፤ ወይም እነርሱ የሚያገኙት ጥቅም ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ያነሰ ይሁን እንጂ አስተዋጽኦቸው ከጥቅማቸው ቢያንስ ብዙም የሚሰማቸው አይሆኑም ። ከሁሉም ጕልቶ የሚታያቸው እነርሱ የሚፈልጉትን ዓይነት ሕይወት መኖር እንጂ ሀገሪቱ የምትፈልግባቸው ግዴታ አይደለም ።

እዚህ ላይ መነሣት የሚኖርበት ጥያቄ አለ ። ግለሰብን ኰትኩቶ የሚያሳድገው ማነው? ያለምንም ጥርጥር በመንግሥት አማካይነት ኅብረተሰቡ መሆኑ ይታወቃል። ግለሰቡ የሚማረውስ ለራሱ ነው ወይስ ለኅብረተሰብ ነው? ዐቢዩ ጥያቄ ይህ ነው ። በብዝበዛ የምርት ግንኙነት ላይ በተመሠረቱ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ግለሰቡን የሚያስተምረው ኅብረተሰብ ነው። ግለሰቡ በዕውቀቱ የሚያገለግለው በዓላማ ጠቅላላ ኅብረተሰብን ፤ በተግባር ግን ጥቂት የገዥ መደብ አባላትንና በዚያውም ራሱን ነው ። በዚህ መልክ የትምህርት ስልት በግለሰብና በኅብረተሰብ ፍላጐቶችና ጥቅሞች መካከል የሚያፃርር ይሆናል ።

በትምህርት ባለሙያዎችና በኢኮኖሚስቶች ግምት ትምህርት ለብሔራዊ ዕድገት አስፈላጊ የሆነ ሙዓለንዋይ ነው ።[13] በአግባቡ ከተያዘና ሥራ ላይ ከዋለ ብሔራዊ ዕድገትን ለማፋጠን የሚያስችል ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ በዛሬው ዓለም የትምህርት ዋና ዓላማም ይኸው ነው ። ነገር ግን በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ የምርት ግንኙ

ንት ባሕርይና አንድ ኅብረተሰብ ካለበት ኋላቀርና ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ አኳያ በሚቀረጸው የትምህርት ሥርዓት ምክንያት ትምህርት ቤቶችና ትምህርት ለማይፈለጉ ማኅበራዊ ችግሮች ምንጭ የሚሆኑበት ሁኔታዎችም አሉ ። እንዲህ ዓይነቶቹ ችግሮች ብዝበዛ ባለባቸው ሀገሮች ውስጥ ሰፍነው የሚታዩ ቢሆንም በሠለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦትና በዚህ ኃይል ለመጠቀም ባለ ብሔራዊ አቅም መካከል ያልተመጣጠነ ግንኙነት ባለባቸው ፣ ሶሻሊዝምን ግባቸው አድርገው በሚታገሉ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥም ጐልተው ይታያሉ ። ግልጽ ለማድረግ ፣ በሀገራችን የትምህርት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታየውን ተጨባጭ ችግር ወስዶ ማገናዘብ ይቻላል ።

ከአብዮቱ ማግሥት ጀምሮ በሀገራችን ውስጥ የትምህርት ዲሞክራሲያዊ ባሕርይ በከፍተኛ ፍጥነት እየዳበረ መጥቷል ። በቅድመ አብዮት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር 2,754 ፣ በዚሁ ደረጃ የመምህራን ቁጥር 18,644 ፣ የተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 859,831 ነበር ። በ1979 መረጃ መሠረት ግን በአብዮቱ ጊዜ የት ቤቶች ቁጥር ወደ 8,261 ፣ የመምህራን ቁጥር ወደ 55,037 ፣ የተማሪዎች ቁጥር ደግሞ ወደ 2,729,200 መድረሱ የሦስት እጥፍ ዕድገት መገኘቱን የሚሳይ ነው ።[14] የመለስተኛና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛትም ከፍ ከማለቱም ሌላ የሥርጭታቸው ሚዛናዊነትም (ለአዲስ አበባ ፣ ለኤርትራና ለሸዋ ያደላ የነበረ) እየተሻሻለ መጥቷል ።[15] በቅድመ አብዮት በ4 ት/ቤቶች ፣ በ161 መምህራን ከ1,960 ለማይበልጡ ተማሪዎች ይሰጥ የነበረው የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ባሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ስምንት ክልሎች በተቋቋሙ ት/ቤቶች ውስጥ በ444 አሠልጣኝ መምህራን ፣ ለ5,540 ተማሪዎች በ21 የሙያ ዓይነቶች ትምህርት ይሰጣል ።[16] ከዚሁ ጐን የጐልማሶች ትምህርት በመሠረት ትምህርት ዘመቻ ፣ በርቀት ትምህርት ፣ በማታ ትምህርት ፣ በጐልማሶች ማሠልጠኛ ጣቢያዎችና በተመጣጣኝ ቴክኖሎጂ መሠረታዊ ልማት አማካይነት እየተሰጠ ነው ። ይህ ሁሉ ጥረት የተደረገው በዓላማ ነው ። ትምህርት ለምርት ፣ ለምርምርና ለሶሻሊስት ንቃተ ኅሊና በሚል መርህ ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን ኅብረተሰብ ለመፍጠር በምናከናውነው የግንባታ ሂደት ውስጥ የተሟላ ስብዕና ያላቸውን ዜጐች ለመፍጠር ነው ። ውጤቱ ግን የተጠበቀው ብቻ አይደለም ። ከምንፈልገው በጐ ውጤት ጐን ችግሮችም ተከስተዋል ።

በዚህ ረገድ ካሉብን ችግሮች ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ጋር የተያያዘው እንደ አንዱ ችግር የሚጠቀስ ነው ። ተማሪዎች ለዚህ ፈተና ሲቀመጡ ከፈተናው በኋላ የሚገጥማቸው ከሁለት ነገሮች አንዱ መሆኑን ያውቃሉ ። አንደኛው ተፈላጊውን ውጤት አግኝተው ወደ ዩኒቨርስቲዎች ፣ ወደ ኮሌጆችና መሰል የሙያና የሥልጠና ተቋሞች መግባት ሲሆን ሁለተኛው በተወሰነ መልኩ ቢሆንም ለሥራ አጥነት መዳረግ ነው ። የተፈለገውን ውጤት አጥተው ከትምህርት ዓለም የሚገለሉ ተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ከሚስተናገዱት ተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ ነው ።

ይሁን እንጂ ብሔራዊ ፈተናን ተቀብሎ ከትምህርት ቤት የሚገለለው ሁሉ ተፈላጊውን የማለፊያ ነጥብ ያጣ ብቻ አይደለም ። ይልቁንም በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች መስተናገድ ያለባቸው ተማሪዎች ቁጥር ከተቋሞቹ አቅም ውጭና በላይ መሆን

ነው። በአኳያውም ይህን የሥራ ኃይል በቀጥታ ተቀብሎ ሥራ ላይ ማሰማራት የሚችሉ የሥራ ፣ የምርትና የአግልግሎት ተቋሞች በስፋት የሉም ። ቢኖሩም ት/ቤቶቻችን ተማሪዎችን ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ አዘጋጅተዋቸዋል ማለት አይቻልም ። በዚህ ምክንያት ባብዛኛው በግብርናና በተለያዩ የምርት ተቋሞች ውስጥ ሥራ ላይ ከተሰማራው የሥራ ኃይል የተሻለ ጉልበትና ዕውቀት ያለው ወጣት ሥራ እጥ ይሆናል ። የተወሰኑት ለራሳቸው ችግር የሚሆን መፍትሔ በግል ጥረታቸው የሚያገኙ ቢሆንም የተቀረው ሀገሩን ለማገልገል አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ራሱን በራሱ ማኖር ስለማይችል ያለው ዕድል በወላጅ ፣ በዘመድና በሀገር ላይ ጥገኛ መሆን ወይም በአስነዋሪ ተግባራት ላይ መሰማራት ነው ። ይህ ችግር ከዕቅድ በላይ ሰውን ከማስተማር የመጣ ወይም ከተማረው ድክመት የመነጨ ሳይሆን የብሔራዊ ኢኮኖሚያችን አቅም ውስን መሆንና በሂደት ላይ ባለው የትምህርት ስልት ምክንያት ተማሪው ለሥራ ያለው የልምድ ፣ የሞራል ወይም የሥነልቡና ዝግጅት ድክመትም ነው ። ይህ ማለት ምን እንደሆነ በመጠኑ ማብራራት ያስፈልጋል ።

ተማሪዎች ትምህርትን ከአሮጌና ኋላቀር ማኅበራዊ አካባቢዎች ፣ ጠፍና አስቸጋሪ ከሆኑ ተፈጥሮአዊ አካባቢዎችና ከጉልበት ሥራዎች ለመሸሽ በመሣሪያነት እንደሚጠቅማቸው ይገምታሉ ። የትምህርቱም ሂደት በሚከተለው ስልት ምክንያት ይህን የተሳሳተ መነሻና ዓላማ እምብዛም አያርምም ። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ሰፊ የልማት ተግባር ሊከናወን የሚገባው በገጠር ነው ። ወደ ትምህርት ቤት የሚጎርፈው ወጣት በስፋት የሚመጣውም ከገጠር ነው ። የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚሸሸውም ይህንኑ ገጠሩን ነው ። በዚህ መልክ ገጠሩ የመልማት ዕድሉ ውሱን ይሆናል ። ምክንያቱም በጣም ንቁና ምርታማ በሆነ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለው ወጣት በትምህርት ሰበብ እየጣለው የሚሄድ ከመሆኑም በላይ የሠለጠነው የሰው ኃይልም ዘመናዊ በሆነ ውና በለማው አካባቢ መኖር (መሥራት) እንጂ ከከተማ ወጥቶ ኋላቀሩን ማኅበራዊ አካባቢ ለማልማትና ለማደራጀት ፈቃደኛነቱ እምብዛም ነው ። በአኳያው ወደ ከተማ ከፈለሰው የገጠር ወጣት መካከል በከተሞች ውስጥ ሥራ የሚያገኘው ሁሉም ስለአይደለ የተቀረው በሥራ አጥነት የሚንከራተት ይሆናል ። በመሆኑም በነበረውና ባለው የሥራ መስክ ላይ መጨናነቅ እንጂ ያልነበረውንና የሌለውን የሥራ መስክ መፍጠር አስቸጋሪ ይሆናል ፣ የሥራ ኃይል ግን እየጨመረ ይሄዳል ። በዚህ መልክ ወጣቱም የሠለጠነው የኅብረተሰብ ክፍል በተወሰነ መልክ ከምርታማ እንቅስቃሴ ውጭ ይሆናል ።

ሌላም የችግር ምንጭ አለ። እስካሁን ባለው የትምህርት ስልት ተማሪዎች የሚለኩበት ትልቁ መስፈርት በቀለም ትምህርት (በአንዳንድ ት/ቤቶች በሙያ ትምህርት ጭምር) ብቻ የተወሰነ ነጥብ ማግኘት ነው።

የትምህርት መስኩ በመጥበቡ የተማሪውን ችሎታ የምንለካው በጠባቡ ነው ። ሰው በሁሉም መስክ ተመሳሳይ ችሎታና ዝንባሌ ሊኖረው አይችልም ። ችሎታውም ባንድ ነገር ብቻ የሚለካ አይሆንም ። ባንድ መስክ የማይገለጽ ፣ ነገር ግን በሌላው መስክ ከፍተኛ ድርሻ ሊኖረው የሚችል ችሎታ ያለው ተማሪ አለ ። ለምሳሌ በቀለም ትምህርት ደካማ ሆኖ በቴክኒክ ትምህርት ወይም በሥራ ትምህርት ከጉበዝ የቀ

ለም ተማሪዎች ልቆ የሚገኝ ተማሪ ይኖ
ራል ። ለዚህ ዓይነቱ ተማሪ የቀለም እንጂ
የቴክኒክ (የሥራ) ትምህርት በሌለበት
መማርና ለፈተና መቀመጥ ምን እንደሚጠ
ብቀው ግልጽ ነው ። በዚህ መልክ ከት ቤት
የሚባረሩ ብዙ ዜጎች አሉ ።

የተማሪ በፈተና መውደቅ (ከፍተኛ ሁለ
ተኛ ደረጃን ሳያጠናቅቅም ሆነ አጠናቆ)
በብዙ መልኩ ጉዳት ነው ። በእርሱም ሆነ
በወላጆቹ ላይ የሚደርሰውን ሥነልቡናዊ
ችግር ትተን ከሀገር ዕድገት አኳያ ብንመለ
ከተው እንኳን በሁለት መንገዶች ጉዳት
አለው ። አንደኛ ፡ የመማር ማስተማር
ሂደት ያለወጭ የሚከናወን አይደለም ።

የት ቤት መምህራንና የአስተዳደር ሠራተ
ኞች ደመወዝ ይከፈላቸዋል ። ት ቤቱ
የሚሠራው ፡ በውስጡ ለትምህርት ሂደቱ
የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የትምህርት መሣሪያ
ዎች ሁሉ የሚገኙት በከፍተኛ ወጭ ነው ።
ይህም ማለት እያንዳንዱ ተማሪ ለት ቤቱ
ከተመደበው ወጭ የተወሰነ ድርሻ አለው ።
በሥራ እጦት ምክንያት ፡ ይህን ወጭ
መሸፈን የሚችል ግልጋሎት ለኅብረተሰቡ
ካላበረከተ የማኅበራዊ ዕድገት መሰናክል
መሆኑ ነው ። ሁለተኛ ፡ የተማረው መማር
የሚፈለገው ማኅበራዊ ችግር ለመፍታትና
የተሻለ ዜጋ ለመፍጠር ነው ። ከት ቤት
በኋላ ተማሪውን የሚገጥመው ሥራ አጥ
ነት ከሆነ ግን የትምህርቱ ዓላማና ውጤት
የሚቃረኑ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ማኅበራ
ዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚያበራክት
ነው ። ውጤቱ የተፈለገው መሆኑ ቀርቶ
ያልተፈለገው ይሆናል ።

በአብዮቱ ዓመታት በሀገራችን ለጥቂት
በዝባዥ መደብ አባላት የቆመውንና በዲበ
አካላዊ ስልት ላይ የተመሠረተውን የትምህ
ርት ስልት በመለወጥ በምትኩ ዲያሌክቲ
ካዊ የትምህርት ስልትን ለማዳበር ጥረትቢ
ደረግም የሚፈለገውን ውጤት ለማስገኘት
በትምህርት መስክና ከእሱ ጋር ግንኙነት
ባላቸው ሌሎች መስኮችም ሰፊ ጥረት ማድ
ረግ ያስፈልጋል ።

በትምህርት አሰጣጥ ስልታችን ውስጥ
ትልቁ ድክመት ተማሪዎች የሥራን ጽንሰ
ሐሳብ በስፋትና በጥልቀት እንዲያውቁ ፤
በምርት እንቅስቃሴ ውስጥም በተግባር
እንዲሳተፉ ማድረግ አለመቻል እንደሆነ
ይገመታል ። በብዙ ተማሪዎች አስተሳሰብ
የተማረ ሰው የሚሠራው የአእምሮ ሥራ
ብቻ ነው (በመንግሥት ተቀጥሮ ፡ ደመወዝ
ተከፍሎት በቢሮ ውስጥ የሚሠራ ነው ።)
በዚህ መልክ ፡ ዜጎችን ምርታማና በሳል
የማድረግ ዓላማ ያለው ትምህርት ዓላማ
ውን ስቶ ከልማትና ከምርት አካባቢዎች
የሚለቁበት መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ።

የዚህ ዓይነቱ ቁንጽል የሥራ ጽንሰሐሳብ
የዕድገት መሰናክል ነው ። ከሌላው ተለይቶ
የሚከበር ወይም የሚናቅ የሥራ ዓይነት
የለም ። ማንኛውም ሥራ (ሥራ እስከሆነና
በጐ ውጤት እስካገኘ ድረስ) ክቡር ነው ።
ት ቤቶቻችን ወጣቱን ትውልድ ከዚህ ቁን
ጽል የሥራ ጽንሰሐሳብ በማላቀቅ የተሟላ
ግንዛቤ እንዲኖረው ካላደረጉ ውጤቱ የምን
ፈልገውና የምንጠብቀው መሆኑ ቀርቶ
የሚያዳክመንና የሚጐዳን ይሆናል ።

ብዙ ተማሪዎች መማርን ሥራ የማግኛ
መንገድ ብቻ አድርገው የሚቆጥሩ ፤ በመሆ
ኑም ሥራ ካገኙ በኋላ (ሠራተኛ ሆነው)
አዳዲስ ዕውቀት ለማግኘት የማይጥሩና
ይልቁንም በተማሩትም በአግባቡ የማይጠ
ቀሙ ናቸው ። የትምህርት ዋና ዓላማ

የነበረውን ዕውቀት ለማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ለማመንጨት ፤ ያለን ሥራ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን በተሻለ ሠርቶ አዲስ ውጤት ማስመዝገብ የሚችል ኃይልና ሁኔታ መፍጠር ነው ። ለዚህ ደግሞ በት ቤት የሚሰጠው ትምህርት መሠረታዊ መነሻ ወይም ስልት ሆኖ የሚያገለግል እንጂ በራሱ ግብ አይደለም ። ት ቤትም ለመሠረታዊ መነሻነት የሚያገለግል ስልት መቅሰሚያ እንጂ ብቸኛ መማሪያ አይደለም ። ይልቁንም የሕይወት ሙሉ ት ቤት ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ናቸው ።

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሌላው ጠቃሚ ጉዳይ የተወሰነ ዕውቀት ከመስጠትና ከመቀበል ባሻገር የተማረውን የሀገር ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት ማዳበርም ነው ። በተወሰነ ዕውቀት ወይም ሙያ ብቁ ሆኖ መሠልጠን ብቻውን በቂ አይደለም ። በሀገራችን ውስጥ በብዙ የሥራና የመኖሪያ አካባቢዎች ቅንነትና ታማኝነት የጐደለው ተግባር ፤ የሥራ ዲሲፕሊን ጉድለት ፤ አድርባይነት ፤ ገለልተኝነትና የመሳሰሉት ጐላ ብለው ይታያሉ ። ከዚህ አኳያ ከችግሮቻችን ምንጭ አንዱ በሥራ ላይ የተሠማራው ኃይል ምግባረ ብልሹነት መሆኑ አከራካሪ አይደለም ።

ይህ ምግባረ ብልሹነት የሚመነጨው ከአሠራር ዝርክርክነት ፤ ከሥራ አመራርና ሥርዓት አደረጃጀት ጉድለት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ስልት ድክመት ምክንያት ዜጐች ውስጣዊ የሀገር ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት ገንብተው አለመገኘት ወይም የተሟላ ሰብዕና ያላቸው ሆነው አለመቀረጽም ነው ። ሰው ከተፈጥሮ ጋርም ሆነ እርስ በእርሱ በሚያደርገው ግንኙነት ምን ዓይነት ጠባዮች ፤ ድርጊቶችና ዝንባሌዎች ለሌሎችም ሆነ ለራሱ መልካም ነገሮችን እንደሚያስገኙና ምን ዓይነቶቹ ደግሞ ጉዳት ላይ እንደሚጥሉ ለይቶ ማወቅ ፤ መልካም ነገሮችን ማዳበር ፤ ጐጂ የሆኑትን ደግሞ ማስወገድ ይጠበቅበታል ። ከዚሁ አኳያ ደግሞ ትምህርት በተፈጥሮአዊ አካባቢ በአግባቡ መጠቀም ፤ እናት ሀገርን ማፍቀር ፤ የወል ሕይወትን መገንባት ፤ ለሕዝብ በቅንነትና በታማኝነት መሥራት፤ ኃላፊነትን መወጣት ፤ ሀገርንና ሕዝብን የሚጐዱ ማናቸውንም ተግባሮች አለመፈፀምና መከላከል የሚያስችል ሞራል በወጣቱ ትውልድ ሕይወት ውስጥ እንዲሠርፅ ማድረግ ይኖርበታል ።

ከላይ ከተጠቃቀሱት ችግሮች በመነሣት ነው ማርክስና ኤንግልስ ሠራተኞች እንዲኖራቸው የሚፈልገውን ክህሎት ብቻ አግኝተውና ሰዎች መሆናቸውን ክዶ የማሽኑ አካልና ተቀጥላ ሆነው እንዲቀሩ በሚያደርጋቸው የቡርዧው ትምህርት ፈንታ የሰዎችን የተሟላ ሁለንተናዊ ዕድገት በሚያስገኝ ትምህርት እንዲተካ ከፍተኛ ትግል ያደረጉት ። ለሰዎች የተሟላ የሰብዕና ዕድገት ለማስገኘት ትምህርት ከአጠቃላይ የምርት ተግባር ፤ ከአሠራሩና ከአደረጃጀቱ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ አጠቃላይ ዕውቀት በሚያስጨብጥ መልክ መቀየስ ይኖርበታል ።

ማርክስ የሠራተኛውን ልጆች ዕውቀትና ችሎታ ውስን የሚያደርገው የትምህርት ሥርዓት ተወግዶ የተለያዩ የሥራና የሕይወት መልኮችን ማሳወቅ በሚያስችል የትምህርት ሥርዓት መተካት እንዳለበት በማሳሰብ የሠራተኛ ልጆች ቴክኖሎጂንና የተለያዩ የሥራ መገልገያ መማሪያዎችን በማንቀሳቀስ ረገድ አስፈላጊውን ዕውቀት

እንዲያገኙ የቴክኒክና የእርሻ ት ቤቶች መፈጠር እንደሚያስፈልግ አስገንዝቧል ።[18] በ1864 ተመሥርቶ የመጀመሪያውን ጉባኤ በ1866 በጄኔቭ ያደረገው ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማኅበር ካሳለፋቸው ውሳኔዎች ውስጥ "ትምህርት ስንል ሦስት ነገሮችን እንረዳለን ። አንደኛው የአእምሮ ትምህርት ፤ ሁለተኛው የአካል ትምህርት ፤ ... ሦስተኛው የምርት ሂደት ጠቅላላ ትምህርት ነው ።"[19] የሚል ይገኝበታል ። ሕፃናት የሚገኙባቸው ት ቤቶች እነዚህን የትምህርት ባሕርያት አሟልተው መገኘት እንዳለባቸው ተጠቁሞበታል ። ቀደም ሲል ሕፃናት ሥራ እንዳይሠሩ ይከለከል የነበረው ትምህርትም ልክ አለመሆኑንና ከከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ዕድገት ጋር የማይጣጣም መሆኑንም አስታውቋል ።[20] ከዕድሜያቸው አኳያ የሥራ ዓይነቱንና ሰዓቱን መወሰን እንጂ ሕፃናት ሥራ እንዳይሠሩ ማድረግ የዕድገትና የኅብረተሰብ መሠረት ከሆነው ሥራ ጋር እንዳይተዋወቁ ማድረግና በብዙ መልክ መዳበርና ኃይሉን የሚሆነውን ችሎታቸውን ማፈን ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ይዘትና ተግባራዊነት

1. ይዘት

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ንድፈሐሳብንና የምርት እንቅስቃሴን በውሁድ በማስተማር ተማሪዎችን ከተለያዩ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፎች እንዲሁም ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ፤ የማምረቻ ድርጅት መሣሪያዎችና የአመራረት ወይም በአጠቃላይ የምርት ተግባር ሂደት ጋር የሚያስተዋውቅ ፤ በሂደትም ሰብዕናው የተሟላ አምራች ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ትምህርት ነው ። ይዘቱም ፤ የአሰጣጡም ስልት ከዚሁ ከትርጉሙ የሚመነጭ ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ንድፈሐሳብን በተግባር መመሪያነት ፤ ተግባርን ደግሞ በንድፈሐሳብ አመንጭነትና ይህንኑ ንድፈሐሳብ እውን ለማድረግ የሚጠቅም የትምህርት ሥልት በመሆኑ አሰጣጡም ከምርት አካባቢዎችና ከአመራረት ዘዴያቸው ጋር የተያያዘ ነው ። ተማሪዎች የተለያዩ የምርት ሥራዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች እየተገኙ ከሥራዎቹ ጋር እየተለማመዱና እየተማሩ ያመርታሉ ። ትምህርት ከምርት ሥራ ጋር ተጣጥሞና ተቀናጅቶ ሲሰጥ ተማሪዎች በንድፈሐሳብ የተማሩትን የቀለም ትምህርት በተግባር በምርቱ ሂደት ስለሚያረጋግጡት የሚሰጣቸው ትምህርትና አጠቃላይ ግንዛቤያቸው እየተጠናከረ ይሄዳል ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ይዘት ተማሪዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂን አጠቃላይ ሳይንሳዊ መሠረቶችና እንዲሁም በእያንዳንዱ የቴክኖሎጂ ውስብስብ ክፍሎች ውስጥ ያሉትን መሠረታዊ አሠራሮች እንዲያውቁ የሚያስችል ነው ። እነዚህን የቴክኖሎጂ መሠረታዊ አሠራሮች ከማወቅም ባሻገር የቴክኖሎጂን የወደፊት የዕድገት አቅጣጫ ለመገንዘብም ያስችላቸዋል ።[21]

ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ማወቅ በአንድ በኩል የተፈጥሮን ኃይል ከመቆጣጠር ጋር በተያያዙ ሳይንሳዊ ምርምሮችና ግኝቶች አንጻር በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ምርምር ፤ የሥራ አደረጃጀትና አደረጃጀቱ ከሰዎች ሕይወት ጋር ከሚኖረው አጠቃላይ ግንኙ

ነት አኳያ ተገናዝቦ መካሄድ አለበት ።
የዚህ ዓይነቱ ግንዛቤም ለተማሪዎች ተጨ
ባጭ በሆነ መንገድ መተላለፍ ይገባዋል ።
ባለው የሥራ አደረጃጀትና በዚህ አደረጃ
ጀት ውስጥ ቴክኖሎጂ ያለውን ሚናና ይህ
ሚናውም ከኅብረተሰቡ አጠቃላይ የእድገ
ቱና የዕድገት ፍላጎት ጋር የሚኖረውን
ግንኙነትና የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚ
ገባ እንዲረዱት ፤ ንድፈሐሳብንና ተግባርን
እያገናዘቡ በኢንዱስትሪዎችና በተለያዩ
የማምረቻ ተቋሞች የምርት ሥራ እንቅስ
ቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ወሳኝ
ነው። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ትምህርት
ለሰዎች ሕልውና አስተማማኝ የሆነውን
የሥራ ችሎታና ተግባራዊ ዕውቀት በሚያ
ስገኝ መልክ ሊሰጥ የሚችለው ።[22]

የፖሊቴክኒክ ትምህርትን ለተማሪዎች
ለመስጠት ት/ቤቶችና የምርት ተቋማት ፕሮ
ግራማቸውን ማቀናጀት አለባቸው ። ተማሪ
ዎች በምርት ሥራ ሂደት ውስጥ በሚሳተፉ
በት ጊዜ በት/ቤቶች የሚሰጠው የቀለም
ትምህርት ማለትም የተፈጥሮ ሳይንስ ፤
የማኅበራዊ ሳይንስና የሒሳብ ትምህርቶች
በፖሊቴክኒክ አጠቃላይ ይዘት ውስጥ እን
ዲንፀባረቁ ይደረጋል ። እነዚህ ትምህርቶች
በቀጥታ የምርት ዘርፎች ባይሆኑም የምርት
ተግባርን ትክክለኛ ግንዛቤ ለማግኘት ፤
በተግባር መመሪያ የሚሆን ንድፈሐሳብን
ለመቅሰም ፤ ለሕይወት ፤ በአጠቃላይ ለአካ
ባቢ ለውጥና ዕድገት የሥራን ወሳኝነት
ለማሳወቅ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል ።
የሒሳብ ትምህርት ሁለገብ ነው ። የተፈ
ጥሮ ሳይንሶች ለቴክኖሎጂ ንድፈሐሳብ
ምንጭና መሠረት ናቸው ። ማኅበራዊ
ሳይንሶች የኅብረተሰብ ዕድገት ሕጋጋትን
የሚያመለክቱና ሰዎችን በንቃት ላይ ለተ
መሠረተ ወገናዊ ተሳትፎ የሚያዘጋጁ
ናቸው ። እነዚህ ሁሉ የፖሊቴክኒክን ትም
ህርት ይዘትና ጥልቀት ሰፊና አጠቃላይ
ያደርጉታል።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ተማሪዎች በሳ
ይንሳዊና በቴክኒካዊ ተግባሮች ፤ በሕዝባዊ
ተሳትፎዎች ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ
በሚካሄዱ የምርት ሥራዎች ፤ ከልዩ ልዩ
አምራች ተቋሞች ጋር በሚደረጉ ግንኙነ
ቶች አማካይነት የሚካሄዱ የምርት ሥራ
ክንውኖችና የተለያዩ የአካባቢው ተጨ
ባጭ ሁኔታ በሚፈቅዷቸው እንቅስቃሴዎች
ሊከሰት ይችላል ።[23] የዚህ ዓይነቱን
የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ አስፈላጊ ከሚያደ
ርጉት በርካታ ምክንያቶች ሁለቱን መጥ
ቀስ ይቻላል ። አንደኛ ፤ ተማሪዎች በቀጥታ
በምርት ሥራ በመካፈል የምርትን ንድፈሐ
ሳባዊና ተግባራዊ ዕውቀቶችና ሂደቶች እን
ዲማሩ ያስችላል ፤ በዚህ መልኩ ትምህር
ትን ለትምህርትነቱ ብቻ የመማር ሁኔታ
ተጋኖ መታየት እንደሌለበትም የሚያስገን
ዝብ ይሆናል ። በሌላ አገላለፅ አእምሮታዊ
በሆነው የቀለም ትምህርት ላይ ብቻ ትኩ
ረት ማድረግ ሳይሆን ተማሪው ትምህርት
ለምርት የሚለውን መርህ በሚገባ በመረ
ዳት የቴክኖሎጂን ፤ የኢኮኖሚን ፤ የሥራ
አደረጃጀትን ፤ የአመራረት ሥርዓትንና
እነዚህ ሁሉ የሚገዙባቸውን መሠረታዊ
ሕጎች ተግባር ላይ በማዋል ሁለንተናዊ
የሆነ ዕድገት የሚያስገኝ ነው ። ሁለተኛ ፤
ወጣቱ ትውልድ የምርት ተግባርን ፤ የኅብረ
ተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና በነዚ
ህም አማካይነት የሚፈጠሩ ባህልና ልምዶ
ችን በንድፈ ሐሳብ ምንጭነታቸው እየተጠ
ቀመ እንዲያድግ ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ
ከሚገኘው ሠራተኛ ጋር በመሳተፍ የምርት
ሥራን አጠቃላይ ባሕርይ ከማወቁም ሌላ
የሠራተኛውን የሥራ ዲሲፕሊን ለመማር
ዓይነተኛ መድረክ መሆኑ ነው ።

2. ተግባራዊነቱ

ለፖሊቴክኒክ ትምህርት ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆነ ማኅበረ — ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መኖር አለበት ። ማርክስና ኤንግልስ በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የፖሊቴክኒክን ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ በሁለት የማይታረቁ ቅራኔዎች ምክንያት አስቸጋሪ እንደሚሆን ጠቁመዋል ። በእርግጥ የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የፖሊቴክኒክን ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ የሚያስችል መዋቅርና ቁሳዊ ኃይል አለው። ከፍተኛ ምርት የሚያስገኙ ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎች ስላሉት ሠራተኛውን ለሁለንተናዊ ዕድገቱ የሚያዘጋጅ ትምህርት መስጠት በተቻለ ነበር ። ይሁን እንጂ በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የማምረቻ መሣሪያዎች በጥቂቶች ከበርቴዎች በመያዛቸውና እነዚሁ ጥቂት ካፒታሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ለማግበስበስ ካላቸው ከፍተኛ ፍላጐት የተነሳ ለሠራተኛው መደብ ትምህርት የሚመድቡት ገንዘብና ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው ። ካፒታሊስቱ ሠራተኛውን የሚያስተምረው ትርፍ ማስገኘት በሚያስችል መልኩ ብቻ ነው ። በመሆኑም በቂ ገንዘብና የመማሪያ ጊዜ ስለማይመደብ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሁለንተናዊ ዕድገት የሚሰጥ ትምህርት ማለትም ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት በተሟላ መልኩ ለማደራጀትና ለመስጠት አይቻልም ።

የፖሊቴክኒክን ትምህርት በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ለመስጠት የሚያስቸግርበት ሌላ ዐቢይ ምክንያት አለ። ከዓላማውና ከይዘቱ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ነባራዊውን እውነታ የትምህርቱ ምንጭና ይዘት አድርጐ የሚነሣ በመሆኑ የተፈጥሮንና የኅብረተሰብን ዕድገትና ዕድገቱ የሚመራባቸውንና የሚገዛባቸውን ሕጋጋት ለተማሪዎች በግልፅ ያሳውቃል ። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት ለተማሪው (ኋላም ለሠራተኛው) የአካባቢውንና ከዛም ውጭ ያለውን ፖለቲካዊ ፡ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ማለትም ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን መገምገም ፡ ማጤንና መረዳት የሚያስችለውን ንቃተ ኅሊና ያስገኛል ። ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ያለው ሠራተኛ ደግሞ ቡርዧው ከሚፈልገው ሠራተኛ ማለትም በአንድ የፋብሪካ ክህሎት ብቻ የማምረቻ ማሺን ተቀፅላ[24] ሆኖ ዕድሜ ልኩን ከሚያገለግለው ሠራተኛ እጅግ በጣም የተለየ ይሆናል ። ስለዚህ በካፒታሊስቱ ዓለም የፖሊቴክኒክ ትምህርት ተሟልቶ የማይሰጥበት ምክንያት ቡርዧው ለዚህ ትምህርት ዕድገት በቂ ገንዘብና ጊዜ ለመመደብ ፈቃደኛ ሆኖ ካለመገኘቱ ሌላ ሠራተኞች ትርፍ ከማስገኘት የተሻለ የሚፈልጉበት ሁኔታ ስለሌለ[25] ሁለንተናዊ ስብዕናቸው የተሟላ ሆኖ የራሳቸውን ሁኔታ በመገምገምና በመጠየቅ ከፍተኛ የፖለቲካና ማኅበራዊ ንቃት እንዳያገኙና ምን ጊዜም ታዛዦችና ተበዝባዥ ሠራተኞች ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ ነው ።

በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ትምህርትም ሆነ ሥራ በተሟላ መልካቸው የሠራተኛውን የፈጠራ ስሜትና ችሎታ የሚያዳብሩና የሚናሣሡ ፡ ለሕይወትና ለኑሮው መሻሻል የሚረዱና የሚያገለግሉ ሊሆኑ አይችሉም። ይልቁንም ሠራተኛው ሥራን እጅግ በጣም አሰልቺና አድካሚ ፡ ለመኖር ሲል መፈፀም ያለበት የግዴታ ሸክም አድርጐ እንዲገ

ምት ያደርገዋል ። ይህ ደግሞ ሥራ የሰዎች፣
የልማትና የዕድገት ዋናው መሠረት መሆኑ
ቀርቶ ወይም ለሥራ ኃይሎች መሻሻልና
ማደግ ማገልገሉ ቀርቶ በተቃራኒው የሥራ
ኃይሎችን ዕድገት የሚጐዳ ፣ የሚያዳክምና
የሚገታ ይሆናል ከሚል ማጠቃለያ ያደር
ሳል ።

በትክክል በሚገነባ በሶሻሊስት ሥር
ዓተ ማኅበር ውስጥ ግን ሁኔታዎች የተለዩ
ናቸው ። ሠራተኛው የማምረቻ መሣሪያ
ዎች ወይም በአጠቃላይ የአገሩ ሀብት
ባለቤት በመሆኑ የሥራ ውጤቱም ተጠ
ቃሚ ነው ። ይህ ነባራዊ እውነታ ሠራተ
ኛው ስለ ሥራ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያገኝ
ያደርገዋል ። በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር
ሠርቶ አደሮች ሥራ ለሰዎች መለወጥ ፣
ማደግና አካባቢያቸውንም በሚፈልጉትና
በሚጠቅማቸው መንገድ ለመለወጥ የሚያ
ስችል የሕይወትና የኑሮ ማሻሻያ ፣ የሕልው
ናና የዕድገት መሠረት መሆኑን ያምናሉ ።
በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን ቁሳዊና ኅሊ
ናዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት ዋናው መሠረ
ትና አስተማማኙ ነገር መሥራትና ማም
ረት ብቻ መሆኑን ይረዳሉ ። በዕቅድ
መሠረት ለማምረት ፣ ከጊዜ ወደጊዜ ምር
ትን ለማሻሻልና ለማሳደግ ወሳኝ ሚና
ያላቸው መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን እንደማ
ንኛውም የኅብረተሰቡ አምራች አባል
በሥራ ፍሬያቸው ውጤት እኩል ተጠቃሚ
መሆናቸውንም ይገነዘባሉ ፤ በተግባርም
ያዩታል ። በዚህ ምክንያት ሠርቶ አደሮች
በተለያዩ ዘዴዎችና የፈጠራ ችሎታዎች
በመጠቀም በየጊዜው ምርትን ለማሳደግ
ያላቸውና የሚኖራቸው ሥነ ልቡናዊ ዝግ
ጅት ከፍተኛ ነው ።

የሶሻሊስት ሥርዓት ትምህርት ዓላማ ፡
ይዘትና ባሕርይ ከላይ እንደተገለጸው የኅብ
ረተሰቡን ቁሳዊና ኅሊናዊ ፍላጎቶች ለማሚ
ላት ካለው ዓላማ ይመነጫል ። ፍላጎቶችን
ለማሚላት ደግሞ ሰዎች መሥራት አለባ
ቸው ። የሥራ አካባቢን በሚጠቅም መን
ገድ ለውጦ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማር
ካት ሰዎች አካባቢያቸውንና በውስጡም
ያሉትን ነገሮች አመጣጥ ፣ ተፈጥሮአዊና
ውስጣዊ ባሕርያቸውንና በአካባቢው ሊያ
ስከትሉ የሚችሉትን ለውጥ ጠንቅቀው
ማወቅ አለባቸው ። ለዚህ ዓይነቱ ግንዛቤ
መዳበር ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው ።
የትምህርቱ መነሻ መሠረትና የይዘቱ
ምንጭ የሰዎች ነባራዊ ሕይወትና የአኗኗር
ሁኔታ ነው። ለዚህ ነው በሶሻሊስት ሥር
ዓተ ማኅበር የትምህርትና የማንኛውም
ዕውቀት መሠረትና ምንጩ ነባራዊው
ዓለም ፡ የሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ፡ ሰዎቹ
አካባቢያቸውንና ተፈጥሮን በሚጠቅማቸ
ውና ለሕልውናቸው ዋስትና ሊሆን በሚ
ችል መልኩ ለመለወጥ የሚያደርጉት ተግ
ባራዊ እንቅስቃሴ የሚሆነው ።

ሰዎች በየፈርጁ የሚያደርጉት የማያቋ
ርጥ የምርት ተግባርና የዕለት ተዕለት እንቅ
ስቃሴ ለትምህርት መሻሻል ፡ ማደግና
ጥራት ማግኘት መሠረት ነው ። ያንኑ ያህል
ትምህርትም ለሰዎች ሥራ መሻሻል ፡
ጥራት ማግኘትና በሳይንስና ቴክኖሎጂ
መታገዝ የሚያደርገው አስተዋጽኦ በጣም
ከፍተኛ ነው ። በሌላ አገላለጽ ለትምህር
ትና ለዕውቀት መሠረቱ ተግባር ነው።ትም
ህርት ደግሞ በበኩሉ የምርት ሥራ ክንዋኔ
በተሻለና በላቀ ደረጃ እንዲካሄድ ንድፈ
ሐሳባዊ መሣሪያ በመሆን ስለምርትና ዕድ
ገት ትክክለኛ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ፡
የነገሮችንና የክስተቶችን ውስጣዊ ባሕ
ርይ፣ አንድነትና ልዩነት በጥልቀት የሚያሳ
ይና የወደፊት የዕድገት አቅጣጫንም የሚ
ያመለክት ነው ።

የትምህርትንና የተግባርን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነትና የሁለቱን የተመጣጠነና የተመዛዘነ ዕድገት ጠብቆ ሁለንተናዊ ስብዕናን የሚያስገኝ ፖሊቴክኒካዊ ትምህርትን ተግባራዊ በማድረግ ለቁሳዊና ኅሊናዊ እሴቶች መፍጠሪያ እንዲውል ፣ ሠርቶ አደሩ በተፈጠሩት እሴቶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ የተቻለውና የሚቻለው በሶሻሊስት ሥርዓት ነው ።[26] ምክንያቱም ሶሻሊዝም በባሕርዩ ማኅበራዊ ነው ። ይህ ባሕርዩው በማምረት ፣ በክፍፍልና በሥርጭት ማኅበራዊነት የሚገለጽ ሲሆን በአደረጃጀቱና በማዕከላዊ ዕቅድ በሚመራው አሠራሩ ኅብረተሰብ በረጅም ታሪካዊ ሂደት ውስጥ ያካበተው ማኅበራዊ ሀብትና ዕውቀት ለሰላም ፣ ለእኩልነትና ለሕዝቦች የጋራ ብልፅግና እንዲያገለግል የሚያደርግ ነው ።

ትምህርትን ፖሊቴክኒካዊ ማድረግ የት/ቤቶችን ሶሻሊስት ባሕርይ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና አለው ። ለፖሊቴክኒክ ትምህርት ተግባራዊ መሆን የሚበጁ ማኅበራዊና ነባራዊ ሁኔታዎች መመቻቸት በጣም አስፈላጊ ነው ። ለምሳሌ የማምረቻ መሣሪያዎች የሕዝብ መሆንና የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች መስፈን ተማሪዎች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ፣ ፋብሪካዎችና የአገልግሎት መስጫ ደርጅቶች ውስጥ እየተመደቡ መሥራትና መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ። በዚህ የሚቀጠሩ ሠራተኞችና በኅብረት የተደራጁ ገበሬዎች በየተቋሞቻቸው ተማሪዎችን በሥራ ልምምድ አማካይነት እንዲማሩና በማስተማሩም ሥራ ከመምህራን ጐን ተሰልፈው እንዲያስተምሩ ማድረግ ለፖሊቴክኒክ ትምህርት ተግባራዊነት ዋነኛው መድረክና ሥልትም ነው ። በመሆኑም ሶሻሊስት አገሮች በኢንዱስትሪዎችና በሶሻሊስት መርህ በተደራጁ እርሻዎች ውስጥ ለመሥራት የሚችሉ ሠራተኞች ለማስገኘት ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመረዳት በትምህርት ሥልትነት እየተጠቀሙበት ነው ።

በሶቭዬት ኅብረት ሠራተኛው ሥልጣን በያዘ ማግሥት ጐልቶ የታየው ችግርና የተነሣው ጥያቄ ዘመናዊ የሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎች እጥረት ብቻ ሳይሆን መሣሪያዎቹም ቢገኙ በትክክል ሊጠቀምባቸው የሚችል በቂ የሰው ኃይል አለመኖርም ነበር ። የማምረቻ መሣሪያዎችና የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በሳይንቲስቶች ፣ በምሁራንና በሰፊው ሕዝብም ዘንድ የቴክኖሎጂንና በዚህ ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችል የሰው ኃይል አስፈላጊነትን አጉልቶ አሳየ ። ይህም ፍላጐት ለሳይንስ ዕድገት ከፍተኛ ግፊት ሰጠ ፣ ሕዝቡም ይህን ፍላጐቱን ለማርካት በተለያ መልኩ ተነሣሣ ። ነገር ግን ሂደቱ በዘፈቀደ የሚከናወን ጉዳይ አልነበረም ። በጊዜም ለተፈጠረው የሕዝብ ፍላጐት ትክክለኛ አመራር በመስጠት ተገቢ አቅጣጫ እንዲይዝ ማድረግ የወቅቱ ጥያቄ ነበር ። ቀድሞ ይሰጥ የነበረው ትምህርት ከምርት ተግባር ፣ ከሕዝቡ የዕለት ተዕለትና የቁሳዊ እሴቶች ፈጠራ እንቅስቃሴ ጋር የነበረው ግንኙነት ደካማ ስለነበረ ለዚህ ጥያቄና ፍላጐት መልስ ሊሰጥ አልቻለም ።

የአገሪቱን ኢንዱስትሪዎች የመገንባትና እርሻንም በሶሻሊስት ፈር የማደራጀት ጥያቄ የትምህርቱን ሥርዓት ፣ ዓይነትና የአሰጣጥ ዘዴ በአዲስ የማደራጀትና የመለ

ወጥ አስፈላጊነትን አጕላው ። አዲሱ ትምህርትም ለወጣቱ ትውልድ ሙያን የሚያስጨብጥ ፤ ለኅብረተሰቡ ቁሳዊና ባህላዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እሴቶች እንዲያመርት የሚያዘጋጀውና የሚያስችለው ትምህርት መሆን ነበረበት ። ይህ ወቅት ማርክስና ኤንግልስ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ያብራሩትን በምን መልኩ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችልም ያሳዩት የፖሊቴክኒክን ትምህርት አስፈላጊነትና በተግባር መተርጐም አበሰረ ።

ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት የተፈጥሮን ፤ የማምረቻ መሣሪያዎችን ፤ አሠራራቸውንና አጠቃቀማቸውን ጥምር የሚያስጠና ፤ የአንድን አገር ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና በአቀማመጡም የተነሣ በኢኮኖሚውና በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ላይ ሊኖር የሚችለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ ፤ የአገሪቱን የተፈጥሮ ሀብትና የተፈጥሮ ሀብቱ እንዴት ሊለማና ለሕዝብ አገልግሎት ሊውል እንደሚችል የሚያስተምር የትምህርት ዓይነት በመሆኑ ወቅታዊና አስፈላጊነቱ የማያጠያይቅ በመሆኑ በተሟላ ሶሻሊስት ይዘት ለመጀመሪያ ጊዜ በሶቭዬት ኅብረት ተግባራዊ መሆን ጀመረ ።

በሶቪዬት ኅብረት ፖሊቴክኒካዊ ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ በት/ቤቶች ውስጥ በተደራጁት የተግባራዊ ትምህርት መስጫ ድርጅቶች አማካይነት ከሥዕሎች መሣያ ፡ ከቅርፃቅርፅ መሥሪያ ፡ ከላቦራቶሪዎች ፤ ወርክ ሾፖች ፤ ከእርሻ ትምህርት መስጫ መሬቶች ወዘተ. ሌላ ተማሪዎች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ፤ ፋብሪካዎች ፤ የመንግሥት እርሻዎችና የማኅበራት እርሻዎች እየተመደቡ ተግባራዊ ትምህርት እንዲማሩ ተደረገ ።

ለተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች የሚሰጠው የፖሊቴክኒክ ትምህርት እንደየትምህርቱ ደረጃ የተለያየ ነው ። ለአንደኛ ደረጃ (ከ1 — 3) የሚሰጠው ትምህርት በባሕርዩ አጠቃላይ ነው ። ዓላማውና ይዘቱም ተማሪዎችን አጠቃላይ ስለሆነው የምርት መሠረታዊ ነገሮች ፤ አደረጃጀታቸውንና አንዱ የምርት ክፍል ከሌላው የኢኮኖሚ መስክ ጋር ያለውን ግንኙነት ፤ አንድነትና ልዩነት ማሳወቅ ነው ። ይህም ለተማሪዎች ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ጋር እያገናዘቡ እንዲማሩ መሠረት ይፈጥርላቸዋል ። ለመካከለኛና (ከ4 — 6) ለከፍተኛ ደረጃ (ከ7 — 10) የሚሰጠው ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት ተማሪዎች በሚገኙበት ደረጃ አንፃር በአንድ በተወሰነ የሥራ መስክ ውስጥ በሚገኘው የምርት ተግባር እንዲሰለፉ የሚያስችላቸው ሲሆን የትምህርት አቀራረቡ ግን አንድን ሙያ በማስጨበጥ ላይ ብቻ የሚያተኵር ሳይሆን ፖሊቴክኒካዊ አመለካከታቸውንና ሁለንተናዊ ዕድገታቸውን የሚያዳብር ነው ።

ሌኒን ይህንኑ ሲያብራራ ሥራ የሚከበርበት የሠራተኞች አገር እየገነባን ነው ።

በዚህ ዓይነቱ አገር ውስጥ ትምህርት ከምርት ተግባር ጋር ተቀናጅቶ ካልተሰጠና ወጣቱ ትውልድ በዚህ መንፈስ ታንጾ ካላደገ ፤ ከምርት ሥራ ጋር ባልተገናዘበ ሥልጠና ፤ ተግባርና ትምህርት ሊኖራቸው የሚገባውን ዲያሌክቲካዊ መስተጋብር ሳናስፍን ፤ ዛሬ ወቅቱ የሚጠይቀውን የሰው ኃይል ማፍራትና ከወቅቱ ጋር ሊራመድና ለወቅቱም መለወጥ እገዛ ሊያደርግ የሚ

ችል ትምህርትና… ዕውቀት ማስገኘት አይቻልም[27] ብሏል ። የታወቀችው የሶቭዬት ፔዳጐግ ክሩፕስካያ ትምህርት ቤቶቻችን የምርት ሥራ ት/ቤቶች ይሆናሉ ። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት መሠረቱ ሳይንስ ነው ። ትምህርቱም ስለምርት ሂደት ፣ የምርት አደረጃጀት አሠራርን ፣ ለሕልውናና ለዕድገትም ያለውን አስፈላጊነት እንዲሁም ጠቅላላ የሰዎችን ማኅበራዊ ኑሮ ማሳወቅ መቻል አለበት[28] ስትል በ1918 ገልፃለች ።

ከ1918 – 1930 ባለው ጊዜ ውስጥ በሶቪዬት ኅብረት በትምህርት ዓይነትና በት/ቤቶች አደረጃጀት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ተደርጐ ት/ቤቶች በሙሉ ፖሊቴክኒካዊ ሆኑ ። በትምህርታቸው ብዙ ሳይገፉ ሥራ የያዙ ሠራተኞችም በማታና በተለያዩ መንገዶች ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት እንዲያገኙ ተደረገ ። ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የኅብረተሰቡ በተለይም ደግሞ የተለያዩ የምርት ተቋማት ተሳትፎ ለምሳሌ የኢንዱስትሪዎች ፣ የፋብሪካዎች ፣ የመንግሥት እርሻዎች ፣ የገበሬ ማኅበራት እርሻዎች ወዘተ. ወጣቱን ትውልድ ከምርት ተግባር ጋር በማስተዋወቅ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ በየምርት ተቋማት የማስተማሪያ መድረኮች እንዲዘጋጁ ፣… ሠራተኞችና ገበሬዎች በማስተማሩ ሥራ እንዲሳተፉ መመሪያ ተሰጠ ። ለዚህ ተግባራዊነት የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማለትም የትምህርት ፣ የኢንዱስትሪ ፣ የግብርና ወዘተ. የበላይ መሥሪያ ቤቶች እንዲሳተፉና… ለሥራውም መቃናት እገዛ እንዲያደርጉ ተደረገ ። በመሠረተ ትምህርት ዘመቻም ይህ ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት ተሰጠ ።

የሕፃናት የማወቅ ፍላጐት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ጥያቄዎቻቸው ሜካኒካዊና ቴክኒካዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ይህን የማወቅ ፍላጐታቸውን ለማርካት የፖሊቴክኒካዊ ትምህርት ጽንሰሐሳብ ከሙዓለ ሕፃናት ጀምሮ መሰጠት ተጀመረ። ሀገሪቷ በዚህ ረገድ የሚገጥሟትን ችግሮች ሁሉ እየተቋቋመች ወቅቱ ለጠየቀው ጥያቄ ምላሽ በመስጠት ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት ፣ እርሻን በአዲስ ለማደራጀትና ሶሻሊስት ፈር ለማስያዝ ፣ ሕዝቧን ወደላቀ የዕድገት ደረጃ ለማሸጋገርና ዛሬ ከሚገኝበት ለማድረስ ትምህርትን ፖሊቴክኒካዊ ማድረጓ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝቶላታል።

በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክም የፖሊቴክኒክ ትምህርት አጀማመርና ዕድገት ከሶቭዬት ኅብረት ልምድ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ፋሺዝም ከተደመሰሰና ሠራተኛው ሥልጣን ከያዘ በኋላ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ክንዋኔዎች አንዱ ሰፍኖ የነበረውን የካፒታሊስት የትምህርት ሥርዓት በማስወገድ በምትኩ አዲስ የትምህርት ሥርዓት የማደራጀቱ ሥራ ነበር ። ለጥቂት የገዥ መደብ አባላት ልዩ መብትና ጥቅም ሆኖ

የነበረውን የትምህርት ሥርዓት በማስወ ገድ ፀረ ፋሺስትና ዴሞክራሲያዊ ትምህ ርት ለሁሉም በእኩል የሚዳረስበትን ሁኔታ መፍጠር የወቅቱ ተግባር ነበር ።

የዚህ ዓይነቱን የትምህርት ሥርዓት ለመዘ ርጋት እንጋፋ ሶሻሊስት ሀገር የሆነችው የሶቪዬት ኅብረት ልምድ ጠቅሟል ። በዚሁ ልምድ ላይ በመመርኮዝ በጀርመን ዴሞክ ራቲክ ሪፐብሊክም አዲሱ ሶሻሊስት ትምህ ርትና ት ቤቶች ፖሊቴክኒካዊ መሆን ይገባ ቸዋል ከሚል አቋም ተደረሰ ።

ይህን በተግባር ለመተርጐም በቅድሚያ በተወሰኑ ት ቤቶች የፖሊቴክኒክ ትምህ ርት በሙከራ እንዲሰጥ ተደረገ ። በነዚህ ት ቤቶች የሚሰጡት ትምህርቶችና ፕሮጀ ክቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲገመገ ሙና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያገኙ በፓር ቲው በተሰጠው አመራር መሠረት መንግ ሥት ሂደቱን እየተከታተለና እየገመገመ ማስፈጸም ጀመረ ። በተለያዩ ወቅቶች በተደረጉ የፓርቲው ስብሰባዎች ፖሊቴክኒ ካዊ ትምህርትን አገር አቀፋዊ ለማድረግ ሁኔታዎች መመቻቸታቸው ተረጋገጠ ።

ከዚህ በኋላ በ5ኛው የፓርቲ ጉባዔ ከ1 — 10 ላሉት ክፍሎች አጠቃላይ ትምህ ርት እንዲሰጥና የትምህርቱም አቀራረብ ፖሊቴክኒካዊ እንዲሆን ተወሰነ ።

ትምህርትን ከምርት ተግባር ጋር አገና ዝቦ መስጠቱ ቀላል አልነበረም ። በየት/ቤ ቶቹ ስለተለያዩ ሙያዎች ጽንሰሐሳብ ለማ ስተማርና ስለሥራ አደረጃጀትም አጠቃ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የማስተማሪያ ወርክ ሾፖችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር ።

በት/ቤቶች ስለምርት ተግባር የሚሰጠው ትምህርት በቂ ስለማይሆን ተማሪዎች በየ ማምረቻ ድርጅቶች ጉብኝትና ልምምድ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ሌላው ተግባር ነበር ። ምክንያቱም ወጣቱን ትውልድ ለሥራና ለተሟላ ሕይወት ለማዘ ጋጀት እንዲቻል ሠራተኛውንና ገበሬውን በፖሊቴክኒክ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ወሳኝ ነው ።

በዚሁ መሠረት ደረጃ በደረጃ በኢንዱስ ትሪዎች ፣ በፋብሪካዎች ፣ በመንግሥትና በገበሬ ማኅበራት እርሻዎች ውስጥ የማሠል ጠኛ ተቋሞች እንዲቋቋሙና ተማሪዎች በየደረጃቸው እየተመደቡ እንዲማሩና በም ርቱ ሥራ ሂደትም እንዲለማመዱ ማድረግ ተጀመረ ። የማሠልጠኛ ተቋሞች እስኪዘ ጋጁ ድረስ ግን ተማሪዎች በምርት ተቋ ሞች እየተገኙ በጉብኝትና በሥራ ልምምድ ፕሮግራም ከሠራተኞችና ከገበሬዎች ጋር በመሥራት ተግባራዊ ትምህርት እንዲማሩ ሲደረግ ቆየ ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት አጀማመር ዓላ ማና ንድፈሐሳባዊ መርህዎች በየትኛውም ሶሻሊስት ሀገር ተመሳሳይ ናቸው ። የአፈጻ ጸም ሥልቱ ግን እንደየአገሩ ተጨባጭ

ሁኔታ ሊለያይ ይችላል ። ዓላማውን ለማስ ፈጸም የሚዘረጋውም የትምህርት መዋቅር እንደየአገሩ የኢኮኖሚ አቅምና አጠቃላይ የዕድገት ደረጃ የተለያየ ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊነት በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ አብዮት በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ሥርነቀል ለውጦች እንዳስከተለ ሁሉ በትምህርት መስክም የመሠረታዊ ለውጥ መሠረት ጥሏል ። በቅድመ አብዮት የነበረውን የትምህርት ሥርጭት ውሱኑነት በመሻር ትምህርት ለሰፊው ሕዝብ እንዲዳረስ አስፈላጊው ጥረት ተደርጓል ፤ እየተደረገም ነው ።

ትምህርት ከተለያዩ ኢሳይንሳዊ አመለካከቶችና የኢምፔሪያሊዝም ርዕዮተዓለም ተጽዕኖ ተላቆ በሳይንሳዊ አመለካከት ላይ ተመሥርቶ ለወጣቱ እንዲሰጥና ወጣቱም በትክክል የተቀረጸ ሰብዕናን ይዞ እንዲያድግ ለማድረግ የሚካሄደው ጥረት እስከ አሁንም የሚያበረታታ ውጤት አስገኝቷል።

ይሁን እንጂ በካፒታሊስትና በታዳጊ ሀገሮች (የካፒታሊስት ወይም ሶሻሊዝምን ዓላማቸው ያደረጉ ታዳጊ አገሮች) ውስጥ በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚታዩትና የሚመነጩት ችግሮች ከሞላ ጐደል በሀገራችን ውስጥም ታይተዋል ። ዛሬ ከደረስንበት ነባራዊ ሁኔታና ከመረጥነው የዕድገት ጐዳና አንፃር የትምህርት ሥርዓታችን በልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስኮች ያሉብንን ችግሮች ለማቃለል የማይረዳ ገጽታው መወገድ ይኖርበታል ። በመሆኑም ነው ባሁኑ ጊዜ በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚታዩት ችግሮች "የትምህርት ጥራት" በሚል አጠቃላይ ሐረግ በተለያዩ መድረኮች የሚነሡት ። ዛሬ በሀገራችን የትምህርት ጥራት የሚፈለገውን ያህል አይደለም ሲባል ይህ ጉድለት በምን መልኩ ነው የሚታየው የሚል ጥያቄ መነሣት አለበት ። እዚህ ላይ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ሳንገባ አጠቃላይ ሐሳቦችን እናነሣለን ።

ትምህርትን የምንማረውና የምናስተምረው ለትምህርትነቱ ብቻ አይደለም ። ትምህርት ለሌላ ግብ በመሣሪያነት (በዘዴነት) የሚያገለግል እንጂ ራሱ ግብ አይደለም ። ከዚህ መሠረተሐሳብ ስንነሣ የትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነው ስንል ትምህርት በምርት ኃይልና በርዕዮተዓለም ዘርፍነቱ በግንባታው ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ወይም የሚያበረክተው ድርሻ ዝቅተኛ ነው ማለታችን ነው ። በሌላ አገላለጽ አዲሱን ትውልድ የኢኮኖሚ ፡ የፖለቲካና የባሕል ግንባታችንን በሚያፋጥን መልክ (በተሟላ ሁኔታ) አላዘጋጀነውም ፤ ወይም ሀገሩንና ወገኑን በቅንነት ፤ በታማኝነትና በጥረቱ

የሚያገለግል አላደረግንውም ፤ ባጭሩ ት/ቤቶቻችን የሚከተሉት የትምህርት ሥርዓት አዲሱን ትውልድ የሚፈለግበትን የኃላፊነት ድርሻ መወጣት በሚያስችል መልኩ አልቀረበለትም ማለታችን ነው ።

ይህ ሁኔታ ከተያያዝነው የሽግግር ወቅት ጋር የሚገናዘብ ነው ። በሌሎች መስኮች እንደምናደርገው ሁሉ በትምህርት ሥርዓት አዘገጃጀትም አንፃር የማፍረስና የመገንባት ሂደት አለ ። በሽግግር ወቅት አሮጌው የትምህርት ሥርዓት ሙሉ በሙሉ አይወገድም ። አዲሱም ወዲያውኑ አድጐና ዳብሮ ሙሉ በሙሉ አሮጌውን የሚተካ አይሆንም ። በዚህ ምክንያት ለትምህርት ጥራት ዝቅተኝነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች ይኖራሉ ። ነገር ግን ይህ የሽግግር ባሕርይ የግድ ይኖራል በሚል መዘናጋትም የሚያስፈልግ አይደለም ። በዕድገት ፍላጐታችንና በሚሠለጥነው የሰው ኃይል መካከል የተጣጣመና የተመዛዘነ ግንኙነት በመፍጠር ለዘላቂው ግባችን ዕድገታችንን የሚያፋጥንና ማኅበራዊ ችግሮቻችንን የሚፈታ የትምህርት ሥልት መቀየስ አማራጭ የለውም ።

ዛሬ በት/ቤቶቻችን የሚቀረጹት ዜጐች የሚኖሩበትን ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ አካባቢዎች ሳያውቁ ምናባዊ ዓለምን የሚናፍቁ መሆን የለባቸውም ፤ ለጥቂቶች መጣሪያ በመሆን ብዙኃኑን ሕዝብ የሚጨቁኑ ወይም የየራሳቸውን የግል ጥቅም በማስቀደም በኅብረተሰቡ ዕድገት ላይ መሰናክል የሚፈጥሩ መሆን የለባቸውም ፤ ባንድ አካል (ለምሳሌ በአእምሮ) በሳል ፤ በሌላው ደግሞ ጥሬ (ለምሳሌ በጉልበት ሥራ) መሆን አይኖርባቸውም ፤ ሥራን እንደመርገምትና ቅጣት በመቁጠር የሚሸሹ ሊሆን አይገባም ፤ በደንታቢስነት ፤ በለዘብተኝነትና በመሳሰሉት ምግባረብልሹነት የእናት ሀገርን ዕድገት የሚያቀጭጩና ለውድቀት የሚዳርጉ መሆን የለባቸውም ። ዛሬ ለምናፈራቸው ዜጐች ትክክለኛና መሠረታዊ መነሻ የሚሆናቸው ሥራ የዕድገት መሠረት መሆኑን መረዳት ነው ። ለምሳሌ ልብስ መልበስና መጠለያ ማግኘት የእያንዳንዱ ዜጋ መሠረታዊ ፍላጐትና ጥያቄ ነው።

ለመሠረታዊ ፍላጐት እርካታ የሚውሉ ነገሮችን የሚያስገኘው ደግሞ ሥራ ነው ። መሠረታዊ ፍላጐቶቹ እንዲረኩ የሚሻ ሁሉ የመሥራት (የማምረት) መሠረታዊ ግዴታም አለበት ።

ከሁሉም በላይ ምርትን ለሚያስገኝ ሥራ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ። የምናፈራው ዜጋ አካባቢያዊና ብሔራዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት በግል እነሳሽነት ጭምር በብዙ ረገድ ራሱን የሚያዘጋጅ መሆን አለበት ። መቅረጽ የሚኖርብን ዜጋ እራሱን ከመጥቀም ባሻገር ሀገርንና ወገንን መጥቀም የሚቻለው እንዴት ነው? ቀልጣፋና ቅን

አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችሉ አዳዲስ የአሠራር ስልቶች ምንድናቸው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማን ሣት ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጥ መሆን ይኖር በታል ።

ከዚያ አኳያ ሀገራችን የምትገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጐት መሠረት በማ ድረግ የተሻሻለ የትምህርት ሥርዓት ለመዘ ርጋት አስፈላጊው ሁሉ እየተደረገ ነው ።

በኢሠፓ ፕሮግራም በግልፅ እንደተመለከ ተው የትምህርት ቀዳሚ ዓላማ ሰብዕናው የተሟላ ፣ … የተፈጥሮና የኅብረተሰብ ዕድ ገት ሕግጋትን ያወቀ ፣ በሶሻሊስት ኅብረተ ሰብ ግንባታ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግና ሶሻሊ ስት ኅብረተሰብን ለመገንባት የሚችል ፣… ቁሳዊ ጠቀሜታን በሚያስገኝ ትምህርትና ዕውቀት የታነጸ ፣ በንቃቱና በባህል ደረ ጃው የዳበረ አዲስ ሰው መፍጠር ነው ። ለዚህ ዓላማ ተግባራዊ መሆንም የፖለቲ ካዊ ትምህርት እንደ አንድ ወሳኝ ሁኔታ በፕሮግራሙ ተጠቁሟል ።[29]

ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለብሔ ራዊ ሸንጐ የመጀመሪያ ስብሰባ ባቀረቡት ሪፖርት ትምህርት ፋይዳ ላለው የምርት ተግባርና ለሕይወት ጠቀሜታ ካልሆነ ዋጋ እንደሌለው ፣ ዓላማውም ወጣቶችን በየእር ከኑና በየዕድሜ ክልሉ ከታች ጀምሮ በአ ንድ ጠቀሜታ ባለው የሥራ መስክ እንዲሰ ማሩ ማዘጋጀት መሆን እንዳለበት ፣ የአጠቃ ላይ ፖሊቴክኒክ ሥርዓተ ትምህርት ተዘርግ ቶና አስፈላጊው ሁኔታ ተመቻችቶ ወጣቱ ለምርት ካልተዘጋጀ ስለሶሻሊስት የትምህ ርት ሥርዓት መናገር እንደማይቻልም ማስ ገንዘባቸውም የሚታወስ ነው ።[30]

የፖሊቴክኒክ ትምህርትን የመስጠ ጉዳይ ተገቢ ትኩረት አግኝቶ ሥርዓተ ትምህርቱ ከተነደፈ በኋላ ከተለያዩ የአገ ሪቱ ክፍሎች የናሙና ት/ቤቶች ተመር ጠው ሙከራው በተግባር ሲካሄድ መቆየ ቱም ይታወቃል ። ሙከራው የተለያዩ ዓላማዎችን ይዞ የተጀመረ ነው ። ከእነዚ ህም ጥቂቶቹ ፣

— የአጠቃላይ ፖሊቴክኒክን ትምህርት ይዘት ፣ የአሰጣጥ ዘዴና ለዚህም የሚያስ ፈልጉ መሣሪያዎችንና ሌሎችንም ሁኔታ ዎች ለማጥናት ፣

— ለፖሊቴክኒክ ትምህርት የመምህራን አሠለጣጠን ስልት ለመቀየስ ፣

— በሙከራው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅና ለወደፊቱ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ[31]… ወዘተ. የሚሉ ናቸው ።

ከ1973 — 1979 በነበሩት የሙከራ ዓመታት በርካታ ልምዶች ተገኝተዋል ። የትምህርቱን ዓላማ ፣ ይዘቱንና የማስተማር ዘዴውን በመንደፍ ፣ እነዚህንም በናሙና ት/ቤቶች ላይ በመሞከር ፣ ሙከራውን

በመከታተልና ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር በተጣጣመ ሁኔታ መስጠቱን ለመገምገም ተሞክሯል ።

በየጊዜው ለተለያዩ ደረጃዎች በተደረጉ ዝግጅቶች ላይ ውይይት በማካሄድ ፣ ዝግጅቱን በማሻሻልና በማዳበር ረገድ የተገኘው ልምድም አመርቂ ነው ። በሥርዓተ ትምህርት ኤክስፐርቶችና በመምህራን መካከል በተደረገው የቅርብ ግንኙነት ሥርዓተ ትምህርቱ እንዲሻሻል ፣ እንዲዳብርና ተጨባጭ እንዲሆን የተቻለው ተደርጓል ።

በየአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የማስተማሪያ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት ልምድ፣ ከአካባቢ በተገኙ የማስተማሪያ መረጃ መሣሪያዎች ላይ ተመሥርቶ የማቀድ ፣ የማስተማርና የመገምገም ልምድም የተገኘ ሲሆን በወላጆችና በት/ቤቶች መካከል የመቀራረብና የሌሎችም ጠቃሚ ልምዶች እየዳበሩ መጥተዋል ።[32]

የፖሊቴክኒክን ትምህርት በመላ አገሪቱ ት/ቤቶች ለመዘርጋት ፣ ተግባራዊ ለማድረግና በአስተማማኝ ሁኔታም ለመቀጠል የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ፣ ኢንዱስትሪዎች ፣ ፋብሪካዎች ፣ የተለያዩ የምርት ተቋሞችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሥልት መቀየስና ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ክትትልና አመራር መስጠት ያስፈልጋል ።

ወጣቱን ትውልድ የማስተማሩ ሥራ የሁሉም ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን የህን ግንዛቤ ከፍ የማድረግና ሁሉም በሥራው የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኃላፊነቶች አንዱ በመሆኑ ትኩረት የሚሰጠው ዐቢይ ጉዳይ ነው።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት አስፈላጊ ነው ሲባል ከወዲሁ ግንዛቤ ማግኘት የሚገባቸው ችግሮች መኖራቸውንም ማንሣቱ ተገቢ ነው ። ካሉን ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ መሠረቶች አኳያ ይህን ትምህርት የማደራጀቱ ሂደት የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላሉ ። የሂደቱም ውጤት ወዲያውኑ የሚጨበጥና በብሔራዊ ኢኮኖሚና በሠለጠነ የሰው ኃይል መካከል ያለውን ቅራኔ ወዲያው የሚፈታም አይሆንም። ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ ስንጀምር ሊገጥመን የሚችለው ትልቁ ችግር ለዚህ ትምህርት አሰጣጥ የተሟላ ዝግጅትና ያለው በቂ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማግኘቱ ነው ። ሰው ብቻም በቂ አይደለም ፤ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ፣ ት/ቤቶች አካባቢ ዘመናዊ የማምረቻ ድርጅቶች ፣ የአገልግሎት ተቋሞችና የምርት ሥራም አስፈላጊ መሆናቸው ይታወቃል ። እነዚህ በተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲመዛዘኑ በጣም እና… ናቸው ።

ይሁን እንጂ ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከመነሣት ሌላ አማራጭ ሊኖር አይች ልም ። ሌኒን ይህን ችግር አስመልክቶ በሰጠው ትምህርት መሠረት ፣ ምንም እንኳ የትምህርት ቤቶች ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረ ቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙና በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ፋብሪካዎችና የምርት ተቋሞችም በቁጥር አነስተኛ ቢሆ ኑም ፖሊቴክኒካዊ ትምህርትን ከምርት ተቋ ሞች ጋር አቀናጅቶ ከመስጠቱ ዓላማ ዝንፍ ማለት ወይንም ወደኋላ ማለት የማያቀጣ መሆኑ ግንዛቤ ላይ ተደርሷል ። የሀገሪቱ አቅም ደካማ መሆኑ የታወቀ ነው ። በእንጻሩ ደግሞ ባለሙያዎች ፣ የብረታ ብረት ሠራተ ኞች ፣ የእንጨት ሥራ አዋቂዎች ፣ ኤሌክትሪ ሺያኖች ፣ ዘመናዊ የግብርና ዕውቀት ያላ ቸው ሰዎች ወዘተ. ያስፈልጋሉ ። በሌኒን ትምህርታዊ ትንታኔ መሠረት እነዚህን ሁሉ ለማግኘት መፍትሔው የፖሊቴክኒክ ትምህርት መስጠቱ ወሳኝ መሆኑ ስለታመነ በት ተግባራዊ የማድረጉ አስፈላጊነት ጥልቅ ግንዛቤና ትኩረት አገኘ ።[33] በአገራ ችንም የፖሊቴክኒክ ትምህርትን የመዘር ጋቱ አስፈላጊነትና ሁኔታው ይህንኑ በመ ሰለ እውነታ ላይ የሚመሠረት ነው ።

በትምህርቱ ሂደትና አሰጣጥ ውስጥ ሚዛናዊነትን አለመጠበቅም ሌላው ሊኖር የሚችል ችግር ነው ። የትምህርቱ ሥርዓት የሚዋቀርበት የተለያዩ አካላት አሉት ። አንዳንድ ጊዜ የአንዱ አካል ሚና ይዘነጋና የሌላው ጐልቶ ሊታይ ይችላል ። ለምሳሌ ትምህርትን ከማምረቻ አካባቢዎችና ከም ርት ሂደት ጋር አጣጥሞ ለመስጠት በሚደ ረገው ጥረት የማስተማር ዓላማ ተዘንግቶ በምርት ማስገኘቱ ላይ ብቻ ማትኮር ወይም በተቃራኒው የምርት ሥራው ተዘን ግቶ ማስተማሩ ላይ የማተኮር ሁኔታ ሊከ ሰት ይችላል ። እነዚህንና ሌሎች መሰል ችግሮችንም ከወዲሁ መገንዘብ ጠቃሚ ነው ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

የተያያዝነው አብዮታዊ የማኅበራዊ ዕድገት ትግል የሚፈለገውን ውጤት እንዲ ያስገኝ ፣ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ኑሮ እየተሻ ሻለ ወደሶሻሊዝም ለመሸጋገር በተለይ በቁ ሳዊ ምርት መስክ የሚገኘው ውጤት ወሳኝ ነው ። ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ የሠራተኛውን ዕውቀትና የፈጠራ ችሎታ ማሻሻልና ማሳደግ ፣ የሥራ አደረጃጀትን ፣ የቴክኖሎጂ መሠረታዊ አሠራርንና የመሣ ሪያዎችን አጠቃቀም ማወቅ ወይም በጠቅ ላላው የሠርቶ አደሩን አመለካከት በሳይን ሳዊ አመለካከት ፣ በዲሲፕሊን ማነጽና ሳይንሳዊ የሥራ አመራርን ማዳበር በጣም አስፈላጊ ነው ። የሳይንስና የቴክኖሎጂን

መሠረታዊ አደረጃጀትና አሠራር ለማወ
ቅና በአግባቡ ለምርት ተግባር እንዲያገለ
ግሉ ለማድረግ እንዲችል በየደረጃው በም
ርት ተግባር ላይ የተሰማራውና የሚሰማ
ራው ሠራተኛ ዕውቀትና የፈጠራ ችሎታ
በዓይነት ፣ በመጠንና በጥራት እያደገ
መሄድ ይኖርበታል ።

ኢትዮጵያ የምትፈልገው ሁለንታዊ
ስብዕናው የተሟላ ፣ በመካሄድ ላይ ባለው
አዲስ የኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ
ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ የሚችልና በተግባ
ራዊ ሙያ ፣ በአዲስ መንፈስና በሠራተኛ
ዲሲፕሊን የታነፀ እምራች ትውልድ ነው።
ስብዕናው የተሟላ አዲስ ትውልድን በት
ቤት ከሚሰጡት የተወሰኑ የትምህርት ዓይ
ነቶች ብቻ በሚገኝ ዕውቀት መፍጠር
አይቻልም ። በመሆኑም ወጣቶች በሳይንስ፣
በቴክኖሎጂ ፣ በኪነጥበብ ፣ በአካል ሥልጠ
ናና በምርት ተግባር በመሳተፍ ፣ የዕውቀት
አድማሳቸውን በማዳበርና በማዝናናት እን
ዲያሳልፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ፕሮግራ
ሞች እንዲቀየሱና በተግባርም እንዲተረ
ጐሙ ተገቢው ትኩረት እንደሚሰጥ የሚጠ
ቁመው መመሪያ[34] ተግባራዊ መሆን
በአገራችን እማራጭ ለማይገኝለት አጠቃ
ላይ የፖሊቴክኒካዊ ትምህርት ሥርዓት
ተፈጻሚነት ወሳኝ ነው ።

አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚያስፈ
ልገውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ከማሟ
ላት አንፃር የኢሕዲሪ መመሥረት ለአ
ሠፓ ፕሮግራም ተግባራዊነትና እስከዛሬ
የተገኙትን ድሎችና ውጤቶች መሠረት
በማድረግ ለላቀ ውጤት መገኘት ሁኔታዎ
ችን ያመቻቻል ። በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ
በኢሠፓ አመራር ፣ በማዕከላዊና በክልል
የሕዝባዊ ሥልጣን አካላት አስፈፃሚነት ፣
በመንግሥት ፣ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በሕ
ዝቡ ያልተቆጠበ ንቁ ተሳትፎ የፖሊቴክ
ኒክ ትምህርት ሥርዓት በመላ አገሪቱ በየደ
ረጃው አግባብነት ባለው መልክ ተዘርግቶ
ተግባራዊ ሲሆን የዕድገት ምኞታችን የበ
ለጠ እውን እንደሚሆን ይታመናል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 18, p. 74
2. Marxism, Communism and Western Society, Vol.6, p.384
3. Ibid, p. 388
4. U. Turchenko, The Scientific and Technological Revolution and the Revolution of Education (Moscow: Progress Publishers, 1976), p.43
5. Marxism, Communism and Western Society, Vol.3, p.121
6. Ibid.
7. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 20, P.388
8. K.Marx and F. Engels, The German Ideology (Moscow: Progress Publishers) pp. 47 48
9. N.Krupskaya, On Labour Oriented Education and Instinction, p. 17
10. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 6, p. 384
11. K. Marx, Capital, Vol.I,(Moscow, Progress Publishers), p. 452
12. Bukharin and Preobrazhensky, The ABC of Communism, p. 279
13. Philip H. Coombs, The World Educational Crisis (London: Oxford University Press, 1868) p. 74
14. ከትምህርት ዓለም ፡ ለኢሕዲሪ ምሥረታና ለ13ኛ የአብዮት በዓል የተዘጋጀ ፡ ልዩ እትም፡ አዲስ እትም ፡ አዲስ አበባ ፡ ነሐሴ 1979 ፡ ገጽ 12
15. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 14
16. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 15
17. Anatoli Lunacharsky, On Education Moscow : Progress Publishers, 1981) p. 52.
18. K.Marx, Capital, Vol, I, p. 488.
19. Marxism, Communism and Western Society, Vol. 3, p.121
20. K.Marx, Capital, Vol.I.P.
21. Study Material for Training and Further Qualification of Cadres of Public Education, (Berlin: Verlag, "Vok and Wissan", 1978).p. 106
22. K.D. Ushinsky, Selected Works, (Moscow: Progress Publishers), P. 225
23. በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት መምሪያ ፡ የአጠቃላይ ፖሊቴክኒክ ምንነት … ሰኔ 1979 (ያልታተመ)
24. K. Marx, Ibid, P. 455.
25. K.Marx and F.Engels, Manifesto of Communist Party, Collected Works, Vol, 6, pp. 500—501.
26. N. Krupskaya, Ibid, p. 13.
27. Ibid, p.94
28. Ibid, pp. 18—19
29. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም ፡ (አዲስ አበባ ፡ ጳጉሜ 1976) ገጽ 126
30. መንግሥቱ ኃይለማርያም ፡ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሪፖርት ፡ ለብሔራዊ ሸንጐ የመጀመሪያ ስብሰባ የቀረበ (አዲስ አበባ ፡ ጳጉሜ 1979) ገጽ 69
31. በትምህርት ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምህርት መምሪያ ፡ ሥርዓተ ትምህርት ከየት ወዴት ? የካቲት 1979 (ያልታተመ)
32. ከላይ የተጠቀሰው
33. V.I. Lenin in his notes to the Thesis of Krupskaya.
34. የኢሠፓ ፕሮግራም ፡ ጳጉሜ 1976 ፡ አዲስ አበባ ገጽ 126።

ዋጋው ብር 1.25

B.S.P.P